# በዘመኑ ፍጻሜ የተቀቡ

ጉባኤ ሆይ፡ ደህና አደራችሁ። እስኪ ከጌታችን ጋር እንነጋገር።

2 በዚህ ሰዓት በዚህ ማለዳ፡ በሰማያዊ ፈቃድ እንድናመልክህ የሰብሰብከን፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ ታላቅ አምላክ ሆይ። ጌታ ሆይ፡ አሁንም አንተ ልታሳውቀን የወደድከው ሁሉ፡ ይሆንልን ዘንድ፡ በልባችን ሙሉ ማንነታችንን ለሰማያዊ ፈቃድህ፡ እና ለመንፈስ ቅዱስ ስራ አሳልፈን እንሰጣለን። የተሻሉ ክርስቲያኖች እና የተሻሉ አምባሳደሮችህ መሆን መሻታችን ነው። አንተን እየጠበቅንህ ሳለን፡ ዛሬ በዚህ ማለዳ ይህን ታደርግልናለህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

3 ተቀመጡ። [አንድ ሰው "የጸሎት ጨርቆችን እናውልቅ?" አለ፡—አርታዒ።] አዎን። እንደገና ዛሬ ማለዳ በዚህ ሰፍራ፡ በ—በ ታላቁ ንጉሰ አገልግሎት ስለተገኘን በጣም ደስተኞች ነን። እናም፡ ለህዝቡ የሚሆን፡ በቂ ክፍል ስለሌለን፡ በድጋሚ ይቅርታ እንጠይቃለን፡ ነገር ግን… በሁኔታዎች መካከል፡ የቻልነውን ሁሉ ለማድረግ እንሞክራለን።

4 አሁን፡ እዚህ ጋር ብዙ የጸሎት ጥያቄዎች እና መሃረቦች አሉ። እናም ለጊዜው ወደ አንድ ጥግ ላይ አቆያቸዋለሁ፥ እየተውኳቸው አይደለም፡ ነገር ግን እጸልይላቸዋለሁ… በዋነኝነት… ዛሬም ማታ፡ በዚህ ማለዳ፡ እንደገናም ዛሬ ማታ፡ እጸልይላቸውና፡ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲፈውሳቸው እጠብቃለሁ። ለ—ለመሃረቦች እና ለሌሎችም መጸለይ የምፈልገው ያኔ ነው።

5 እጅግ ወሳኝ የሆኑትን የጸሎት ጥያቄዎችን፡ ቢሊ፡ እያንዳንዳቸውን፡ ለእኔ ሰጥቶኛል። ወደ ሶስት መቶ ይሆናሉ፡ እና ያን ጊዜ፡ ገና ከቢሮ እንደወጣሁ ነው። አያችሁ፡ በተቻለኝ ፍጥነት ወደ እነሱ እሄዳለሁ፡ የቻልኩትን ያህል፡ ሁሉንም አዳርሳለሁ። እና በተቻለኝ መጠን በፍጥነት አገኛቸዋለሁ። ሁሉንም ላዳርስ አልችልም ይሆናል። ልክ እዚያ ስደርስ፡ አንዱን እይዝና፡ እንዲህ እላለሁ፡ "ጌታ ሆይ፡ **ይሄኛው** ነውን፡ ወይስ **ይሄኛው**?" ምክኒያቱም፡ ሁሉም፡ እያንዳንዳቸው፡ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል፡ ጥያቄአቸው እውነተኛ ነው፥ ስለዚህ ጉዳይ፡ መነጋገር እንዳለብን፡ ምንም ጥርጥር የለውም። እና እኔ… ታውቃላችሁ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ እኔ የማነበውን፡ በልቤ የሚመላለሰውን፥ ራሱን ሊናገረኝ ይችላል፡ እንደገና ወደዛ ሄጄ እስካገኘው ድረስ በዚያ እፈልገዋለሁ። ካልሆነም፡ በዘፈቀደ እወስዳቸዋለሁ።

6 አሁን፡ በዚህ ማለዳ፡ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉትን ደግሞ፡ ሰላም ለማለት እንፈልጋለን። ዛሬ ማለዳ በቴሌፎን መሰመር ውስጥ ያሉትን ወዳጆቻችንን ሰላም ለማለት እንፈልጋለን፡ በኒውዮርክ ከተማ፥ በቢውሞንት፡ ቴክሳስ፥ ፕሪስኮት፡ አሪዞና፥ ቱሰን፡ አሪዞና፥ ሳን ሆሴ፡ በካሊፎርኒያ፥ ኮነክቲከት፥ ጋንስቬል፡ ጆርጂያ፥ በኒው አልባኒ፡ እንዲያና፡ በመላው አገሪቱ ያሉትን ሰላም እንላለን። በጌታ በኢየሱስ ስም ሰላም እንላችኋለን።

7 ዛሬ ጠዋት፡ ኢንዲያና ውስጥ፡ ማለዳው ደስ ይላል። ትናንት ምሽት እየሩን ያቀዘቀዘ ዝናብ ዘንቦ ነበር። እኛም… ተበርናክሉ ሞልቶ ተጨናንቋል፡ ሰው

ሁሉ፡ በታላቅ ጉጉት፡ የሰንበትን ትምህርት እየጠበቀ ይገኛል። በዚያም ታላቅ የእግዚአብሔር በረከት እንደሚያገኛችሁ አምናለሁ።

8 በተቻለ ፍጥነት፡ ሁላችንም፡ አንድ ላይ የምንሰበሰብበት፡ ምናልባት—አንድ ትልቅ ድንኳን ስር፡ በእርግጠኝነት ስለ ሰባቱ የመጨረሻ መቅረዞች የምሰብክበት ጊዜ፡ ቶሎ እንደሚመቻች ተስፋ እናደርጋለን።

9 ስለዚህ አሁን፡ በዚህ ማለዳ በዚህ ታላቅ ትምህርት ሬዥም ጊዜ እንወስድም... "ጌታ ሆይ ምን ልናገር?" እያልኩ፡ በፊቱ ቀርቤ ነበር፡ ይህ የመጨረሻው አገልግሎታችን እንደሚሆን አውቅ ነበርና። የጌታ መምጣት በጣም ቅርብ ነው!

10 በካሊፎርኒያ ከተደረገው ትንበያ በኋላ፡ በዚያ ያሉትን፡ ብዙ ቤቶች፡ እና ቦታዎች፡ በሰዓት በሰላሳ ኢንች ፍጥነት ሲሰጥሙ፡ ጣውላዎች ሲሰነጣጠቁ እና ሲሰባበሩ አይቻለሁ። እንዲህ እንዲሆን የሚያደርገው አያውቁትም። ፍጻሜ ላይ ነን። በመቶ-ሺ-ዶላር የሚገመቱ ቤቶች፡ እየሰጠሙ ናቸው። ዛሬ ማታ አቀርበዋለሁ ብዬ ተስፋ ያደረግኩት፡ ምስሎችን የያዘ፡ ታላቅ የጋዜጣ አርዕስተ ዜናዎችን አይቻለሁ፡ ዛሬ ማታ በዚያ ዙርያ አንዳች ነገር መናገር እፈልጋለሁና።

11 ከዚያም፡ ዛሬ ምሽት፡ ለታመሙት እንጸልያለን። ከሰዓት በኋላ፡ አሰራ አንድም፡ አሰራ ሁለት ሰዓትም ይሁን፡ ብቻ ኑ። ህዝቡ በጊዜ እንዲመለስ፡ በጊዜ እንጀምራለን፡ እና የጸሎት ካርዶቻችሁን እንድትቀበሉ፡ እሰባለሁ። እናም እንደ ጌታ ፈቃድ፡ ዛሬ ማታ ለታመሙት እንጸልያለን።

12 አሁን፡ እዚህ ጋር ለተናገርኩት ለእያንዳንዱ ነገር የሆነ ቀን መልስ መስጠት እንዳለብኝ ሰለማውቅ፡ በጸሎት ተሞልቼ "ምን ማድረግ እንዳለብኝ?" ካሰብኩ በኋላ... ዛሬ ማለዳ መንፈስ ቅዱስ በትንቢት እንዲናገረን፡ ወይም እንዲያሳውቀን፡ ወሰንኩ። አያችሁ? ምናልባት አንዳንድ ጊዜ... ካልተነገረን፡ እና ነገር ሁሉ እንዲሁ በተለመደው ከሆነ፡ ማወቅ ያለብን ነገር ነው። መንፈስ ቅዱስ የሚመጣውን ሕዝብ፡ ማስጠንቀቅ እንድንችል ሰጥቶናልና። ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልገለጠ በቀር፡ ምንም ነገር አያደርግም፡" ይላል። እና—ኢየሱስ ምን እንደሚከሰት፡ ሕዝቡን እንዴት እንዳሰጠነቀቀ፡ ነቢያትም ምን እንደሚከሰት፡ ሕዝቡን በደንብ አስጠንቅቋል። አሁንም በምንኖርበት ታላቅ ሰዓት፡ በምንኖርበት ዘመን፡ ምን እንደ ሆነ እና፡ በዚህ ዘመን፡... ምን እንደሚከሰት ማየት ለእኛ ተገቢ ነው። ስለዚህ ምናልባትም ብዙ ጊዜ ካነበብናቸው ከእነዚህ እንግዳ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ፡ ዛሬ ጠዋት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ለሰዎች ለ—ለመናገር ወደ ልቤ መጣ።

13 አሁን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳችን ከማቴዎስ 24ኛው ምዕራፍ እናነባለን፡ ከቃሉ የተወሰነ ክፍል እናንብብ [ወንድም ብራንሃም ጎሮርውን አጸዳ—አርታዒ።] (ይቅርታ።) ለርዕሰ ጉዳያችን እውደ—ጽሑፍ ለማግኘት ይጠቅመናል።

14 አሁን፡ ይህንን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማስተማር እንደምንሄድ አስታውሱ፡ በዝግታ። ብዕራችሁን እና ወረቀታችሁ ያዙ። እዚህ ላይ የተጻፉ ብዙ ጥቅሶች ይዣለሁ፡ ሁሉንም—መጻፍ ብትችሉ ጥሩ ነው። ይህ የሰንበት

ትምህርት ክፍል ነው ስለሆነ፡ ወደ ቤት ስትሄዱ አንብቧቸው፡ ስለምንኖርበት ጊዜ ማወቅ፡ እና መጠንቀቅ እንድንችል ይረዳናል።

15 በቅዱስ ማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ፡ [ወንድም ብራንሃም ጎርሮውን አጸዳ—እርታዒ።] (ይቅርታ።) 24ኛ ቁጥር፡ ወይም፡ ማለቴ፡ 24ኛው ምዕራፍ ላይ፡ ከ15ኛ ቁጥር ጀምሮ፡ ከቃሉ የተወሰነ ክፍል ማንበብ እፈልጋለሁ።

> እንግዲህ **በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን፡ የጥፋትን ርኩሰት፡ በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፡ (አንባቢው፡ ያስተውል፡)**
>
> **በዚያን ጊዜ በይሁዳ** ያሉት **ወደ ተራራዎች ይሽሹ፡**
>
> **በሰገነት—በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፡-**
>
> **በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።**
>
> **በዚያችም ወራት ለርጉዞችና፡ ለሚያጠቡ ወዮላቸው!**
>
> **ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት፡ ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፡**
>
> **በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ፡ እንግዲህም፡ ከቶ የማይሆን፡ ታላቅ መከራ ይሆናልና።**
>
> **እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ፡** ሥጋ የለበሰ ሁሉ **ባልዳነም ነበር፡ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።**
>
> **በዚያን ጊዜ ማንም፡ እነሆ፡ ክርስቶስ ከዚህ አለ፡ ወይም፡ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ።**
>
> **ሐሰተኞች ክርስቶሶችና፡ ሐሰተኞች ነቢያት፡** ይነሣሉና፥ **ቢቻላቸውስ፡** የተመረጡትን **እንኳ እስኪያስቱ ድረስ፡ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።**
>
> **እነሆ፡ አስቀድሜ ነገርኋችሁ።**
>
> **እንግዲህ፡ እነሆ፡ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፡ እነሆ፡** በእልፍኝ **ነው ቢሉአችሁ፡ አትመኑ።**
>
> **መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ፡ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።**
>
> **ስጋ ወዳለበት፡ በዚያ ንሰሮች ይሰበሰባሉ...**

16 አሁን፡ እንደ ርዕሰ ጉዳይ፡ 24ኛውን ጥቅስ መውሰድ እፈልጋለሁ፡ ይህም ዛሬ ጠዋት ለምናስተምረው የሰንበት ትምህርት ይህን ጥቅስ ለማጉላት ነው። ይህን እንደገና ሳነበው፡ በጥንቃቄ አዳምጡ።

> **ሐሰተኞች ክርስቶሶችና፡ ሐሰተኞች ነቢያት፡** ይነሣሉና **የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፥** የተመረጡትን **እንኳ እስኪያስቱ ድረስ፡ ታላላቅ ምልክትና፡ ድንቅ ያሳያሉ።**

17 አሁን ዛሬ ጠዋት ለምናነሳው ርዕሰ ጉዳይ፡ ወይም ጽሑፍ፡ **በዘመኑ ፍጻሜ የተቀቡ፡** የሚል ርዕስ፡ መጠቀም እፈልጋለሁ። እኔ መናገር የምፈልገው ርዕሰ ጉዳይ፡ ወይም ጽሑፍ፡ **በዘመኑ ፍጻሜ የተቀቡ** የሚል ይሆናል።

18 የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን እንደሆነ አምናለሁ። ሁላችሁም እንዲሁ ይመስለኛል... የቅዱሳት መጻሕፍትን አንባቢ፡ ወይም አ—አማኝ የሆነ ሰው፡ አሁን በዓለም ታሪክ ፍጻሜ ላይ መሆናችንን ያውቃል ብዬ አስባለሁ። የሚያነበው ሰው ስለማይኖር፡ መጻፍ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። በዘመኑ ፍጻሜ ላይ ነንና። መቼ እንደሆነ፡ እኔ አላውቅም። ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ፡ የሰማይ መላእክት እንኳ ያንን ደቂቃ ወይም ሰዓት አያውቁም። ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረን፡ እነሆ፡ እነዚህ ነገሮች መፈጸም ሲጀምሩ፡ መዳናችን ቀርቧልና ራሳችንን ቀና ማድረግ ይገባናል። አሁን፡ "ቀርቧል" ማለት፡ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። ምናልባት...

19 የሳይንስ ሊቃውንት ባለፈው፡ በቴሌቪዥን እንደተናገሩት፡ በሺዎች-የሚቈጠሩ-ማይሎች ርዝመት ያለው የምድር ክፍል እንደሚሰጥም ነው። በቀደም ሰለ ሎስ ኤንጀለስ፡ ምዕራባዊው ዳርቻ "ሊሰምጥ ይችላልን?" የሚል ጥያቄ፡ ተጠይቀው ነበር። ብዙዎቻችሁም በራዳር እንዴት እንደተከተሉት፡ እስከ ታች እስከ ሳን ሆሴ ድረስ ተሰንጥቆ... እንደሄደ፡ ወደ አላስካ ተሻግሮ፡ በአሉሽያን ደሴቶች በኩል፡ ሁለት መቶ ማይል ያህል ወደ ባሕሩ ተሻግሮ፡ ወደ ሳን ዲዬጎ ተመልሶ፡ በሎስ አንጀለስ ጀርባ ይዞርና፡ ማዶ ተሻግሮ፡ ወደዚያ መድረሱን አይታችኋል።

20 ይህ ሁሉ ርዕደ መሬት ሲደርስብን የኖረው፡ እሳተ ገሞራው ይህንን ትልቁን ስንጥቅ፡ ሲለሚመታው ነው። እነሱ—የሰየሙትን ስያሜ መጥራት አልችለውም። ይሁን እንጂ፡ በሚናወጥበት ጊዜ፡ በምዕራብ ጠረፍ ለዓመታት ሲከሰቱ የነበሩትን ርዕደ መሬቶችን ያስከትላል። አሁን ዙሪያው ሁሉ ተሰንጥቋል። የሳይንስ ሊቃውንቶች እንዳሉትም፡ አንዱ...

ሰውዬ ሌላኛውን "ይሄ ሊወድቅ ይችላልን፡" አለው?

"'ይችላልን' ብቻ ሳይሆን፡ በርግጥ ይሆናል፡" አለው።

አለውም፡ "ምናልባት በትውልዳችን ላይሆን ይችላል፡ አይደል?"

"በሚቀጥሉት አምስት ደቂቃዎች፡ ወይም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ። መቼ እንደሆነ በትክክል አናውቅም፡" አለው።

21 በዚህ ሳምንት፡ በጋዜጣ ውስጥ አንድ ርዕስ ተልኮልኝ ነበር፡ ብዙ ትልልቅ የመቶ-ሺህ-ዶላር ቤቶች ሲሰነጣጠቁ እና ሲሰባበሩ፡ ሰዎች እየሸሹ ነው። እና እንዴት ማቆም እንዳለባቸው አያውቁም። ለማቆም ምንም መንገድ የለም። አያችሁ፡ እግዚአብሔር የፈለገውን ማድረግ ይችላል፡ እንዴት ማድረግ እንዳለበትም ማንም ሊነግረው አይችልም።

22 ቤቶችን ትገነባላችሁ፡ ሳይንሳዊ ነገሮችን ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ እግዚአብሔርም የሳይንስ ፈጣሪ ነው። እንዴት ልታስቆሙት ትችላላችሁ? ከፈለገ ዛሬ ጠዋት ምድርን በቁንጫዎች ሊያጠፋ ይችላል። ታውቃላችሁ፡ እሱ ቁንጫ ወደ መኖር እንዲመጡ መናገር ይችላል፡ እነርሱም ግማሽ ሰዓት ጊዜ ውስጥ አርባ ማይልስ ያህል ጥልቀት ምድርን ሊሞሉ ይችላሉ፡ አያችሁ፡ የለም... እና ሰዎችን ከመሬት ላይ በልተው ሊያጠፉ ይችላሉ። እርሱ እግዚአብሔር ነው። የሚሻውን ብቻ ይሠራል። እርሱ በራሱ፡ ሉዓላዊ ነው።

23 አሁን፡ ይህን ሁሉ የተከማቸ ማስረጃ ስንመለከት፡ አሁን የምንኖርበት ሰዓት፡ ማኅተሞቹ ስለተከፈቱ እነዚህን ነገሮችን መለማመድና ማንሣት፡ እግዚአብሔርም በጸጋው፡ እነዚህን ነገሮች ለእኛ ለማሳየት፡ ለእኛ ታማኝ እንደሆነ፡ የእነዚህን ነገሮች እውነት ማወቅ፡ ለእኛ ጥሩ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ።

24 ኢየሱስ በማቴዎስ 24 ላይ፡ "ክርስቶሶች፡" C-h-r-i-s-t-s፡ "ክርስቶሶች" የሚለውን ቃል እንደተጠቀመ ልብ በሉ። ሊብዙ እንደሚናገር "ክርስቶሶች፡" አለ እንጂ፡ በነጠላ ቁጥር፡ ክርስቶስ አላለም። "ክርስቶሶች።" ስለዚህ፡ **ክርስቶስ** የሚለው ቃል "የተቀባ" የሚል ትርጓሜ አለው። እንግዲያውስ "የተቀቡ" ከተባለ፡ አንድ ብቻ አይደለም፡ ብዙ ቅቡዓን ማለትም፡ "የተቀቡ" ይሆናሉ። አያችሁ?

25 አለበለዚያ፡ ይብዛም ይነስም እንድንረዳው ቢፈልገን ከፋፍሎ ይለው ነበር፡ "በዘመን ፍጻሜ፡ ሐሰተኛ ቅቡዓን ይነሣሉ፡" ይለን ነበር። አሁን፡ ይህ ማለት የማይቻል ይመስላል፡ ኣያችሁ፡ "የተቀባ" የሚለው ቃል ጉዳይ፡ ነገር ግን ቀጥሎ ያለውን ቃል ልብ በሉ፡ "ሐሰተኛ ነቢያቶች"፡ p-r-o-p-h-e-t-s፡ ብዙ ቁጥር።

26 አሁን፡ **የተቀባው፡** ማለት፡ "መልእክት ያለው" ማለት ነው። መልዕክቱ ሊተላለፍ የሚችለው **በተቀባ** ሰው ብቻ ሲሆን፡ ያም ሰው ነቢይ፡ የተቀባ ነው፡ "የተቀቡ፡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ይነሣሉ።" ነቢይ ማለት መልዕክቱ ምን እንደሆነ የሚያስተምር ነው። የተቀቡት አስተማሪዎች፡ ነገር ግን በሐሰት ትምህርት የተቀቡ ሰዎች ናቸው። የተቀቡ፡ "ክርስቶሶች፡" ብዙ ቁጥር፡ "ነብያት፡" ብዙ ቁጥር። በነጠላ ቁጥር ክርስቶስ—የሚባል ነገር ካለ፡ እንግዲያውስ እነዚህ ሰዎች ደግሞ "የተቀቡ፡" መሆናቸው ነው፡ እነዚህ ሰዎች የተቀቡ፡ ወይም ቅቡዎች እስከሆኑ ድረስ፡ ብቸኛው ልዩነታቸው የሚያስተምሩት ትንቢት ነው።

27 አሁን፡ ይህ የሰንደይ ስኩል ትምህርት ነው፡ ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካኝነት፡ ይህን በትክክል ማሳየት—እንፈልጋለን፡ ሌላ ሰው በሚናገረው ነገር ሳይሆን፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን በማንበብ ነው።

"ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ቅቡዓኑስ... ? ምን ነበሩ? " ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል።

"ክርስቶሶች፡" C-h-r-i-s-t-s። "የተቀቡ ክርስቶሶችና፡ ሐሰተኛ ነቢያት።" የተቀቡ፡ ግን ሐሰተኛ ነቢያት!

ኢየሱስ፡ "ዝናብ በጻድቃን እና በኃጥያተኞች ላይ ይወርዳል፡" ብሏልና።

28 አሁን፡ አንድ ሰው እንዲህ ሊለኝ ይችላል፡ "የእነዚያ ሰዎች መቀባት ማለት የመንፈስ ቅዱስ መቀባት ነው ብላችሁ ታምናለህን? " እዎን፡ ወዳጄ፡ እውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይወርድበታል፡ ሰውዬው ግን ሐሰተኛ ነው።

29 አሁን በጥሞና አዳምጡኝ እና ምን እንደተናገረ እዩ። "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፡ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።" እናም በእውነተኛው መንፈስ ቅዱስ የተቀቡ ናቸው። ይህ በጣም ሞኝነት

እንደሚመስል አውቃለሁ፡ ነገር ግን ጊዜ ወስደን በቃሉ እናብራራዋለን፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ይህ ፍጹም እውነት ነው።

30 አሁን ለአንድ ደቂቃ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችንን፡ ከማቴዎስ ምዕራፍ 5 ላይ እንክፈት፡ ከ—ከቁጥር 45 እንጀምራለን፡ እስቲ አሁን እነዚህን ጥቅሶች ለጥቂት ጊዜ ስናነብ እንመልከት። ከዚያም፡ ወደዚህ ከደረስን በኋላ፡ ለምን፡ እንሰጣችኋለን... ስለዚህ እናንተ፡ ሁሉንም ማንበብ ካልቻላችሁ፡ የራሳችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ስላላችሁ፡ እንዲሁም እኛ—እኛ ከዚህ ከሄድን በኋላ ወደ ቤትም ስትሄዱ ማንበብ ትችላላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን—እንደሚልም ማንበብ ትችላላችሁ።

31 አሁን ጊዜያችንን ወስደን፡ አንድ—መሰረታዊ እውነታ ለመረዳት እንሞክር፡ ምክንያቱም እዚህ ላይ የምናገረው ነገር አስገራሚ ነገር ነው። መንፈስ ቅዱስ ሐሰተኛ አስተማሪን እንዴት ሊቀባ ይችላል? ኢየሱስ ግን ይህ እንደሚሆን ተናግሯል።

አሁን፡ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 5፡ ከቁጥር 45፡ አሁን እናንብብ። ትንሽ—ከፍ ብለን፡ ከ44ኛው ቁጥር፡ እንጀምራለን።

> **እኔ ግን እላችኋለሁ፡ በሰማያት ላለ አባታችሁ፡ ልጆች፡ ትሆኑ ዘንድ፡ ... ጠላቶቻችሁን ውደዱ፡ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣**
>
> **ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፡ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ፡ ፀሐይን... ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ... ዝናቡን ያዘንባልና።** (ዝናብ በጥሩዎቹ ላይ እንደሚዘንብ ሁሉ በክፉዎቹም ላይ ይዘንባል።)

32 ከዚህ ቀጥሎ፡ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ወዳለው ሌላ ትንቢት፡ ወደ ዕብራውያን ምዕራፍ 6 እንሂድ፡ በዚህ ላይ የሚቀጥለውን-ቁጥር ለማግኘት፡ ጳውሎስ ኢየሱስ የተናገረውን ተመሳሳይ ነገር ወደ አዕምሯችን ያመጣል። ተናጋሪው፡ ጳውሎስ ነው። ይህን እያደናችሁ ሳላችሁ... እናንተም በመገናኛው ዘዴ ላይ ያላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አጠገባችሁ አርጋችሁ ማስታወሻ ያዙ፡ እና ተመልከቱ። ዕብራውያን፡ ምዕራፍ 6 ላይ፡ ጳውሎስ ለእብራውያን ሰዎች መልዕክት ሲጽፍ፡ ጥላዎቹንና ምሳሌዎቹን እያሳያቸው፡ ከአይሁድ እምነት ወደ ክርስትና እምነት በማምጣት፡ አሮጌዎቹ ነገሮች ሁሉ ወደፊት ለሚመጡት ነገሮች ተምሣሌት መሆናቸውን ያሳያቸዋል። በዕብራውያን 6፡ ጳውሎስ እየተናገረ ነው።

> **ስለዚህ የክርስቶስን** (C-h-r-i-s-t፡ ነጠላ ቁጥር) **ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን፡ ወደ ፍጻሜ እንሂድ፥ መሠረትን ደግመን አንመሥርት፡ እርሱም የሞተ ሥራ ንሰሐና...** በ**እግዚአብሔር ያለን እምነት ነው።**
>
> **ስለ... ጥምቀቶችና፡ እጆችንም ስለ መጫን፡ ስለ ሙታንም ትንሣኤ፡ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።**
>
> **እግዚአብሔርም** ቢፈቅድ፡ **ይህን እናደርጋለን።**
>
> **አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፡ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን፡** ከመንፈስ **ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡**

33 ለጥቂት ደቂቃዎች ትኩረታችሁን ለመሳብ እፈልጋለሁ። አስተውላችኋል? ያም "ስጦታ" ይላል እንጂ፥ "ስጦታዎች፡ ሰማያዊውንም ስጦታዎች የቀመሱትን" አይልም"፥ ነገር ግን፡ "ሰማያዊውንም ስጦታ፡" ነጠላ ነው፥ "ክርስቶስ፡" ነጠላ ነው፥ "ስጦታ፡" ነጠላ ነው።

> **... ሰማያዊውንም ስጦታ፡ የቀመሱትን...** ከመንፈስ **ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡**
>
> **መልካሙንም የእግዚአብሔርን... ቃል የቀመሱትን፡**... (ምን የቀመሱትን? )... **የእግዚአብሔርን ቃል፡ እና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን፡**
>
> **በኋላም የካዱትን፡ እንደገና ለንስሐ** እነርሱን **ማደስ የማይቻል ነው፥ ራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና፡ ያዋርዱትማልና።**
>
> **ሉብዙ ጊዜ፡** (አዳምጡኝ) **በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ... የምትጠጣ መሬት፡** ብዙ ጊዜ **በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፡ ከእግዚአብሔር** በረከትን ታገኛለችና፡
>
> **እሾህና ኩርንችትን ግን ብታወጣ... የተጣለች ናት፡ ለመረገምም ትቀርባለች፣ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።**

34 አሁን ያንን ከማቴዎስ 5፡24 ጋር በድጋሚ አነጻጽሩት። አስተውሉ፡ በምድር ላይ የሚወርዱ ጸሐይ እና ዝናብ፡ እግዚአብሔር ለምድር ወገኖች ምግብ እና ሌሎች ነገሮችን ለማዘጋጀት ያወርዳቸዋልና። ዝናብ፡ ለዕጽዋት ለምግባቸው ይላካል። ነገር ግን አረም፡ እና እንክርዳድ፡ በሜዳ በመሆናቸው፡ ተመሳሳይ ዝናብ ያገኛሉ። ያው ዝናብ ስንዴ እንዲያድግ የሚያደርገው ያው ዝናብ እንክርዳዱም እንዲያድግ ያደርጋል።

35 ከጴንጤቆስጤ ሰዎች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በተገናኘሁ ጊዜ፡ እንደዚህ ያለ ትምህርት በአንድ ጊዜ አገኘሁ! ያ ለእኔ ትልቅ ትምህርት ነበር። ሁለት ሰዎችን አየሁ፡ አንደኛው... ከዚያ በፊት ልሳኖች በጭራሽ ሰምቼ አላውቅም ነበር። እና አንደኛው በልሳን ሲናገር፡ ሌላኛው ይተረጉመዋል፡ ወይም-በተቃራኒ፡ እና እውነቱን ይናገሩ ነበር፡ "በዚህ ምሽት ንስሃ መግባት ያለባቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ሴቶችም፡ ወንዶችም አሉ፡" እሉ ይሉ ነበር። ሰዎችም ተነስተው ወደ መሠዊያው ይሄዳሉ።

"እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው!" ብዬ አሰብኩ፡

36 እና በነበረችኝ ትንሽዬ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፡ ሰዎቹን አነጋገርኳቸው፡ እንደው፡ የመለየት ጸጋ፡ እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ምን መሆኑን ለማወቅ ነበር። አንደኛው እውነተኛ ክርስቲያን፡ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ነበር፡ ሌላኛው ደግሞ ግብዝ ነበር። አንደኛው፡ ግብዝ የነበረው፡ ጥቁር-ጸጉር ያላት ሚስት የነበረችው ሲሆን፡ ወርቃማ ጸጉር ካላት ሴት ጋር ይወጣል ይገባል ልጆችም ወልዷል። በቃ፡ ሊካድ አይችልም፡ ግልጽ ራእይ ነበርና። እኔም ስለ ጉዳዩ አነጋግሬው ነበር። አየት አርጎኝ በህንጻው በኩል ዞረ።

37 በቃ፡ ግራ ተጋባው። ወደ መላዕክት ጉባኤ የመጣሁ መሰሎኝ ነበርና፡ ምናልባት በአጋንንት ጉባኤ እንዳልሆን አልኩ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሊገባኝ አልቻለም። ለብዙ ዓመታት እጆቼን አጣጥፌ ዝም አልኩ፡ አንድ ቀን ግን...

ከሴቷ ልጄ ጋር የሚሄደው፡ ከጆርጅ ስሚዝ፡ ጸሎት ለማድረግ ወደምሄድበት ወደ ጥንታዊው ወፍጮ ቦታ፡ ትላንት አንድላይ ሄደን ነበርን።

38 በዚያም ሁለት ቀን ከቆየሁ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ ይህንን ጥቅስ መልሶ ሰጠኝ፡ "ዝናም ብዙ ጊዜ ምድርን ያለብሳልና፡ ፍጻሜአቸው ለመቃጠል የሆኑትን እሾህና አሜከላም፡ በዚያው ዝናብ ይኖራሉ።" ህይወት-ሰጪ በሆነው በተመሳሳይ በእግዚአብሔር ምንጭ ይኖራሉ። ያን ጊዜ፡ ይህ ተረዳሁ፡ እየሱስ ሲናገር፡ "በ" "በፍሬያቸው ይታወቃሉ፡" ብሏል።

39 ስለዚህ፡ አሁን፡ በምድር ተፈጥሯዊ እጽዋቶች ላይ የሚዘንበው ዝናብ፡ ዘላለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ የመንፈሳዊ ዝናብ ተምሳሌት ነው፡ ይህም በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚዘንብ ነው፡ እኛም ፊተኛው ዝናብ እና የኋለኛው ዝናብ ብለን እንጠራዋለን። ይህም ዝናብ፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ፡ በቤተክርስቲያኑ ላይ የሚያፈስ ዝናብ ነው።

40 አስተውሉ፡ እዚህጋ በጣም እንግዳ ነገር ነው። አያችሁ? ወደ ምድር የተዘሩ እነዚያ ዘሮች፡ ምንም እንኳ በዚያ ውስጥ ቢገቡም፡ ከመጀመሪያ እሾህ የነበሩ ናቸው። ምድር ላይ የተዘራው ስንዴ፡ እና የለመለሙ ዛፎች ሁሉ፡ ከጅምሩ እጽዋቶች የነበሩ ናቸው። ስለዚህ ደጋግመው እራሳቸውን የሚያፈሩ ዛፎች፡ ከጅምሩ፡ በመጀመሪያ በዋናው የነበሩ እንደሆነ ያስረዳል።

41 "የሚቻል ቢሆን ኖርስ የተመረጡትን ያስታሉ፡" ምክንያቱም ተመሳሳይ ዝናብ፡ ተመሳሳይ በረከት፡ ተመሳሳይ ምልክቶችን፡ ተመሳሳይ ድንቆችን ያሳያሉ። አያችሁ? "ያስታሉ፡ ወይም የሚቻል ቢሆን ኖርስ የተመረጡትን ያስታሉ።" አሁን፡ እሾህ እሾህ ልሁን ብሎ ሊሆን አይችልም፡ ስንዴም እኔ ስንዴ ልሁን ብሎ መሆን አይሆንም፡ ፈጣሪ እያንዳንዳቸውን በመጀመሪያ ላይ የወሰነላቸው ነገር ነው። የተመረጡ ማለትም ይህ ነው። ተመሳሳይ ዝናብ!

42 ፀሐይ በማለዳ ትወጣለች እናም በዚህች ምድር እና እኛ በምንኖርበት ቀን ላይ፡ እንደነበረው ሁሉ በምድር ላይ ትሰራጫለች። ፀሐይም፡ በምስራቅ የምትወጣው ፀሐይ በምዕራብ ከምትጠልቀው ፀሐይ ጋር ተመሳሳይ ፀሐይ ነች። እና ያቺ ፀሐይ የተላከችው፡ ሰውነታችን የተሰራበትን እህል በምድር ላይ ለማብቀል ነው።

43 እኛ የምንኖረው በሞተ ንጥረ ነገር ነው። ያ መኖር የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ነው። እናንተ በየቀኑ እንድትኖሩ፡ ተፈጥሮአዊ የሆነ ነገር መሞት ካለበት፡ እንግዲያውስ ሰውነታችሁ ደግሞ ከ— ሰውነታችሁ ተፈጥሯዊ ሕይወት ለመኖር፡ በሟች ንጥረ ነገር መኖር ካለበት፡ መንፈሳዊ ሕይወታችሁ ለማዳንም፡ የሚሞት መንፈሳዊ ነገር፡ ሊኖር ይገባል። እግዚአብሔርም፡ እኛ በሕይወት፡ መኖር እንድንችል ዘንድ፡ ሥጋ ለብሶ ሞተ። በአለም ላይ ከእግዚአብሄር በቀር ሊያድናችሁ የሚችል ሌላ ነገር፡ ሌላ ቤተክርስቲያን የለም። የሚኖሩበት ብቸኛው መንገድ ነው።

44 ቅዱሳት መጻሕፍትን እናንብብ። ኢየሱስ ቃል ነው። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም ዘንድ አደረ። በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ፡ ኖረም፡ በእኛም ዘንድ አደረ።” “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡” ለሰጋው፡ “በእንጀራ ብቻ አይኖርም።” ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እኛ የምንኖረው በቃሉ፡ ማለትም በእግዚአብሔር ነው።

45 አሁን ፀሀይ መጥታ እህሉን ታደርሳለች። አሁን፡ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ማድረስ አትችሉም። እያደገ ሲሄድ፡ እየበሰለ፡ ሙሉ በሙሉ እስኪደርስ ድረስ ያለማቋረጥ ያድጋል።

46 ዛሬም፡ በቤተክርስቲያን፡ እንዲሁ ነው። የተጀመረውም ገና በጨቅላነቱ፡ በጨለማው ዘመን፡ ከመሬት በታች በነበረበት ጊዜ ነው። አሁን ወደ ብስለት አድጓል። እኛም እግዚአብሔርን፡ ዘወትር በተፈጥሮ ውስጥ እንዴት እንደሆነ፡ በትክክል ማየት እንችላለን...

47 ተፈጥሮን ማዛባት አትችሉም። የዘመኑ ችግር ይህ ነው። ቦምቦችን እንወረውራለን፡ ውቅያኖስ ውስጥ፡ በአቶሚክ ቦምብ ውስጡን እናፈነዳለን እንሰባብራለን። ቆሻሻውን ደጋግማቹ ትወረውራላችሁ፡ ወደ ውስጡም ትጥላላችሁ። ዛፎችን ትቆርጣላችሁ፥ ዓውሎ ንፋስ ይወስዳችኋል። ወንዙን ትገድባላችሁ፡ ከዚያም አልፎ ይጎርፋል።

48 እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያከናውንበትን መንገድ መርምራችሁ በዚያ መጽናት አለባችሁ። ሰዎችን በቤተክርስቲያን እና በድርጅት የተቋም አባላት አድርገናል፥ ውጤታችንን ተመልከቱ! እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ ጸንታችሁ ቁሙ።

49 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ወደ ርዕስ ጉዳያችን ስንመለስ፡ “በመልካሞችና በክፉዎች” ላይ “ዝናብ ያዘንባል፡”። ኢየሱስ በማቴዎስ 24 ላይ፡ በመጨረሻው ዘመን ምልክት እንደሚሆን፡ ይነግራችኋል።

50 አሁን፡ ይህ ምልክት የሚታወቀው በመጨረሻው ዘመን ከሆነ፡ ከማህተሞቹ መከፈት በኋላ መሆን አለበት። አያችሁ? የመጨረሻው ዘመን ምልክት ነው። እነዚህ ነገሮች፡ በሚፈጸሙበት ጊዜ፡ የመጨረሻው ጊዜ ይሆናል። እና ምልክት ይሆናል፡ አሁን፡ ስለዚህ የተመረጡት በእነዚህ ነገሮች ግራ አይጋቡም። አያችሁ? ከዚያም፡ የተገለጠ እና፡ የሚታይ መሆን አለበት።

አስተውሉ፡ ስንዴውና እንክርዳዱ የሚኖሩት ከሰማይ በሚመጣው በተመሳሳይ ቅባት ነው። ሁለቱም በዚህ ይደሰታሉ።

51 ይህን አስታውሳለሁ፡ በዚያ ቀን በግሪንስ ሚል ላይ የነበረውን ሁኔታ መለስ ብዬ አስባለሁ። ያን ራዕይ ሲመጣ አ—እየሁ። እነሆ ታላቅ መሬት ነበረች፡ በደንብ ተለሳልሣ ነበር። እነሆ፡ ፊተኛው ዘሪ ወጣ። ያንን በፊታችሁ ማሳየት እፈልጋለው። መጀመሪያ ምን እንደመጣ፡ ከዚያም ምን እንደሚከተለው ተመልከቱ። ይህ ነጭ ልብስ የለበሰ ሰው ዘር በመዝራት፡ ምድርን ሲዞር፡ እርሱ በኋላም፡ ጥቁር ልብስ የለበሰ ሰው መጣ፡ ሾካካ ይመስል ነበር፡ ከኋላው እየተደበቀ፡ እንክርዳድ ይዘራ ነበር። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፡ ሁለቱም ስብሎች ሲበቅሉ አየሁ። በበቀሉ ጊዜም፡ አንደኛው ስንዴ ሌላኛውም እንክርዳድ ሆኑ።

52 ከዚያም ድርቅ መጣ፡ ያን ጊዜ፡ ሁለቱም ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ዝናብ ለማግኘት፡ የሚለምኑ ይመስሉ ነበር። ከዚያም በምድር ላይ ታላቅ ደመና መጣ፡ ዝናብም ዘነበ። ስንዴው ቀና በማለት እንዲህ አለ፡ “ጌታ ይመስገን! ጌታ ይመስገን!” እንክርዳዶቹም ቀና በማለት እና ጮክ ብለው፡ “ጌታ ይመስገን! ጌታ ይመስገን!” አንድ አይነት ውጤት ነበረ። ሁለቱም ሊጠፉ፡ ሁለቱም እየሞቱ ነበር። ከዚያም ስንዴው ተጠማ። ይህ የሆነው በተመሳሳይ እርሻ፡ በተመሳሳይ የአትክልት ስፍራ፡ በተመሳሳይ ቦታ፡ ከተመሳሳይ አሸንዳ ሥር ስለነበሩ፡ ስንዴም ሆነ እንክርዳድ የሚበቅሉት በተመሳሳይ ምክንያት ነው። አስተውሉ፡ ስንዴውንም እንክርዳዱንም የሚያበቅለው፡ የቅብዓቱ ውኃ ነው።

53 ቤተክርስቲያንቷን የሚቀባው መንፈስ ቅዱስ፡ ነፍሳትን የማዳን ፍላጐትና፡ ተአምራትን የማድረግ ኃይል የሚሰጠው፡ ያው መንፈስ ቅዱስ በጻድቃን ላይ እንደሚወርድ ሁሉ በኃጢአተኞችም ላይ ይወርዳል። ያው መንፈስ! አሁን፡ ማቴዎስ 24፡24ን በሌላ መንገድ መረዳት አትችሉም። እርሱ እንዲህ ብሏል፡ “ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይነሳሉ፡” የተቀቡ፡ ሓሰተኞች። እውነተኛ በሆነ ነገር የተቀቡት፡ ነገር ግን ለዛ ሐሰተኛ ነብያቶች የሆኑ፡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሆኑ።

54 አንድ ሰው እውነት የሆነውን ነገር ሐሰተኛ አስተማሪ እንዲሆን የሚያነሳሳው ምንድን ነው? አሁን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደ አውሬው ምልክት እንሄዳለን፡ ያ የሃይማኖት ተቋም መሆኑን ታያላችሁ። አያችሁ? ሐሰተኛ አስተማሪዎች፥ ሐሰተኛ የተቀቡ። የተቀቡ ክርስቶሶች፡ ግን ሐሰተኛ አስተማሪዎች ናቸው። ይህን ማየት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው።

55 ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ይህንን ጠቅሼዋለሁ። በመላ አገሪቱ በመገናኛው ዝዬ እየተላለፈ ስላለ ደግሜ ልናገረው። አንድ ቀን ከጓደኛዬ ጋር እየተነጋገርን፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከአሪዞና ይመጣል። እና የ—የሆምጣጤ ዛፍ እርሻ ነበረው። በዚያም የወይን ፍሬ፡ ሎሚ፡ መንደሪን፡ እና ታንገሪን የሚያፈራ ብርቱካን ዛፍ ነበረው። እና በአንዷ ዛፍ ላይ ምን ያህል ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎች እንደነበሩ ረስቼዋለሁ። ሰውዬውንም እንዲህ አ—አ—አልኩት፡ “እንዴት ነው? ምን አይነት ዛፍ ነው፡” ብዬ ጠየቅኩት?

እርሱም “ዛፍ ነው፡ የብርቱካን ዛፍ፡ ነው፡” አለኝ።

እኔም፡ “ታዲያ የወይን ፍሬ ላዩ ላይ ምን ይሰራል? ሎሚስ እንዴት በላዩ ላይ ያዘ? ”

“በላዩ ላይ ተዳቅለዋል፡” አለኝ።

56 እኔም፡ “ገባኝ። በደንብ፡ ተረድቻለሁ፡” አልኩትም፡ “አሁን፡ በሚቀጥለው ዓመት ይህ ዛፍ ሌላ ፍሬ ሲያፈራ፡” ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ይበስላሉ፡ ቀጠልኩና እንዲህ አልኩት፡ “ከዚያም ሁሉም ብርቱካን ያፈራሉ። ዋናው ብርቱካናማ ዛፍ ከሆነ፡ ብርቱካናማዎችን ያፈራል፡ አይደል፡ ጌታዬ? አልኩት”

እርሱም “አይደለም፡ ጌታዬ። የተተከለው ቅርንጫፍ ሁሉ የራሱን ዓይነት ፍሬ ያስገኛል፡” አለኝ።

“ይህ የሎሚ ቅርንጫፍ ከዚህ የብርቱካን ዛፍ ላይ የሎሚ ፍሬ ያስገኛል ማለትህ ነው፡” አልኩት?

“አዎን፡ ጌታዬ፡” አለኝ።

“ይህ የወይን ዛፍ ከብርቱካን ዛፍ ላይ የወይን ፍሬ ያፈራልን? ”

እርሱም “አዎን፡ ጌታዬ። የተዳቀለው ቅርንጫፍ ውስጠኛው ተፈጥሮው ይህ ነውና፡” አለኝ።

እኔም “እግዚአብሔር ይመስገን!” አልኩት፡

እርሱም፡ “ምን ማለትህ ነው? ”

እኔም፡ “አንድ ተጨማሪ ጥያቄ አለኝ። አሁን፡ ይህ የብርቱካን ዛፍ እራሱስ ዳግመኛ ብርቱካን ያፈራ ይሆን? ”

57 እርሱም “ሌላ ቅርንጫፍ ካወጣ፡” አለኝ። ሌላ ቅርንጫፍ **ሲያወጣ** እንጂ፡ በላዩ ላይ በተዳቀለው ቅርንጫፍ አይደለም። ሁሉም ግን፡ የሆምጣጤ ፍራፍሬዎች ናቸው፡ ሁሉም በሆምጣጤው ዛፍ ባለው የሆምጣጤ ዛፍ ህይወት ይኖራሉ።

58 እኔም “ይኸውላችሁ! ሜቶዲስቶች፡ በየጊዜው ሜቶዲስቶችን ያፈራሉ፡” አልኩት። ባፕቲስትም፡ ሁል ጊዜ ባፕቲስቶችን ያፈራል። ካቶሊክ፡ ሁል ጊዜ ካቶሊክን ያፈራል። ነገር ግን የሕያው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የሆነ የራሷን የወይን ግንድ የምታበቅል ከሆነ፡ ክርስቶስን ከስር፡ ቃሉንም በየጊዜው ታፈራለች።”

59 አሁን፡ እሱን እዛ ላይ ለማዳቀል መትከል ትችላላችሁ፡ አያችሁ። እያንዳንዱ የወይን ፍሬ፡ ሎሚ፡ መንደሪን፡ ብርቱካን፡ ምንም ዓይነት የሎሚ ፍራፍሬዎች ቢሆኑ፡ እያንዳንዳቸው በዚያ ዛፍ ውስጥ መኖር ይችላሉ፡ ነገር ግን በዛፉ ላይ እየኖሩ፡ ስለ ዛፉ የሐሰት ምስክርነት ይሰጣሉ። አያችሁት? በዚያ ዛፍ ውስጥ ባለው እውነተኛ ሕይወት እየኖሩ እና እየበለጸጉ ነው።

60 አሁን፡ በማቴዎስ 24፡24 ላይ፡ በተመሳሳይ ህይወት እየኖሩ፡ ነገር ግን ከጅምሩ፡ ትክክል አልነበሩም። በዚያ ዛፍ ላይ የሐሰት ምስክርነት ይሰጣሉ! የብርቱካን ዛፍ ነው፡ ሆኖም ግን የሆምጣጤ ዛፍ ነው። እንዲህም ይላሉ፡ “ይህች ቤተክርስቲያን፡ ይቺ የሃይማኖት ተቋም የክርስቶስ ምክር ያላት ናት።” ሐሰተኛ ጥምቀት፡ ሐሰተኛ የቃል ምስክርነት ያላቸው ናቸው፡ የእግዚአብሔር ኃይል ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ነውን ለማለት ይሞክራሉ?

61 ኢየሱስ፡ ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ሰበኩ ዛፉ ለሚያበቅለው… ለቅርንጫፍ ሁሉ፡ በዛፉ ላይ ለሚበቅለው ቅርንጫፍ ሁሉ ሰበኩ። እና ለእውነተኛዎቹ ቅርንጫፎችም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።” እስከ የት? ዛፍ እስከሆነ ድረስ፡ ቅርንጫፎችን እስከሚያወጣ ድረስ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ። “በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ የሚገድል ነገርንም ይጠጣሉ፣ እጃቸውን በታመሙ ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።” የምንኖርበትን ጊዜ ተመልከቱ? ኢየሱስ የተናገረውንም ተመልከቱ?

አስታውሱ፡ ይህ በመጨረሻው ጊዜ ነበር፡ በዌስሊ እና ከዚያ በፊት አልነበረም። አሁን፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ይህ ይፈጸማል።

62 አሁን ቅዱሳን መጻሕፍትን ተመልከቱ፡ ይመስክሩ። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “በእነርሱም፡ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁ፡ ወይም ታምናላችሁና፡ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ ነገር ግን እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ

ናቸው።” በሌላ አነጋገር፡ ይህ ዛፍ ቅርንጫፍ ቢያወጣ… “እኔ የወይኑ ግንድ ነኝ፡ ዛፉ ነኝ፣ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ። በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡” ቅዱስ ዮሐንስ 14፡12።

አሁን፡ “በእኔ የሚኖር፡ እርሱ… ከመጀመሪያው ከሥሬ ውስጥ የነበረ እርሱ ነው።”

63 ኢየሱስ የዳዊት ሥርና ዘር የሆነበት ምክንያት ይህ ነው። እርሱ ከዳዊት በፊት የነበረ፡ በዳዊት ውስጥ፡ ከዳዊት በኋላ፡ የዳዊት ሥርና ዘር፡ የንጋት ኮከብ፡ የሳሮን ጽጌረዳ፡ የቆላ አበባ፡ አልፋና ዖሜጋ፥ አብ፡ ወልድ፡ እና መንፈስ ቅዱስ ነው። “በእርሱ የመለኮት ሙላት በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራል።” የዳዊት ሥር እና ዘር!

64 “በእኔ ውስጥ ያለው፡ የተመረጠው ሕይወት፡ አስቀድሞ የተወሰነው ሕይወት፡” እርሱ ቃል ነው፡ “ከመጀመሪያ ጀምሮ፡ በሚወጣበት ጊዜ፡ ፍሬዬን ያፈራል።” ቅዱስ ዮሐንስ 14፡12።

ነገር ግን ሌሎች እራሳቸውን ክርስቲያን እና አማኝ እያሉ፡ በተመሳሳይ ነገር ይኖራሉ። “‘ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡’ የሚል ሁሉ፡ የሚገባ አይደለም።”

አሁን፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደምናየው፡ “የእግዚአብሔር ምሥጢር በሚፈጸምበት ጊዜ፡” ይህ የሚሆነው እና የሚገለጠው በመጨረሻው ዘመን ነው።

65 እነዚህ ዛፎች፡ እውነተኛው የወይን ግንድ እና ሐሰተኛው የወይን ግንድ! አብረው እንዴት እንዳደጉ እየሰበክኩ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ ሰምታችሁኛል። ከቃየንና አቤል፡ በመሠዊያው ላይ በተገናኙት፡ ሁለት የወይን ግንዶች፡ ሁለቱም በግለሰቦቹ በመምጣት ይታያሉ፥ ሁለቱም ሃይማኖተኞች፡ ሁለቱም የተቀቡ፡ ሁለቱም ሕይወትን የሚሹና፡ አንድ አምላክን የሚያመልኩ መሆናቸውን በግልጽ አሳይቷል። እና አንደኛው ተቀባይነት ያጣ ሲሆን ሌላኛው ተቀባይነት አግኝቷል።

66 እና ተቀባይነትን ያገኘው ሰው ከወንድሙ የተለየ ነገር ሊያደርግ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ፡ ለእርሱ ተገለጦለት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር፡ “በእምነት… ” ዕብራውያን፡ 11ኛ ምዕራፍ፡ “አቤል ከቃየን መሥዋዕት ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፡ እግዚአብሔርም ስለ እርሱ ሲመሰክር ጻድቅ እንደ ሆነ ተናገረ።”

ኢየሱስ፡ ማን እንደነበረ ስለ መንፈሳዊው ማንነት መገለጥ! እንዲህ ብሏል፡ “ሰዎች እኔን የሰውን ልጅ ማን ይሉታል? ”

እሱ እንዲህ አለ፡ ጴጥሮስም፡ “አንተ ክርስቶስ፡ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” አለው።

67 “የዮና ልጅ፡ ስምዖን—ስምዖን ሆይ፣ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና፡ ብፁዕ ነህ። በሰማያት ያለው አባቴ ገለጠልህ። በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡” (በምን? ) በቃሉ እውነተኛው መገለጥ። እውነተኛው የወይን ግንድ እንደገና ይህ ነው። “አቤል፡ በእምነት!”

እናንተም “በመገለጥ አይደለም፡” ብላችኋል።

68 እምነት ምንድን ነው? እምነት ማለት ለግልህ የሚገለጥ ነገር ነው፡ ገና ያልሆነ ነገር፡ ግን እንደሚሆን የምታምነው ነገር። እምነት የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጥ ነው። ስለዚህ፡ በመገለጥ ነው!

69 በዛሬው ጊዜ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ መገለጥ እንኳ የማያምኑ ናቸው። በአንዳንድ ዶግማዊ ስርዓት አስተምህሮ ያምናሉ። "አቤል በመገለጥ ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ፡ እግዚአብሔርም እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ መሰከረለት።" አሜን። እንደምታዩት ተሰፋ አደርጋለው። የት እንደምንኖር አያችሁ? ዘመኑን አያችሁት?

በቅርብ ጊዜ ከ—ከአንድ ክርስቲያን ምሁር ጋር እየተነጋገርኩ ነበር፡ ክርስቲያን ምሁር እና ጨዋ ሰው ነው። እርሱም "አቶ ብራንሃም፡ እኛ ሁሉንም መገለጦችን አንቀበልም፡" አለኝ።

እኔም እንዲህ አልኩት፡ "እንደዛ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስንም መቃወም አለባችሁ፡ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ።" ያንን ማየት ካልቻላችሁ፡ ጠፍታችኋል።

70 ኢየሱስም "እኔ እሱ እንደሆንኩ ባታምኑ፡ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ፡" ብሏል። እርሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው መልክ ተገለጠ። ያንን ማመን አልቻላችሁም፡ እናንተ ጠፍታችኋል። እርሱን ሦስተኛ ሰው፡ ሁለተኛ ሰው፡ ወይም ከእግዚአብሔር ሌላ ማንኛውንም ሰው ነው ብትሉት፡ ጠፍታችኋል። "እኔ እሱ እንደሆንኩ ካላመናችሁ፡ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።" መገለጥ!

71 እርሱን ማየት አለመቻላቸው አይደንቅም። "አብ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡" ከሰሩ፡ "ወደ እኔ ይመጣል።" አያችሁ? ተረዳችሁ? ኦህ፡ እንዴት እናፈቅረው ዘንድ፡ እናወድሰው ዘንድ፡ እና እናመሰግነው ዘንድ ይገባን ይሆን፥ በዘመኑ ፍጻሜ የመንፈስ ፍሬ ደርሶ፡ እና የሙሽራይቱ ዛፍ በዘመኑ እናት ላይ እንዲህ ጎምርቶ አይተናልና!

72 እውነተኛ የወይን ግንድ እና ሐሰተኛ የወይን ግንድ፡ ሁለቱም ተመሳሳይ ቅባት ነበራቸው። ዝናብ በሁለቱም ላይ ይዘንባል። "የሚቻል ቢሆን የተመረጡትንም ያስታል፡" ብሎ እኛን ማስጠንቀቁ አይገርምም።

ልብ በሉ፡ አንድ ዓይነት ይመስላሉ። አንድ ዓይነት ቅባት ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን ልብ በሉ፡ እንዴት አወቃችሁት? "በፍሬያቸው… "

73 ብርቱካን አለመሆኑን እንዴት ታውቃላችሁ? ምክንያቱም ወይን ፍሬ እያፈራ ስለሆነ። ይህ ግንድ መልካም ነው፡ በዛፉ ላይ ይኖራል፡ ነገር ግን የወይን ፍሬ እያፈራ ነው። እንደ መጀመሪያው አይደለም።

74 አንድ ቤተ ክርስቲያን "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ እና፡ ለዘላለም ያው ነው" ብላ የምታምን ከሆነ፡ ኃይሉን፡ ሥራውንና፡ ቃሉን ብትክድ፣ በ—በኢየሱስ ክርስቶስ የ… የምታምን ቤተክርስቲያን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ የምትሠራ ከሆነ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ይኖራታል። ይህ ካልሆነ ግን፡ ምንም እንኳ ሕይወት በውስጧ ቢጎርፍ፡ ከስሯ ጀምሮ፡ አስቀድማ ካልተወሰነች፡ በእያንዳንዱ ወቅት ወይን ፍሬ፡ ወይም የተለየ ነገር ታፈራ ይሆናል። አስቀድሞ የተወሰነ

ሕይወት ከሆነ ግን፡ ከሰሩ፡ ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘለዓለም ያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ያፈራል፡ ይህ የሚሆነው ከሰሩ የሚወጣው ቃል ከሆነ ነው። እሱም፡ የሁሉም ነገር ምንጭ፡ የሁሉም ነገር መጀመሪያ ነው።

75 አስተውሉ፡ ልዩነቱን የሚነግራችሁ የሚያፈሩት ነገር ነው። ኢየሱስም እንዲህ ብሏል፡ "በፍሪያቸው፡" "ታውቋቸዋላችሁ።" አሜከላው በቀጥታ በወይን ግንድ ውስጥ ቢኖርም እንኳ፡ "ሰው ከአሜከላ ዘንድ ወይንን አይሰበስብም።" ይህ ሊሆን ይችል ይሆናል፡ ነገር ግን ፍሬው ይነግረናል።

76 ፍሬው ምንድን ነው? ቃሉ ነው፡ ለዘመኑ-... ለዘመኑ የሚሆን ፍሬ ነው። ትምህርታቸው፡ ይህ ነው። የምን ትምህርት ነው? ስንት ሰዓት እንደሆነ፡ የዘመኑ ትምህርት ነው። የሰው ትምህርት ነውን፡ የሃይማኖት ተቋም ትምህርት ነውን፡ ግን፡ ወይስ፡ ለዘመኑ የሚሆን፡ የእግዚአብሔር ቃል?

77 እንግዲህ፡ ጊዜ ሰጥተን እንዳንታገስ፡ ሰዓቱም እጅግ ይፈጥናል። እየተከታተላችሁ እንደሆናችሁ ግን እርግጠኛ ነኝ፡ እናንተም በመላ አገሪቱ ያላችሁ፡ ምን ለማለት እንደፈለግኩ ማየታችሁ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም እዚህ ላይ ግዜ ለማጥፋት የሚያስችል ጊዜ የለንም።

78 ነገር ግን ቅባቱ በኃጢአተኞች በሐሰተኛ አስተማሪዎች፡ ላይ እንደሚመጣ እና እግዚአብሔር እንዳያደርጉ የነገራቸውን፡ በትክክል እንዲያደርጉ እንደሚያደርጋቸው ማየት ትችላላችሁ፡ ያም ሆነ ይህ ግን፡ ያደርጉታል። ለምን? ምንም ማድረግ አይችሉም፡ እሾህ እሾህ ካልሆነ በቀር ሌላ ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል? ምንም ያህል ጥሩ ዝናብ በእሾህ ላይ ቢዘንብበትም፡ እሾህ እሾህ መሆኑ አይቀሬ ነው። ኢየሱስ "የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ እጅግ ይመሳሰላሉ፡" ያለበት ምክንያት ይህ ነው፡ በሰሩ ውስጥ ያለውን፡ "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፡" ነገር ግን አይቻልም። ስንዴ ስንዴን ከመስጠት በቀር ሌላ መሆን አይችልም፡ መሆን የሚችለው ይህ ብቻ ነው።

79 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር የድርጅት ፈጣሪ አለመሆኑን፡ አስታውሱ። የድርጅት ፈጣሪ ዲያብሎስ ነው። ይህንንም በቃል፡ ደግሜ ደጋግሜ፡ አረጋግጫለሁ፥ ዛሬ ጠዋት ወደዚያ መግባት አያስፈልገኝም። እግዚአብሔር በጭራሽ ሰዎችን አንድ ላይ በማደራጀት፡ ድርጅት እንደማያቋቁም እናውቃለን። የመጀመሪያዋ ድርጅት የመሰረቷት፡ ገና የመጨረሻው ደቀ መዝሙር ከሞተ በመቶዎች ከሚቈጠሩ ዓመታት በኋላ ነው። ሁሌም ውድቅ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ይህ እውነት ካልሆነ፡ ታዲያ በዛሬው ጊዜ በሜቶዲስት፡ በባፕቲስት፡ በፕሬስባይተሪያን፡ በካቶሊክና፡ በሌሎችም መካከል ፍቅር የሌለን ለምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሥራ የማይከተለን፡ ከዚያስ፡ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ነገር፡ በቃል ላይ አንድ ለምን አይሆኑም? ሰውን፡ እና ወንድማማችነትን የሚከፋፍሉት እነዚህ ናቸው... እኛ ስለ ቤተክርስቲያናት እያወራን፡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከእግዚአብሔር ርቀናል።

80 አሁን፡ ይህ ተነግሮናል፡ "የብሉይ ነገሮች በሙሉ ተምሣሌት ይሆኑን ዘንድ፡ ለማስተማር፡ ለመገሠጽ፡ እና ተግሣጽ ይሆኑን ዘንድ ተፈጽመዋል።" በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበሩ ነገሮች ሁሉ የተፈጸሙት፡ ጥላዎች ነበሩ፡ ይህም በዘመናችን፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምን እንደሚሆን ለማየት ነው።

81 ልክ እጃችሁን አይታችሁ የማታውቁ ከሆነ፡ እና ወደ ላይ ስትመለከቱ ግድግዳው ላይ ጥላውን ካያችሁ፡ እጄ ከብርሃን እንደሚንጸባረቅ ሁሉ። (ኔጌቲቩ ሲታይ) ጥላው ውስጥ አምስት ጣቶች ካያችሁ፡ (ፖዘቲቩ ላይ) እጃችሁን ብታንቀሳቅሱ፡ ከ—ከወደ ኔጌቲቩ፡ ባለ አምስት ጣት መታየቱ አይቀርም።

82 ይህም፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፡ "ብሉይ ኪዳን ጥላ መሆኑ ነው፡ የአዳዲሶቹ ነገሮች፡ ወይም ሊመጡ ያላቸው ነገሮች ተምሣሌት ነው፥ እውነተኛው ነገር ሳይሆን፡ ሊመጡ ላላቸው ነገሮች፡ የነገር ጥላ ነው።"

83 ወደ ኋላ ተመልሰን ይህ ነገር በሌላ ዘመን ይኖር እንደነበር እንመልከት። ፊቃደኞች ናችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ይህንን ወደ ፊት እና ወደ ኋላ፡ በቃል፡ ለማረጋገጥ፥ በአንዳንድ ሰው ሃሳብ፡ በአንዳንድ ጽንሰ ሃሳብ እንዳልሆነ፡ እናውቃለን።

84 እኔም ልሁን ሌላ፥ ማንም ይሁን፡ አይገደኝም፡ "በሕጉ እና በነቢያት መሠረት ካልተናገረ፡ በእርሱ ውስጥ ብርሃን የለም።" አያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረው ይህ ነው። "የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ የእኔ እውነት ይሁን፡" የማንም ይሁን የማንም።

አሁን አንድ ምሳሌ ለማሳየት ወደ ኋላ ሄደን፡ እንዲህ ከሆነ እንረዳው።

85 ወደ ኋላ ተመልሰን በዘጸዓት መጽሐፍ ውስጥ፡ ሙሴ ስለተባለ ሰው መናገር እንችላለን፡ እርሱ በዘመኑ ለነበረ ትውልድ ከእግዚአብሔር ቃል እና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር፡ ከእግዚአብሔር ተቀብቶ የተላከ ነብይ የነበረ። የእግዚአብሔር ቃል ሁል ጊዜ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚሄድ፡ "አስቀድሞ ለነቢያቱ እስኪገልጥ ድረስ ምንም አያደርግም፡" ብሏል። ከዚያ በኋላ ስራውን ያደርጋል። ኧሃ-ሃህ።

እንግዲህ፡ እርሱ አይዋሽምና። እየዋሸ አምላክ ሊሆን አይችልም። አይችልም፡ ወዳጄ። በእውነተኛነቱ መጽናት አለበት። በእርሱ ዘንድ ውሸት የለም። እ...

86 ስለዚህ አይለዋውጠውም። ቢለውጠው ግን፡ አምላክ አይደለም፡ ስሕተት ሰርቷል። እርሱ ፍጻሜ የለውም። ፍጻሜ የሌለው አምላክ ስሕተት ሊፈጽም አይችልም። አያችሁ? ስለዚህ እግዚአብሔር አንዴ የተናገረው ነገር፡ ያ ለዘላለም ትክክል ነው። አያችሁ? እናም ይህን ቃል ገብቶናል። ስለዚህ፡ ተከታተሉ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀጣይነት እንዳያገኝ የሚከለክል ምንም ነገር የለም።

87 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩ ለአራት መቶ ዓመት በ—በባዕድ አገር እንግዳ እንደሚሆን፡ ከዚያም በታላቅ እና በብርቱ እጅ እንደሚያወጣው፡ በሚኖሩበት ሕዝብ መካከል ምልክቶቹን እና ድንቆቹን እንደሚያሳይ ቃል ገብቶለት ነበር። የተሰፋው ጊዜም ቀረበ። ሰዎች ግን ረሱት። ፈሪሳውያን እና ሰዱቃውያን፡ እና ሊሎችም፡ የሃይማኖት ተቋሞች ነበሯቸው። ነገር ግን፡ በድንገት፡ እግዚአብሔር በዚያ ብቻውን መጣ እና፡ ከእነዚህ ሁሉ ውጪ፡ አመጣው።

88 እግዚአብሔር በፍጹም፡ በማንኛውም ዘመን ወይም በማንኛውም ጊዜ፡ ከየትኛውም ሃይማኖት ነቢይ ጠርቶ አያውቅም። አይ፡ ወዳጄ። እጅግ ጠማማ ነው፡ እሺ አይልም፡ ከሐይማኖቱ ጋር ቢቀመጥ ይመርጣል።

89 ሙሴ፡ የእግዚአብሔር ቃል ይዞ፡ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ በጥብቅ እየተከተለ፡ እስራኤልን ወደ ተሰፋይቱ ምድር በመውሰድ ጉዞው ላይ ሳለ፡ ሌላ ነቢይ ተገናኘው፡ ይህ የተቀባ ሌላ ሰው በሙሴ ላይ የነበረው ተመሳሳይ እና እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነበረው። ትክክል ነው። ነቢይ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሰው ላይ ነበር። ሰሙም በለዓም ይባላል። ሁላችንም እናውቀዋለን። እና፡ ብዙ ነገሮቹ፡ ተመሳሳይ ናቸው፡ ይህ—ይህ ሰው የተናገራቸው ነገሮች፡ እስከ አሁን ድረስ እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡ ከሁለት ሺ-ሰምንት መቶ አመታት በፊት ነበር። "እስራኤል ሆይ፡ አንተ አንድ ቀንድ እንዳለው ነህ። የሚባርክህ ብሩክ ይሆናል። የሚረግምህ ይረገማል። ያዕቆብ ሆይ፡ ብርታትህና፡ ኃያልነትህ፡ ድንኳኖችህም እንዴት ጽድቅ ናቸው!" እያችሁ፡ ራሱን መርዳት አልቻለም። ወደዚያ የመጣው በልቡ አሰቦ ሰዎችን ለመርገም ነው።

90 ኦህ፡ እናንተ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እነዚህን ቴፖች ለዓመታት ስታዳምጡ፡ እና እግዚአብሔር የተናገረውን በትክክል ሲያረጋግጥ ስታዩ፡ እና በጥናታችሁ ውስጥ ተቀምጣችሁ እውነት መሆኑን ታውቃላችሁ፥ እና በሃይማኖታዊ ተቋም ልዩነቶቻችሁ ምክንያት፡ ትከራከራቸዋላችሁ እናም ለህዝባችሁ እንዲህ አይደሉም ትላላችሁ። ወዮላችሁ! ጊዜያችሁ ቀርቧል።

91 በለዓም፡ በሙሴ ላይ በነበረው መንፈስ ተቀብቷል። ታዲያ ልዩነቱ ምንድን ነው? የሙሴ ትምህርት ፍጹም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በሁለተኛ ጴጥሮስ ላይ፡ እንደተናገረው እስራኤል የተቀበለው "የበለዓም ትምህርት" ነበር፡ እግዚአብሔር በጭራሽ ይቅር አላላቸውም። ይቅርታ የሌለው ኃጢአት! ምንም ከእግዚአብሔር በረከቶች ሥር ቢወጡም እንኳን፡ እንዳቸውም አልዳኑም፡ የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ኃያል ነቢይ ሲንቀሳቀስ ተመልክተዋል፡ በትክክል በእግዚአብሔር እንደተረጋገጠ ተመልክተዋል። ምክንያቱም፡ ከሙሴ ትምህርት ጋር፡ የሚቃረን፡ ሌላ ነብይ መጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ተገዳደረ፡ ሙሴ የተሳሳተ መሆኑን ለሕዝቡ ለማሳየት ሞከረ። ዳታንም፡ ቆሬና፡ ሌሎቹም ከእሱ ጋር ተሰማምተው፡ የእስራኤል ልጆች ዝሙት እንዲፈጽሙ፡ ድርጅቱን እንዲከተሉ፡ "ሁላችንም አንድ ነን፡" ብለው እንዲማሩ አድርገዋል።

"የሜቶዲስት፡ የባፕቲስት፡ የፕሬስባይተሪያን፡ የጴንጤቆስጤ፡ ወይም፡ የሌላ-ሌላም እምነት ተከታዮች ብንሆንም፡ ሁላችን አንድ ነን።"

92 አንድ አይደለንም! እናንተ ለጌታ የተለያችሁ፡ ቅዱስ ህዝብ ናችሁ፡ ለእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ራሳችሁን አሳልፋችሁ ሰጥታችኋል፡ የዚህን ቀን ተሰፋ ፍሬ ለማፍራት። እናንተ ከእነርሱ ወገን አይደላችሁም! ይህ እጅግ እንደሚከብድ አውቃለሁ፡ እውነቱ ግን አሁንም ያ ነው። በዚህ የመጨረሻ ዘመን ለአንድ አገልግሎት የተወሰናችሁ! "ከውስጧ ውጡ።"

93 አሁን፡ የበለዓም ትንቢት ሳይሆን፡ "የበለዓም ትምህርት" ነው። ያ ትክክል ነበር። ያ እግዚአብሔር ነበር። ያንን ሰንቶቻችሁ ታምናላችሁ? [ጉባኤው እንዲህ አለ፡ "አሜን።"—እርታዒ።] የበለዓም ትንቢት በትክክል ልክ ነበር፡

ምክንያቱም ሌላ ምንም ነገር መናገር አልቻለም። የእግዚአብሔር ቅብዓት ሌላ ምንም ነገር አይናገርም ነበር፡ እግዚአብሔርም እውነት መሆኑን በማረጋገጥ አረጋግጧል። ችግሩ ግን "የበለዓም ትምህርት" ነበር።

አሁን ደግሞ ይህን ሃሳብ በማቴዎስ 24:24 ላይ ከሚገኘው ሃሳብ ጋር አነጻጽሩ። የተቀቡቱ፡ ነገር ግን ትምህርታቸው ውሸት ነው። የሥላሴ ትምህርቶች፡ እና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ፥ ስሕተት፡ ፀረ ክርስቶስ ናቸው!

94 ስሜታችሁን እንዳትጎዱ ተሰፋ አደርጋለሁ። እና ያንን አታድርጉ፡ ስልኮቻችሁን መዝጋት። እና ተነስታችሁ አትዉጡ። ዝም ብላችሁ ተረጋግታችሁ ተቀመጡ፡ መንፈስ ቅዱስ ይገልጥልንና ያረጋግጥልን፡ እንደሆነ እንመልከት። እንዲህ ትላላችሁ፡ "ነገር ግን ያ... " የምታምኑበት ነገር ምንም ይሁን ምን፡ ዝም ብላችሁ አዳምጡ። እግዚአብሔር ልባችሁን እንዲከፍትላችሁ ጠይቁ፡ ያኔ እሾህ መሆናችሁን፡ ወይም አሜከላ መሆናችሁን፡ ወይም የት እንደቆማችሁ ትገነዘባላችሁ። አያችሁ?

95 አሁን፡ ደግሞ ይሁዳ እንኳ፡ "ለሚደርስበት ጥፋት አስቀድሞ ተወሰኖለት፡" በኢየሱስ ፊት ቆሞ ነበር። ኢየሱስም፡ "አንተው ነህ። ሂድና፡ የምትሠራውን ሁሉ፡ ቶሎ አድርገው" አለው። እርሱ የሚያደርገውን ነገር በማወቅ፡ ነገር ግን፡ ለእነርሱ ስለ ሠላሳ የብር ሳንቲሞች፡ እና ስለ አንጋፋነት፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሸጠ። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፡ የቤተክርስቲያን ንብረት ያዥ የነበረ፡ ኢየሱስን "ወዳጄ።" ብሎ ጠራው። ስለ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እንደተወለደ ሁሉ እርሱም "የጥፋት ልጅ ሆኖ ተወለደ፡" ይላል። "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ።"

96 በመቀጠልም ሰናጠና በጥንቃቄ ተመልከቱ። ሌላ ምሳሌ እንወስዳለን፡ በነገሥታት መጽሐፍ ውስጥ። ሚክያስ የሚባል አንድ—አንድ ነቢይ ነበረ፡ ስሙ ሚክያስ፡ የኢምላ ልጅ ነበር፡ ነቢይም ነበር። አዎ ነብይ ነበር።

97 ሌላም ነቢይ ነበር፡ እርሱም የነቢያት ድርጅት መሪ ነበር፡ የተቀቡ ሰዎች። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ በልዓም ነበይ ስለመኖሩ እንደሚናገር ሁሉ፡ እነዚህ ሰዎችም የተቀቡ "ነቢያት፡" እንደነበሩ ይናገራል።

ከእነሱም መካከል ሚክያስ የተባለ አንድ ሰው ነበር፡ ሚክያስ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር፡ በእግዚአብሔር የተቀባና በእግዚአብሔር የተላከ ነበር።

98 ከእግዚአብሔር ተልኬአለሁ ብሎ የሚያምን፡ ሴዴቅያስ የተባለ፡ አንድ ሰው ነበረ። በእግዚአብሔር የተቀባ ቢሆንም፡ የሚያስተምረው ነገር ከአምላክ ቃል ጋር የሚጋጭ ነበር። "ሐሰተኛ ክርስቶሶች ይነሳሉ፡ ታላላቅ ምልክቶችን ያደርጋሉ፡ ቢቻልስ የተመረጡትን ለያስቱ ጥረት ያደርጋሉ።"

99 ሁለቱም፡ ሁለቱም ቅቡዓን እንደሆኑ፡ ልብ በሉ። አሁን፡ የትኛው ትክክል፡ የትኛው ስሕተት እንደሆነ እንዴት ማወቅ ትችላላችሁ? ለአክዓብ የተገባለትን ቃል ምን እንደነበረ መርምሩ። ከእሱ በፊት የነበረው፡ ኤልያስ የተባለው ነብይ፡ ከዘመናት ታላላቅ ነቢያት አንዱ፡ የተረጋገጠ ነቢይ ነበር። ይህ የተረጋገጠ ነብይ፡ እንዲህ ብሏል፡ "አክዓብ ይህን ክፉ ድርጊት በመፈጸሙ ምክንያት፡ የናቡቴን ህይወት በመውሰዱ፡ ውሾች ደሙን ይልሳሉ ብሎ ነበር። ኤልዛቤልን ደግሞ ውሾች እንደሚበሏት፡ አ... አካልዋም በሜዳ እንደሚጣል አስቀድሞ ተናግሮ

ነበር።" አሁን፡ እንግዲህ እግዚአብሔር የረገማቸውን እንዴት ትባርካላችሁ? ወይስ እግዚአብሔር የባረካቸውን፡ በለዓም እንዳለው፡ እንዴት ትረግማላችሁ? አያችሁ?

100 እነዚያ ነቢያት ግን ከልባቸው ቅኖች ነበሩ። ጥሩ ሰዎችና የተከበሩ ሰዎች፡ እንደነበሩ ምንም ጥርጥር የለውም። በእስራኤል ዘንድ ነብይ መሆን ማለት፡ የተከበረ ሰው መሆንህ የማይቀር ነው፡ ወይም፡ እስራኤላዊ መሆንህ ግድ ነው። ካልሆንክ፡ በድንጋይ ትወገራለህ። የተከበሩ ሰዎች ነበሩ። ብልህ ሰዎች ነበሩ። የተማሩ ሰዎች ነበሩ። የተመረጡ፡ የአክዓብ ወገን ነበሩ። (አየሽ፡ እህት ራይት? ) የተመረጡ ወገኖች፡ በደንብ የሚሆኑ ናቸው-...

አሁንም፡ ሚክያስ ራዕዩን ሲመለከት፡ ቃሉ ምን እንደሚል በልቡ ያውቅ ነበር፡ በውስጡ የነበረዉ መንፈስ ምን እንደሚል ማየት ግን ፈልጎ ነበር።

101 ስለዚህ፡ እንዲህ አሉት፡ "እነዚህ ሌሎች ነቢያት የሚሉትን ሁሉ አንተም ተናገር። ይህን ካደረግክ፡ ይኸውልህ፡ አንተን፡ ያለጥርጥር፡ እንደገና፡ ወደ ሕብረት እንመልስሃለን። አያችሁ? ከእኛ አንዱ እናደርግሃለን። ወደ ሃይማኖት ተቋማችን እንመልስሃለን። አንተ... አንተ ነቢይ እንደሆንክ እናውቃለን፡ ነገር ግን ሁሌም የመርገም ነገር ትናገራለህ። ሁሌም አክዓብን ትራገማለህ። አሁን፡ ይህ ሴዴቅያስ፡ አለቃ፡ ሊቃነ ጳጳስ፡ ወይም... " ማንም ይሁን። "አሁን እርሱ አክዓብን ባርኮታል፡ እናም እንዲህ አለ፡ "ሂድና ተከናወን" ብሎታል። አንተም እምላ ሆይ፡ ተመሳሳይ ነገር ተናገር። ለምን፡ አንተ ድሃ ሰው ነህ። ምንም ጉባኤ የለህም፡ በጭራሽ፡ ምንም የለህም። እና እነዚህ ሰዎች ሚሊዮኖችን አላቸው። መላ አገሪቱ የነርሱ ናት። አሁን እናንተም እንደ እነሱ ትናገራላችሁ፡ የምታደርገውን አስተውል፡ አንተም—የምድሪቱን ሃብት ትበላለህ።" ከማያዋጣው ሰው ጋር እየተነጋገረ ነው!

እንደዚህ ተብሎ ቢሆንስ፡ "ሴዴቅያስን አንዲት ስሕተት አይተህበት ታውቃለህ፡ ሚክያስ? "

"አይ።"

"ኃጢአት ሲሠራ አግኝተኸው ታውቃለህ? "

"አይ።"

"ሰውን ሲሳደብ ሰምተህ ታውቃለህ? "

"አይ።"

"የሰከረበት ጊዜ አጋጥሞህ ያውቃል? "

"አይ።"

"አልተማረም ብለህ ታስባለህ? "

"አይ።"

"የዶክትሬት ዲግሪው ሐሰተኛ ነው ብለው ታምናለህ? "

"አይ።"

"ፒ—ፒኤ.ችዲው. ችግር እንደሌለው ታምናለህ? "

“አዎን። በሳንሄድሪን ምክር ቤት አማካኝነት፡ ሁሉም ነገር… ከምክር ቤት፡ ሁሉም ነገር ጥሩ ነው ብዬ እገምታለሁ።”

“መልካም፡ ታዲያ፡ ለምን ከእሱ ጋር አትተባበርም? ”

“ከቃሉ ውጭ ስለ ሆነ ነው!”

102 መልካም፡ እንግዲህ፡ ከዚህ በፊት እንደነበረ፡ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ዓይነት ትዕይንት እናሣያለን። እና የእግዚአብሔር ልጅ ከሆናችሁ፡ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ ጋር ትወግናላችሁ። ቃል ነውና። ሰዓቱን፡ ወቅቱን ልብ በሉ።

መልካም፡ ሴዴቅያስ እንዲህ ቢል ኖሮስ፡ “ኦህ፡ ነቢዩ ይህን እንደተናገረ አውቃለሁ፡ ነገር ግን ይህ ለወደፊቱ ትውልድ ነው። ከዛሬ በኋላ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው” ቢልስ?

እርሱ ግን “ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይ እስካይ ድረስ ጠብቁኝ፡ ከዚያም እናገራለሁ፡” አላቸው።

አሉትም፡ “ከዚያስ ተመሳሳይ ነገር ትናገራለህን? ”

እርሱም እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር የሚናገረውን ብቻ እናገራለው፥ ሌላ ነገር፡ ምንም አልጨምርም። አንድም ቃል ልጨምርበት፡ ወይም አንድም ቃል ልቀንስበት አልችልም።”

ስለዚህ በዚያ ምሽት፡ በጸሎት ላይ፡ ጌታ በራእይ ተገለጠለት። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ወጥቶ፡ እንዲህ አለ…

ሁለቱ ነቢያቶች ቀረቡ!

103 በወታደራዊና በብሔራዊ እይታ፡ የአገሪቱ ታላቁ ሰው፡ ሴዴቅያስ ነበር። እርሱ በንጉሡ ዘንድ፡ የበላይ ነብይ ነበር። በድርጅቱ ዘንድ የሌሎች ነቢያት፡ ሁሉ ራስ ነበር። በድርጅቱ አማካኝነት፡ የሁሉም መሪ፡ ሆኖ ተሾመ፥ ምናልባትም በጣም ስላነበበ፡ በጣም ስለተማረ፡ ለሥራው የበለጠ ብቁ የሆነ ይሆናል። “ነቢይ” ተብሎ ስለተጠራም፡ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል። እርግጥ ነው፡ ተራ ነቢይ ሳይሆን፡ ዕብራዊ ነቢይ ነበር። አሁን ተመልከቱት።

104 ሴዴቅያስ ቀረበና “ጌታ እንዲህ አለኝ፡ ለምልክት ይሆኑ ዘንድ፡ ‘እነዚህ ሁለት የብረት ቀንዶችን፡’ ሰራ፡” ብሎኛል አለ። ነቢይ ብዙውን ጊዜ ምልክቶችን ይሰጣልና። “እንዲህ አለ፡ ‘እነዚህን የብረት ቀንዶችን’ ሰራ። የባረከኝ ያንን ቅባት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ‘እነዚህን ውሰድ’ አለኝ።” አንድ ነጥብ ላይ ለመድረስ እንጂ፡ እንደ መሰዋዕትነት አድርገው ለመቁጠር አይደለም። “ያ በእኔ በኩል በልሳኖች የሚናገር፡ ሰለ እኔም የመሰከረው ቅዱሱ መንፈስ፡ እንዲህ አለ፡ ‘እነዚህን ቀንዶች ውሰድ፡ እና፡ ለንጉሡ ንገረው፡ ሶሪያን ከሀገሪቱ በዚህ ታባርራቸዋለህ በለው። እኔም ለእስራኤል፡ ማለት ለቤተ ክርስቲያን የተገባውን ምድር አሳልፌ እሰጠዋለሁ።”’

105 ወንድሜ፡ ይህ በጣም መሰረታዊ ነገር ነው፡ እዚህ ጋርም ልክ እንደ በለዓም ነበር። በለዓም በመሠረታዊነት እንደ ሙሴ ተናግሯል። ሙሴ… ሰባት የእግዚአብሔር ትክክለኛው ቁጥር ነው። በለዓምም፡ “ሰባት መሠዊያዎች ሠርተህ፡ ንጹሕ መሥዋዕት፡ ሰባት በሬዎችና፡ ሰባት አውራ በጎች አቅርብልኝ” አለው። ይህ የእግዚአብሔር ልጅ መምጣት መናገር ነው። በመሠረታዊነት፡ ልክ እንደ እነርሱ ትክክል ነበር።

106 እናም ይህ ሴዴቅያስ፡ በመሠረታዊነት ትክክል ነው፡ “ይህች ምድር የእኛ ናት። ለምን፡ በዚያ የሚኖሩ እነዚህ ሶርያውያንና ፍልስጥኤማውያን፡ የልጆቻቸው እና፡ የጠላቶቻችን ሆድ ሁሉ፡ እየሞሉ ይገኛሉና፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ይህችን ምድር ለእኛ ሰጥቶ ሳለ! ልጆቻችን በማያገኙት ምግብ ጠገቡ!”

107 ወንድሜ፡ ይህ ደንበኛ ሙግት ነው። ይህንንም በእስራኤል ፊት ጮክ ብሎ መናገር እንደሚችል እገምታለሁ፡ እነሱም የቻሉትን ያህል ጮክ ብለው መናገር ይችላሉ። አሁን፡ ስለዚህ ዘመን እያወራሁ ነው። እየተከተላችሁኝ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ጩኸት ሁሉ፡ መንጫጫት ሁሉ!

108 ባለፈው እሁድ ዳዊትን ታስታውሳላችሁ? አያችሁ? እናንተ በሬዲዮ ውስጥ ያላችሁ፡ ወይም በዚህ በቴለፎን መገናኛው-አውታር ውስጥ ያላችሁ፥ የትናንቱን እሁድ መልዕክት ያልሰማችሁ፡ መልዕክቱን በደንብ ስሙት። **ሳይሾሙ እግዚአብሔርን ለማገልገል መሞከር፡** የቱንም ያህል ቅን፡ መልካም ይሁን፡ በፍጹም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። አያችሁ?

አሁን፡ ሴዴቅያስ፡ ትክክል ነኝ ብሎ እያሰበ ነበር።

ሚክያስም “እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ፡” አለ። ስለዚህ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እያለ መጣ። ራእዩን በቃል አረጋገጠ።

አሁን ሴዴቅያስን እንዲህ ቢለው ኖሮ፡ “የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ በዚህ ሰው ላይ የሚደርሰው ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ ቢለውስ? ”

109 “ነገር ግን በዚህ ጊዜ አይደለም፡ ምክንያቱም ይህ ሰው የተከበረ ሰው ነው። እየሞከረ ነው።” ይህንን ለመረዳት እንዲያቅታችሁ። “የቤተክርስቲያን የሆነውን ለቤተክርስቲያን መልሶ ለመስጠት እየሞከረ ነው። ኀብረቷን ለመመለስ እየሞከረ ነው፡” መንፈሳዊ ነገሮች አይደሉም፡ ቢሆኑ ኖሮ፡ መላ አገሪቱን እንደ ኤልያስ ያናውጣቸው ነበር። ነገር ግን፡ ቁሳዊ ነገሮችን ሊሰጣቸው እየሞከረ ነው፡ “ኅብረት አለን። ትልቅ ድርጅት ነን። የእሷ ነኝ። ሁላችንም፡ ሰዎች ሁላችሁ፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሆናችሁ፡ ከእኛ ጋር ማበር አለባችሁ።” ኧሃ-ሃህ።

110 በጥቂቱ ወደዚያ እየመጣን ነው። “ለማንኛውም፡ ሁላችንም ወንድም እና እህቶች ነን።” አይደለም! እውነተኛና እውነተኛ በሆነው የአምላክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈጽሞ እንዲህ አልነበረም፡ ወደፊትም አይኖርም። ሊሆን አይችልም!

111 እስተውሉ፡ ራእዩን አየ። እናም እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር ተናገረኝ።” አሁን፡ ተመልከቱ፡ ሰውየው ቅን ነበር። እርሱም፡ “እንዲህ አለ፡ ‘እነዚህን ቀንዶች ሠርተህ፡ በንጉሡ ፊት ወደዚያ ውጣና ወደ ምዕራብም ግፋ፡’” ወይም ከቆሙበት ቦታ እንጻር መሬት የተቀመጠበት መንገድ ምንም ይሁን ምን። “‘ግፋ፡ እንዲህም ይሆናል፡ በድል ያሸንፋል ተመልሶ ይመጣል፡ ለቤተክርስቲያን ድል ያመጣላታል ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር።’ ይጠራርጋቸዋል!” በጣም ይቀራረባል፡ አይደል? ልዩነቱ ምን ነበር?

እነሆ ሚክያስም መጣ። “አሁን ትንቢትህን ተናገር፡” አለው።

“ሂድ! ነገር ግን እስራኤልን፡ እረኛ እንደሌላቸው በጐች፡ ተበትነው አየኋቸው።” ዋው! በትክክል በተቃራኒው።

112 አሁን፡ እንግዲህ ጉባኤው እናንተ ናችሁ። እስኪ የትኛው ነው ትክክል? ሁለቱም፡ ነቢያት ናቸው። ልዩነታቸውን ማወቅ የምትችሉበት፡ ብቸኛው መንገድ፡ ቃሉን በመመርመር ነው።

“ይህን ከወዴት አገኘኸው፡” አለው?

እርሱም “እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት፡” አለ። “የሰማይ ሰራዊት በዙርያው አየኋቸው፡” አለ።

113 አሁን አስታውሱ፡ ሴዴቅያስም፡ በተመሳሳይ መንፈስ እግዚአብሔርን እንዳየ፡ ተናግሯል። “እግዚአብሔርን አየሁት። እነዚህን ቀንዶች ከ—ከብረት እንድሠራ ነገረኝ። ውጣና አሕዛብን ከዚህ አስወግዳቸው፡ ይህ ርስታችን ነውና። እነዚያ በዚህ ውስጥ ምንም መብት የላቸውም።” በእግዚአብሔር ዘንድ ጸንተው ቢሆኑ ኖሮ ይወርሷት ነበር። ያስመልሷትም ነበር፡ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ራቁ።

114 ድርጅት፡ ማለትም ቤተክርስቲያን እንዲህ ነው። ለእነዚህ ነገሮች መብት ነበራት፡ እናንተ ግን በዚያ ተታለላችሁ፡ ምክንያቱ የወቅቱን ቃል ከሚያረጋግጥ፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ተታልላችሁ ርቃችኋል። ይህ መልዕክት መረዳት እንዲያቅታችሁ።

115 አሁን የተከሰተውን ነገር ልብ በሉ። ሚክያስም፡ “እግዚአብሔርን አየሁት፡” እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔርን በሰማይ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት። የሰማይ ሰራዊት በዙሪያው ተሰብስቦ ነበር። እርሱም እንዲህ አለ፡ ‘ይህ የተረጋገጠለት የራሴ ነብይ ኤልያስ፡ የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም፡ አክዓብን ለማታለል ማን ይሄድልናል። እኔ እሱ እንደሚመጣ ተናግሬአለሁ። ኤልያስም ቃሌን ተቀብሏል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አይጠፋም። ምን ያህል ዘመናዊ ቢሆኑ፡ ወይም ምን ያህል ጥሩ ቢሆኑ፡ ወይም ምን ያህል ቢማሩ፡ ወይም ምን ያህል ትልቅ ቢሆኑ ግድ አይሰጠኝም፡ ቃሌ መቼም አይወድቅም።’

116 “እናም አንድ ውሸታም መንፈስ ከሲኦል ወጥቶ፡ ተንበርክኮ፡ እንዲህም አለ፡ ‘ከፈቀድክልኝ፡ ቅባቴን ሰጥቼአቸው፡ ከቃሉ ብቻ ገለል ላድርጋቸውና፡ የቱንም አይነት ምልክት እና ድንቅ ላሰደርጋቸው እችላለሁ። እንዲያውም ይህ ቃልህ መሆኑን እንኳን አያውቅም። ስለ አንጋፋነት ሲል፡ ችላ ይለዋል።’” ወንድሜ፡ ዘመኑ አልተለወጠም። ወንድም ኔቪል፡ ያ እውነት ነው። ትዝ ይልሃል፡ ያ እውነት ነው። “‘እነሆ ወደ እሱ እወርዳለሁ፡ ሌሎቹ የሚያደርጉትን ሁሉ እንዲያደርግ አደርገዋለሁ። ትንቢት እንዲናገርና፡ ውሸት እንዲናገር አደርገዋለሁ።’” እንዴት ውሸት ሊሆን ይችላል? ከቃሉ ጋር በመቃረን።

117 እነዚህ የሐሰት ጥምቀቶች ብትሉ፡ የሐሰት **ይህ-እና-ይህ-እና-ይህ** ብትሉም፡ ምንም ያህል እውነት ቢመስልም፡ ምንም ያህል ለመምሰል ቢሞክሩም፡ በዚህ ሰዓት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ከሆነ ውሸት ነው። ያ ትክክል ነው።

እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንደው፡ እኛ፡ እንግዲህ፡ **ይህን** አደረግን፡ እኛም **ይህን** እናደርጋለን፡ ቤተ ክርስቲያናችን **በዚህ** መንገድ እና **በዚያ** መንገድ ነው።”

118 ምንም ይሁን ግድ አይሰጠኝም። በዚህ ሰዓት ከተጻፈው ቃል ጋር የሚቃረን ከሆነ፡ ውሸት ነው። ምንም ያህል ቅን ምንም ያህል የተማረ፡ ምንም ያህል ብልህ፡ ምንም ያህል እውነት ቢመስልም፡ ምንም ያህል ምክንያታዊ ቢመስልም፡ ከዚህ ዘመን ቃል ጋር፡ የሚቃረን ከሆነ፡ እግዚአብሔር ከዚህ ጋር ምንም ነገር አይኖረውም። ጊዜ ቢፈቅድልን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በጥልቀት ወደዚያ እንገባለን። ካልተሳካልን፡ ማታ ላይ እንደገና እንቀጥላለን።

119 አሰተውሉ፡ ቅን፡ ጥሩ ሰው፡ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም። እርሱም አለ... ከዚያም፡ ሚክያስ በቀጥታ ሳይሆን፡ በሌላ አነጋገር፡ በእጁ ዙር፡ “በሐሰተኛ መንፈስ ተቀብተሃል፡” አለው። ይህ ለጳጳስ የሚነገር ነገር አይሆንም? እሱ ግን አደረገው።

120 እናም ይህ ጳጳስ ወደ እሱ ቀርቦ፡ “ከእንግዲህ ወዲህ ኅብረት አይኖርህም አለው፡” እና ፊቱን መታ። እንዲ አለ፡ “እኔ የተከበርኩ ሰው እንደሆንኩ ታውቃላችሁ። ቤተክርስቲያኔ የዚህ ነገር መሪ አድርጋኛለች። የእግዚአብሔር ህዝቦች የሕዝብ ድምፅ ነው ይህን ያደረገኝ። ድርጅቴ ነው ይህን ያደረገኝ። የኔ ድርጅት እንደዚህ አድርጎኛል። እግዚአብሔርም ይህንን መሬት ሰጥቶናል፡ ለእኛም እንዲሆን ይፈልጋል። በእኔም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል አለ።” መታው፡ እና እንዲህ አለ፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ ዘንድ በየት በኩል አልፎ? ”

121 ሚክያስ እንዲህ አለ፡ “አንድ ቀን፡ ትረዳዋለህ፡” ካሊፎርኒያ በውቅያኖስ ሥር፡ እና እነዚህን ሁሉ ነገሮች በሆኑ ጊዜ። አያችሁ? “በጥልቅ እሰር ውስጥ በገባህ ጊዜ፡ ያኔ በምን በኩል እንዳለፈህ ታያለህ።”

122 አሁንስ፡ አክዓብ ሆይ፡ ምን ትላለህ? “ነቢዬን እምናለሁ” አለ። ቃሉን ብቻ ቢመረምርስ ኖሮ? አያችሁ፡ ራሱን የተረገመ ሆኖ ማየት አልፈለገም። ሰሙኝ! ራሱን የተረገመ ሆኖ ማየት አልፈለገም። ማንም ሰው አይፈልግም።

123 እና የድ-... የድርጅት ወንድም ሆይ፡ ችግርህ ያ ነው። በልባችሁ እያወቃችሁ፡ ትክክል እንደሆናችሁ፡ ማሰብ ትፈልጋላችሁ፡ በ “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡” የሚለውን ስም በመጠቀም ስታጠምቁ ውሸታም እንደሆናችሁ እያወቃችሁ። እናንተ እየሰራችሁ ያላችሁን እነዚህን ነገሮች-... ታውቃላችሁ፡ የመጀመሪያ ማሰረጃዎችን፡ እና እንደዚህ ያሉ ነገሮች ሁሉ ትጠቀማላችሁ፡ በዚህም ትስታላችሁ። የመጀመርያው ማሰረጃ በልሳኖች መናገር እንዴት ይሆናል፡ ከዚያም በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጋር የሚቃረን ነገር ትናገራላችሁን? ይህ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? መረገምን አትፈልጉትም፡ ትፈልጋላችሁ'ዴ? ነገር ግን **እዚህ** ላይ ተጽፏልና፡ ስለዚህ ይሆንባችኋል። ይህ የአውሬው ምልክት ነው፡ የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስት ድረስ እጅግ ተመሳሳይ ይሆናል።

124 እያንዳንዱ ምልክት፡ እያንዳንዱ ድንቅ፡ የተቀባው ሰው፡ ትንቢቱ፡ የሚፈፀሙ ነገሮች ሁሉ፡ ምልክቶች ሁሉ፡ ድንቆች ሁሉ፡ ልዩነቱን እንዴት ታውቁታላችሁ? የዘመኑን ቃል ተመልከቱት። ማወቂያው መንገድ በዛ ነው...

ሙሴን ተመልከቱ፡ በለዓምን እንዴት ሊነግረው እንደሚችል ተመልከቱ። ሚክያስን ተመልከቱ፡ ትክክል መሆኑን እንዴት እናውቃለን? ከአክዓብ በፊት በነበረው፡ ቃል፡ ይህ ትንቢት አስቀድሞ ተነግሮ ነበር።

125 ቃሉ ራሱ፡ በእነዚህን ድርጅቶችና፡ በእነርሱ ላይ የሚወርደውን እርግማን፡ አስቀድሞ በፊታችን ተንብዮአል። እናም በእውነት በተቀባችው ቤተክርስቲያኑ የሚከናወኑ ነገሮች፡ ቃሉ፡ የቃሉ ሙሽራ ይኖራቸዋል። ይኸውላችሁ እንግዲህ። ይኸው፡ ዛሬም፡ እንደ ድሮው ነው።

126 መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በሁለት ወይም በሦስት አፍ ምስክር ነገር ሁሉ ይጸናል" ይላል። ስለ በለዓም፡ ስለ በለዓምና ስለ ሙሴ ተናገርኩ። አሁን ደግሞ ስለ ሚክያስና ስለ ሴዴቅያስ ተናገርኩ። አሁን አንድ ተጨማሪ እሰጣችኋለሁ። እነርሱም፡ በመቶዎች የሚቈጠሩ ናቸው፡ ነገር ግን ሦስት ምስክሮች ለማድረግ፡ አንድ ተጨማሪ እሰጣችኋለው። እዚህ ላይ የፃፍኳቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡ ግን ጊዜን ለመቆጠብ ነው።

127 ኤርምያስ የተረጋገጠ፡ የተገለለ፡ ሆኖም የተረጋገጠ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር። ሰዎችም ይጠሉት ነበር። በሰለው የበሰበሱ-... ፍራፍሬዎችና፡ ሌሎች ነገሮችን ይወረውሩበት ጀመሩ። እርሱም ረገማቸው። እና እርሱ ያደረጋቸው ነገሮች፡ እና በጎኖቹ ላይ ወድቆ፡ ወዘተ፡ እስራኤል መሳታቸውን ምልክቶችን ሰጠ።

128 በዛሬው ጊዜ በዓለም ላይ የተነሡ፡ እውነተኛ ነቢያት ሁሉ፡ እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን ይረግማሉ። እንዴት ሊለወጥ ይችላል፡ በማይለወጠው አምላክ?

129 መንፈስ ቅዱስ የዚህ ዘመን ነቢይ ነው፡ ቃሉን ያረጋግጣል፡ እውነት መሆኑን ያሳያል። መንፈስ ቅዱስ የሙሴ ዘመን ነቢይ ነበር። መንፈስ ቅዱስ የሚክያስ ዘመን ነቢይ ነበር። ቃሉን የጻፈው መንፈስ ቅዱስ፡ መጥቶ ቃሉን፡ ያረጋግጣል።

በሚክያስ ዘመን የሆነው ምንድነው? በአምላክ ቃል መሠረት፡ አክዓብ ተገደለ፡ ውሾችም ደሙን ላሱት።

130 እናንተ የሐሰት አስተማሪዎች ሆይ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ አንድ ቀን የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ፡ እናንተ ዕውሮች የዕውሮች መሪዎች! እየተቆጣሁ አይደለሁም። እውነትን ብቻ እነግራችኋለሁ። እኔም መንፈስ ቅዱስ እዚህ ላይ፡ እዚህ ቤት ውስጥ፡ "በዚህ መንገድ ተናገር፡" ባይለኝ ኖሮ ይህንን አልናገርም ነበር። አምላክ ትክክል መሆኑን ካረጋገጠው በቐር የተሳሳተ ነገር ተናግሬ አውቃለሁን? ወንድሞቼ ሆይ፡ እጅግ ሳይረፍድባችሁ፡ ንቁ!

131 ነገር ግን ይህንን ልንገራችሁ። እሾህ እንዲሁ እንዲሆን አስቀድሞ ተወስኖ ሳለ፡ ዛሬ ተነስቼ አሜኬላ ልሁን እንዴት ይላል? የተመረጡትስ ይህን አለማየት እንዴት ይችላሉ? ምክንያቱ፡ እናንተ ይህን ለማየት የተመረጣችሁ ናችሁ። "አባቴ የሰጠኝ ሁሉ ይመጣል፡" አለ ኢየሱስ፡ "ነገር ግን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ ለእኔ የሰጣቸው ስማቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ፡ ከተጻፉት በስተቀር ማንም ሊመጣ አይችልም፡" በቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቄስ መዝገብ ሳይሆን፡ በመጽሐፉ፡ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ነው።

አስተውሉ፡ ኤርምያስ በሕዝቡ ፊት፡ የተረጋገጠ ምስክር ሆኖ ቆመ፡ ሕዝቡ ግን ጠሉት።

132 እነሱም ወጥተው ቀንበር ሠሩ፡ እርሱም እንዲሁ፡ አንገቱ ላይ ጠምዶ፡ በሕዝቡም ፊት ሄደ። እነርሱም እንዲህ አሉ፡ "ኑህ፡ እኛ ታላቅ የእግዚአብሔር

ሕዝብ ነን። እኛ’ኮ፡ እስራኤል ነን። በምኩራባችን ውስጥ በጣም ቅን ነን! በየሳምንቱ እሁድ በስብሰባው ላይ እንገኛለን፡ እኛ፡ መሥዋዕት እናቀርባለን፡ ገንዘባችንንም እንከፍላለን። ናቡከደነፆር የእግዚአብሔርን ቅዱስ ነዋያት እንዴት ሊማርክ ይችላል? ” ኧሃ! ኃጢአታችሁ ይህንን አደረገ።

133 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “ትእዛዜን ብትጠብቁ፡ ይህን አላደርግም። ካልጠበቃችሁ፡ ግን፡ ወደ እናንተ ይመጣባችኋል።” ያ በትክክል እውነት ነው። አሁንም ተመሳሳይ ነው። ትእዛዛቱን ጠብቁ፡ እርሱ ለገባው ለዘመኑ ቃል፡ ቃል ኪዳኑን ጠብቁ።

134 አሁን አስተውሉ። አሁን፡ ኤርሚያስ፡ ቢጠሉትም እንኳ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ የተረጋገጠ ነብይ ነበር... እያንዳንዳቸው በየዘመናቸው የተጠሉ ነበር። በወቅቱ ከነበረው ከሃይማኖት ተቋም አሠራር ጋር የሚቃረኑ በጣም እንግዳ የሆኑ ነገሮችን አድርገዋል፡ ሁሉም ሰው፡ ነገሥታትም ሆኑ ሌሎች ሰዎች እንኳ ይጠሉት ነበር። ስለዚህ አንገቱ ላይ ቀንበር—አስቀመጠና፡ እንዲህ አለ፡ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ በዚያም ለሰባ ዓመታት ይቀመጣሉ አለ፡” ከአምላክ ቃል የተረዳው ነገር ነበረውና። “ሰባ ዓመት!”

135 ከዚያም ሐናንያ፡ ሐናንያ፡ አጻጻፉም፡ H-a-n-a-n-i-a-h ይመስለኛል። በሕዝቡ መካከል ነቢይ የነበረው፡ ሐናንያ፡ መጣና፡ ከኤርምያስ አንገት ላይ የነበረ ቀንበር፡ አውልቆ ሰበረው። እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል የሚፃረር ነገር ሲናገር፡ በሕዝቡ ፊት አትቅለል፡ አለው። እርሱም “በሁለት ዓመት ውስጥ ተመልሰው ይመጣሉ። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡” አለ።

ሁለት የተቀቡ ነቢያት። ልዩነታቸው ምን ነበረ? አንደኛው ቃሉን ተናገረ፡ ሌላኛው ግን አልተናገረም። ኤርምያስም “አሜን፡” አለ።

136 ከሽማግሌዎችና ከጉባኤው፡ እንዲሁም ከእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፊት፡ እያችሁ፡ እንደ ኤርምያስ ታላቅ መሆን እንደሚችል ለማሳየት ፈለገ። “ምንም ብሆን፡ አንተን እንደማይወዱህ ታውቀዋለህ። ስለዚህ እኔም፡ ነቢይ ነኝ። ከአንተ የበለጠ ነቢይ ነኝ፡ ምክንያቱም አንተ የምትተነብየው ውሸት ነው። የእግዚአብሔር ህዝቦች **በዚህ-እና-በዚያ** ዓይነት ሁኔታ ሥር ይሆናሉ ብለህ ትነግረኛለህን? ”

137 ዛሬም ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ እናንተም ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን፡ እንዲሁ በዚያ ትገኛላችሁ። በመርገም ትረገማላችሁ። እናንተ አብያተ ክርስቲያናት፡ የእግዚአብሔርን ቃል ከመከተል ይልቅ የሰውን ወግ የምትከተሉ የሃማኖት ተቋሞች፡ በእግዚአብሔር የተረገማችሁ ናችሁ።

138 አሁን ልብ በሉ፡ እነሆ እርሱ መጣና። ሐናንያ ቀንበሩን ከአንገቱ ላይ ወረወረው፡ የእግዚአብሔር ምልክት፡ ሰበረና፡ እንዲህ አለ፡ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ከሁለት ዓመት በኋላ ተመልሰው ይመጣሉ።” ለታይታ ብቻ ነው፡ “እኔ **እከሌ-እና-እከሌ ነኝ**።” የድርጅት ነቢይ ነበርና፡ ተቃወመ።

ኤርምያስም ብቻውን የሚኖር የበረሀ ሰው ነበር። እነርሱ ክፉዎች ስለነበሩ፡ ሁልጊዜ በእነሱ ላይ ክፉ ትንቢት ይናገርባቸው ነበር።

139 እናም ይህ ሰው እየነገራቸው የነበረው፡ “ኦህ፡ እናንተ አባላት እስከሆናችሁ ድረስ ሁሉም ነገር ደኅና ነው። እስራኤል እስከሆናችሁ ድረስ፡ ሌላ ነገር አያስፈልግም። አያችሁ፡ እናንተ፡ እ... እግዚአብሔር ይህን አያደርግም። እዚህ የተፈጠረ ትንሽ ነገር እንደሆነ አውቃለሁ፡ ነገር ግን አትደናገጡ፡ አትፍሩ።”

140 ወንድሜ፡ ሆይ፡ ዛሬም አሉ። “አትጨነቁ፡ ሁሉም ነገር ደኅና ነው። እኛ ሁሉንም ነገር በቍጥጥር ሥር አድርገናል። እኛ ቤተክርስቲያን ነን።” ምንም አታስቡም። አዎን።

141 ስለዚህ እንዲህ አለ፡ “ሁሉም ነገር ደኅና ይሆናል። በሁለት ዓመት ውስጥ ተመልሰው ይመጣሉ። የሆነው ነገር ኢምንት ነገር ነው። እንግዳ ነገር አይደለም። የተለመደ ነገር ነው። ናቡከደነፆር ወደዚህ ቢመጣም፡ አምላካችን ግን ይህን ሁሉ ይቆጣጠራል።”

142 ቃሉ ግን ያ ትውልድ እስኪጠፋና ሌላ ትውልድ፥ እስኪመጣ ድረስ፡ በዚያ ሰባ ዓመት ይቆያሉ ይላል። አንድ ትውልድ አርባ ዓመት ነው። “ይህ ማለት ለሁለት ትውልዶች ገደማ ነው ማለት ይቻላል።” ኤርምያስም እንደ እግዚአብሔር ቃል ተናገረ።

ሐናንያም ያንን ሰበረ! ኤርምያስ እንዲህ አለ፡ “ይሁንልን። አሜን። ይሁን እንጂ፡ ሐናንያ ሆይ፡ ሁለታችንም፡ ነቢያት መሆናችንን እናስታውስ። እኛ አገልጋዮች ነን።”

143 እናም ወንድሞቼ፡ ይህን እላችኋለሁ። ከኛ በፊት የነበሩ ነቢያቶች መኖራቸውን እናስብ፡ እነሱም መንግሥታት ላይ ትንቢት ተናግረዋል፡ እናም በተወሰኑ ነገሮች ላይ ትንቢት ተናግረዋል። ይሁን እንጂ፡ ነቢዩ የተናገረው ነገር ሁሉ፡ ከቃሉ ጋር የሚስማማ መሆን እንዳለበት፡ አስታውሱ። እንደነ ሚክያስ፡ እና ሙሴ፡ እና እንደ ሌሎቹ። ቃሉ እንደሚለው መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ፡ ምን እንደሆነ አስቡ።

144 ከዚያም፡ ሐናንያ፡ የጽድቅ ቁጣው ተነሳ። “እኔ ሐናንያ ነኝ” (ጥያቄ የለውም)፡ “የእግዚአብሔር ነቢይ ነኝ፡ እኔም ‘ሁለት ዓመት ነው፡’ ብያለሁ።” በሌላ አነጋገር፡ “ቃሉ ምን እንደሚል ግድ የለኝም።” ቅባቱ፡ “‘ከሁለት ዓመት በኋላ፡ ተመልሰው ይመጣሉ፡’ ብያለሁ።”

145 ኤርምያስ ከፊቱ፡ ወጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ እርሱ ምንም ቢል አይገደኝም፡ አሁንም አምናለሁ ቃሉም እንዲህ እንደሚል አውቃለሁ። ለአንተ እታመናለሁ። በእርሱ አልታለልም።”

146 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፡ “ሂድና ለሐናንያ ንገረው፡ ‘ቀጣዩን ቀንበር ከብረት አደርገዋለሁ፡’ በለው።” ሐናንያ፡ ይህን በማድረጉ ምክንያት፡ በዚያው ኦኣመት፡ ከምድረ ገጽ ተወገደ።

ሁለቱም ነቢያት፡ ተምሣሌታችን ናቸው። በዚህ ጊዜ ብዙ ተጨማሪ ሊነገሩና ሊባሉ ይችላሉ።

147 ግን ተመልከቱ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ሁለቱ መናፍስት፡ እንደገና፡ አንድ ላይ እንደሚሆኑ ተናግሯል። ልክ ነው? [ጉባኤው እንዲህ “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] አሁን ልብ በሉ። ከፊተኛው ይልቅ የቀረበ ይሆናል። ይህ የመጨረሻ ጊዜ ነው። ኦህ፡ ልጆቼ ሆይ! እግዚአብሔር ምህረቱን

ያድርግልን! እስካሁን፡ “ቢቻልስ የተመረጡትን ለማታለል እስከሚችል ድረስ እጅግ እውን ሊመስልም ይችላል።” አሁን እንዴት ትሄዳለህ... በእነዚያ ቀናት ምንና ምን አልን? ዛሬስ ምንና ምን ትላላችሁ? ዛሬም ያው ነው፡ ከቃሉ ጋር ጽንታችሁ ቁሙ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ዘላለም ያው ነው።”

148 አሁን ስለ መልዕክቱ ሁሉ ተጠንቀቁ። እና ይህን ቴፕ ስትሰሙ፡ ምናልባትም አንድ ቀን ጌታ ከእኔ ጋር በምድር ላይ ሲጨርስ እኔ አልኖርም ይሆናል፡ መለስ ብላችሁ ይህን አስቡት። እየነገርኳችሁ ያለውን፡ ድምጼን ስሙት። ከመምጣቱ በፊት የሚወስደኝ ከሆነ፡ ይህን አስቡ፡ በጌታ ስም፡ በጌታ ቃል ነግሬአችኋለሁ። አዎን።

149 ልብ በሉ፡ “ቢቻላቸውስ የተመረጡትን የሚያታልሉ ከሆነ እጅግ ይቀራረባሉ፡” እንደ ነብያት ዓይነት ምልክቶችን፡ አንድ ዓይነት ተአምራቶችን፡ በአንድ መንፈስ ያደርጋሉ። ልክ ነው? [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—እርታዒ።] ልክ እንደ ነብያት እንዳወራናቸው፡ ነቢያት። አሁን፡ እንዲህም ደግሞ ተጽፏል...

ከፈለጋችሁ፡ ይሄን ለማየት፡ ሁለተኛው ጢሞቴዎስ 3፡ እንክፈት። እስኪ ከዚህ እንውታ። መውጣት አልፈልግም...

150 ሰዓቱን እያየሁት ነው፡ እና—ብዙዎቹን መተው እፈልጋለሁ፡ ግን አሁን ማድረግ ያለብን አይመስለኝም። አያችሁ? እስተውሉ። ብቻ... እዚህ ቆሜ፡ እያላበኝ ነው፡ አያችሁ፡ ይሁን እንጂ ደስተኛ ነኝ። ይህም እውነት መሆኑን አውቃለሁ። ሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3፡8።

151 ጳውሎስ፡ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፡ “መልአክ ከሰማይ መጥቶ እኔ ካልኩት በቀር ሌላ ቃል ቢነግራችሁ፡ የተረገመ ይሁን፡” እንግዲህ፡ መልአክ ወርዶ። ሁለተኛ ተሰሎንቄ ነው... ኦህ፡ ይቅርታ።

152 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡8ን ተመልከቱት። ጳውሎስ ሲናገር ተመልከቱ። እስቲ ከመጀመሪያው ጥቅስ... እንጀምር እና፡ አሁን በጥሞና አዳምጡ። መጽሐፍ ቅዱስ ያላችሁ፡ አብራችሁኝ አንብቡ። መጽሐፍ ቅዱስ የሌላችሁ፡ ደግሞ በጥሞና አዳምጡ። የ...

**ነገር ግን ይህን እወቅ፡ በመጨረሻው ቀን፡**

“በመጨረሻው ቀን፡” የሚለውን አስምሩበት። ያ የሚሆንበት ጊዜ ነው።

**... አስጨናቂ ጊዜ ይመጣል።** (እኛ ውስጥ ነን።)

**ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፡ ገንዘብን የሚወዱ፡ ትምክህተኞች፡ ትዕቢተኞች፡ ተሳዳቢዎች፡ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፡ የማያመሰግኑ፡ ቅድስና የሌላቸው፡**

153 ዛሬ ያሉትን መንጎች ተመልከቷቸው፡ በሰብሰዋል። በመንገድ ላይ ወንድ እንኳ፡ ወጣት ወንድ፡ ጸጉሩን ወደ ግምባሩ እየጎተተ፡ ልክ እንደ ሴት ሆኗል። ብልሹነት! ሰዶማዊነት!

154 የዚህ ዓመት፡ የዚህ ወር **ሪደርስ ዳይጀስት** ላይ የወጣውን አንብባችኋል? እንዲህ ይላል፡ “የአሜሪካ ሕዝብ ዕድሜያቸው፡” እኔ እንደሚመስለኝ፡ “ከሀያ እስከ ሀያ-አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሰዎች፡ በመካከለኛ-ዕድሜያቸው ውስጥ።” የቀረ ነገር የላቸውም! በሰብሰዋል! ሳይንስ እንደሚለው፡ ወንድ

በመካከለኛው ዕድሜ ላይ፡ ሴት ደግሞ፡ ገና በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ ሲደርሱ። ስውነታቸው ለእድፈት የተሸጠ ከንቱ ነው።

ኦህ፡ አሜሪካ ሆይ፡ እግዚአብሔር ስንት ጊዜ ሊያሳርፍሽ ነበር፡ አሁን ግን ጊዜሽ ደርሷል! ዓለምን በእድፈት ውስጥ መራሽ...

**... ተሳዳቢዎች፡ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፡ የማያመሰግኑ፡ ቅድስና የሌላቸው፡**

**ተፈጥሮአዊ ፍቅር** የሌላቸው፡...

ወንድ ለሴት፡ ሴት ለወንድ ሳይቀር፡ እንዳቸው ለሌላው እውነተኛ ፍቅር የላቸውም። "ተፈጥሯዊ ፍቅር እንኳን የላቸውም።" ያደፈ፡ ወሲባዊነት!

**... ዕርቅን የማይሰሙ፡ ሐሜተኞች፡ ራሳቸውን የማይገዙ፡ ጨካኞች፡ መልካም የሆነውን የማይወዱ፡**

155 በሌላ አነጋገር፡ እንዲህ ይላሉ፡ "እናንተ የወንበር ሰባሪዎች መንጋ።" በቀደምለት አንድ ሰው ወደዚህ ቤተክርስቲያን መምጣት ፈልጎ ጠየቀ። "ወደዚያ አትሂድ። ሁሉም ትልቅ ጫጫታ እና ጫጫታ ብቻ ናቸው፡" አሉት።

እያችሁ፡ "መልካሙን የሚንቁ።"

**ከዳተኞች፡ ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ** ተድላን **የሚወዱ ይሆናሉ፥**

እናንተም "ወንድም ብራንሃም፡ ያ ኮሚኒስታዊነት ነው፡" ትላልችሁ። ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ምን ይላል?

**የአምልኮት መልክ አላቸው** (ምን? ) **ኃይሉን ግን ክደዋል፡** (ቃሉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነው፡ ተገለጠ፡ ለዘመናችንም የተሰፋ ቃል ነው)...

ልክ እንደ ሐናንያ፡ ልክ እንደ ሴዴቅያስ፡ ልክ እንደ በለዓም፡ ልክ እንደ ሌሎች፡ ሐሰተኛ ነቢያት።

**የአምልኮት መልክ አላቸው፡** (የተቀቡ... እያችሁ? )

**መልክ አላቸው፡** (የተቀቡ፡ የተሾሙ አገልጋዮች... )

**የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ነገ ግን** (እርሱ ትላንትና፡ ዛሬ፡ ያው መሆኑን... ቃሉን ይክዳሉ!)

156 በዚያን ቀን ኢየሱስን የካዱት እንዴት ነው? ኢየሱስን ሲክዱ የካዱት ማንን ነው? ቃሉን ነው። ሃይማኖተኞች ነበሩ። ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ያስተምሩ ነበር፡ ሆኖም የዘመኑን-ቃል ይክዱታል።

157 ዛሬስ ምንድናቸው? ተመሳሳይ ነገር፡ የተቀቡ፡ የጴንጤቆስጤን ወንጌል የሚሰብኩ፡ ነገር ግን የዘመኑን-ቃል የተረጋገጠውን የቃሉን ቃል ኪዳን ይክዳሉ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" እያችሁት? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—እርታዒ።]

**ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፡ ሁልጊዜም እየተማሩ... በብዙ የሚስቱትን**፡ ሐጢአተኞች **ሴቶች የሚማርኩ፡**

158 “የእኛ የልብስ ስፌት ፓርቲዎች እና **የእኛ እንዲህ-እና-እንዲያ።**” አንድ ሰው መጥቶ ቃሉን በተሳሳተ መንገድ ለመተርጎም ይሞክራል፡ እናም እንዲህ ይላል፡ “ጸጉርሽን ማሳጠር ከፈለግሽ፡ ችግር የለውም፡ እኅቴ። ለዚያ ለማይረባው ትኩረት አትስጪ። አያችሁ? ወይም፡ **ይህን**—ብትለብሺ፡ **ያ** አይሆንሽም፡ ‘ሰውን የሚያረክሰው ከልቡ የሚወጣው ነው።’” አያችሁ? ክፉ፡ ምግባረ ብልሹና፡ ርኩስ መንፈስ እንደተቀባችሁ ተገንዝባችኋል? ተጠንቀቁ፡ ጸጉራችሁ ቆራርጣችሁ በመዘምራን ቡድን ውስጥ፡ መዘመር ትችላላችሁ፡ አንድ ክፉ መንፈስ ግን አለባችሁ። ከዚህ ቃል ጋር ይቃረናል። ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ያለውም ይህ ነው። እናም እንዲህ ትላላችሁ፡ “መልካም፡ እኔ ቁምጣ መልበሴ። አይኮንነኝም።”

“ማንም ቢሆን፡ ሴት የወንድ ልብስ ብትለብስ፡ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው።” የማይለወጠው አምላክ እንዲህ ተናገረ።

159 ኦህ፡ ብዙ ነገሮች አሉ፡ እንዴት እናልፋቸዋለን? ጊዜያችን ያልቃል። ቢሆንም ትክክልና ስሕተት የሆነውን ነገር ማወቅ በቂ እውቀት ነው። ይህን እንዲያደርጉስ እንዴት ላደርጋቸው እችላለሁ? እንዴት ላደርገው እችላለሁ? “ተው እንጂ፡ ስለምን ትለፈልፋለህ፡” ትሉኛላችሁን? ስለ ክፋታችሁ እኔ ምስክር ነኝ። አንድ ቀን፡ በፍርድ ቀን፡ የምትገቡበት ጥግ አይኖራችሁም።

160 ሚክያስ ይህን እንዴት ሊያስቆም ይችላል? ሙሴ ይህን ለማስቆም፡ እየጮኸ፡ ሊያስቆመው የሚችለው እንዴት ነው? ኢያሱም በሕዝቡ መካከል ሲመላለሱ? ሌዊ ሰይፋን፡ መዘዘና፡ ገደላቸው? እንደዚሁ ቀጠሉ።

161 ይህን እንደሚያደርጉ በትንቢት ተነግሯል። ማድረጋቸው አይቀርም፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል ነውና ያደርጋሉ። እነዚህ ተቋማት ይለያያሉ ብላችሁ ታስባላችሁ፡ የሃይማኖት ተቋማቸው ወደ ቃሉ ይመለሳሉን? የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡ አያደርጉትም ይላል! የክርስቶስ ተቃዋሚ ወደ መሆን ይሄዳሉ? በትክክል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ብሏልና፡ ይቃወማሉ! “ስለ ምንድነው የምታወራው? ” እኔ ምስክር ነኝ፡ እናንተም፡ አማኞች ሁላችሁም እንዲሁ። ተመልከቱ።

### ... በብዙ ምኞቶች፡ የሚመሩ ሴቶችን፡

“መልካም፡ ሁሉም ሴቶች።” ሐሰተኛ ነቢያት! አሁን አዳምጡ። የማወራው፡ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ነው። አሁን በመጨረሻው ቀን ምን ያደርጋሉ?

### ... በ ምኞትንም የሚወሰዱትን... ሞኞች ሴቶች የሚማርኩ፡

“እሺ፡ ሌሎች ሴቶች ሁሉ አውቃቸዋለሁ... ” እሺ፡ ቀጥል።

162 በካሊፎርኒያ ውስጥ ይህ ትልቅ ክስተት ከመሆኑ በፊት ምን አልኩ? “እናንተ ሰዎች ሆይ በየዓመቱ ተመልሼ በመጣሁ ቁጥር፡ ከፊት ይልቅ የተቈረጠ-ጸጉር ያላቸው ሴቶች አያለሁ እና ሴታ ሴት ወንዶች ይበዛሉ፡ ብዙ ሰባኪዎች ወደ ድርጅት እየገቡ ነው። ያለ ቅጣት አትቀሩም! በእናንተ የተደረገው ተአምራት በሰዶምና በገሞራ ቢደረግ ኖሮ፡ ዛሬ ይቆሙ ነበርና። አንቺ፡ ቅፍርናሆም፡ አንቺ በመላእክት ስም የምትጠሪ፡ ሎስ ኤንጀልስ ሆይ!” ምን እየሆነች እንደሆነ አያችሁ? ወደ ባሕር ጥልቅ እየሰጠመች ነው። መቼ? መቼ

እንደምትሰምጥ አላውቅም። ግን ትሰምጣለች። እናንተ ወጣቶች፡ በእኔ ዘመን ውስጥ ካላየሁት፡ እናንተ ታያላችሁ። ትሰምጣለች!

> **ሁልጊዜም እየተማሩ:... እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን።**

አሁን አስደንጋጭ ነገር ይህ ነው፡ አስደንጋጩ ክፍል ይህ ነው። ይህን አዳምጡ።

> **ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፡ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ፡ አእምሮአቸው የጠፋባቸው፡ ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው** እውነትን ይቃወማሉ፡ ለቅዱሳን ፈጽሞ የተሰጠውን።

"እምነትን በተመለከተ ነው።" "እናም የአባቶችን እምነት፡ ወይም የልጆችን፡ ወደ አባቶች ይመልሳል።"

163 "ስለ እምነትም የተጣሉ።" ኸህ! **ምናምንቴ** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? የስኮፊልድ መጽሐፍ ቅዱስ ካላችሁ፡ እዚህ **ኤች** ላይ አለ። እዚያው ላይ፡ "ከሃዲነት፡" ይለዋል። ከሃዲነት፡ ማለት ነው።

164 አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። እኔ እዚህ ላይ አንድ ነገር መመልከት እፈልጋለው። ይህንን በትክክል የጻፍኩት ይመስለኛል። እርግጠኛ አይደለሁም፡ ግን መናገር እፈልጋለሁ፡ እና ከ—ከመናገሬ በፊት መፈለግ እፈልጋለሁ። አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። [በቴፑ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] "ስለ እምነትም፡ እውነትን የማይቀበሉ ምናምንቴዎች።" "እምነት፡" እምነት አንድ ብቻ ናት። በትክክል። "ስለ እምነትም፡ እውነትን የማይቀበሉ ምናምንቴዎች!"

ሉቃስ 18ን ማንበብ እፈልጋለሁ። አንድ ደቂቃ ብቻ። እ... እናንተ ማስታወሻ መያዝ ትችላላችሁ፥ ማንበብ አይጠበቅባችሁም።

> **ሳይታክቱም...** እስከ **ፍጻሜ** ዘወትር **ሊጸልዩ፡ እንዲገባቸው የሚል፡ ምሳሌን ነገራቸው፥**
>
> **-እንዲህ—እንዲህ ሲል፡ በአንዲት ከተማ፡ እግዚአብሔርን የማይፈራ፡ ሰውንም** የማያፍር **አንድ ዳኛ ነበረ፡**
>
> በዚያችም **ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፣ ወደ እርሱም እየመጣች፡ ከባላጋራዬ ፍረድልኝ፡ ትለው ነበር።**
>
> **እያሌ ቀንም አልወደደም፡** ከዚህ በኋላ **ግን በልቡ፡ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፡ ሰ—ሰውንም ባላፍራ፣**
>
> **ይህች መበለት ስለምታደክመኝ፡ ሁልጊዜም... እየመጣች እንዳታውከኝ፡ እፈርድላታለሁ አለ።**
>
> **ጌታም አለ፡ ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ሰሙ።**
>
> **እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት** ወደ እርሱ ለሚጮኹ፡ **ለሚታገሣቸውም... ምርጦቹ፡ አይፈርድላቸውምን?**
>
> **እላችኋለሁ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል። ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ፡ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?**

165 አሁን ጥያቄው ይኸው ነው። እዚህ ላይ ነው መድረስ የፈለግኩት፡ በራእይ 10 ላይ (በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ወደ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡ እንሄዳለን።)፡ እርሱም እንዲህ አለ፡ “በሰባተኛው መልእክ መልእክት ዘመን፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማ**ል**።” ጥያቄው የሚከተለው ነው፡ ጥያቄው፡ በዚህ ሰዓት ያንን መስመር ብትከተሉ፡ **ይ**ፈጸም ይሆን? “እምነትን አገኛለሁን? ” ሚልክያስ 4 በዚህ ዘመን ይፈጸም ይሁን፡ “የልጆችን እምነት፡ ወደ አባቶች እምነት፡ ወደ መጀመሪያው፡ ወደ ቃሉ ይቃና ይሆን”? አያችሁ?

166 “ምናምንቴዎቹ፡ ኢያኔስና ኢያንበሬስም፡ እንደተቃወሙት።” አሁን፡ ደግሞ፡ ሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3:8ን፡ አዳምጡ። “ኢያኔ-... ሙሴን እንደ ተቃወሙት፡ እንዲሁ ደግሞ በመጨረሻው ዘመን እንደዚህ ያሉ የሚቃወሙት ይነሳሉ፡” አሁን ምን እንደሚል ተመልከቱ፡ “የአምልኮት መልክ ያላቸው፡” የተቀቡ። አሁን እስቲ... ወደ ቤት ስትመለሱ—ደግማችሁ አንብቡት፡ ከቻልኩኝ፡ ይህን ጽሑፍ፡ ዛሬ ጠዋት ልጨርሰው እችላለሁ። “ስለ እምነትም ምናምንቴ የሆኑ... ” በ—በ—በኑሮአቸው ውስጥ ምናምንቴዎች አይደሉም፡ በዛማ ጥሩ፡ የሰለጠኑ ሰዎች ናቸው።

167 አሁን አስተውሉ፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ የሚል መልእክት ይዞ፡ ሙሴ ወደ ግብጽ ሲወርድና ሲመሰከርለት፡ እስራኤልን ጠራ፡ ቤተክርስቲያን ሳይሆን፡ ህዝብ። እስራኤል ህዝብ ነው እንጂ፡ መቼም ቤተክርስቲያን ሆነው አያውቁም። ምክንያቱም፡ **ቤተክርስቲያን** የሚለው ቃል “የ-ተጠሩ” የሚል ትርጉም አለው። የእግዚአብሔር ህዝብ ነበሩ። ከዚያም ከቃሉ ስር፡ ከተቀቡና ከተጠሩ በኋላ፡ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይሆናሉ። የአምላክን ቃል ሰላላመኑና፡ የሀሰተኛ ነቢይ ቃል ሰለሰሙ፡ ከሃዲዎች ሆኑ። ግልጽ ነው ብዬ እሰባለው።

168 እስራኤል፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆነ፡ በእግዚአብሔር ክንድ ወጥቶ፡ በቃሉ ተቀባ... በእግዚአብሔር ኃይል ተቀባ፡ የእግዚአብሔርን ምልክቶችና ድንቆችም አየ። እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ጉዞ ላይ በነበረ ጊዜ፡ ሐሰተኛ፡ ነገር ግን የተቀባ ነቢይ መጣባቸው፡ የሰሙትን የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ነገር አስተማራቸው፥ ከሦስት ሰዎች በስተቀር፡ ሁሉም በምድረ በዳ ጠፉ። አሁን በደምብ ተከታተሉኝ።

169 “በኖኅ ዘመን፡ ሰምንት ነፍሳት ከውኃ እንደዳኑ ሁሉ፡ በሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል።” “በሎጥ ዘመን፡ ሦስት ሰዎች ከሰዶም እንደወጡ ሁሉ፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል።” የምጠቅሰላችሁ፡ የጌታን ቃል ብቻ ነው፡ ይህም፡ “ሰማይና ምድር ያልፋል... ” እነሆ ታናሽ መንጋ ይሆናል!

170 እዚህ ላይ ልብ በሉ። ሙሴ ወደ አሮን ወረደ። ሙሴ አምላክ ነበረ። አምላክ እንዲሆናቸው እግዚአብሔር ነግሮታልና፡ እንዲህ አለው፡ “አንተ አምላክ ሁን፡ ወንድምህ አሮን ነቢይ ይሁን። በደንብ መናገር ከተሳነህ ቃላት በአፉ ውስጥ ታኖራለህ።” “ሰውን ዲዳ ያደረገው ማን ነው? ሰው እንዲናገር ያደረገው ማን ነው፡” አለው? ጌታ ነው ያደረገው።

171 እርሱም ወረደ። ምን አደረገ? እግዚአብሔር እንዲሰራ የጠየቀውን እውነተኛ እና በጽድቅ ተአምር አደረገ። እግዚአብሔርም፡ “ሂድና በትርህን

ጣል” አለው፡ እባብም ሆነች፡ አነሳትም። አነሳትና፡ ወደ በትርም ተመለሰች። አለውም፡ “ወደ ፈርዖን ሂድና፡ እንዲህ ብለህ ንገረው፡ ‘የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።’”

172 ፈርዖንም ይህን ባየ ጊዜ፡ እኛም እንደምንለው፡ “ምነው፡ እንዴት ያለ ርካሽ የጠንቋይ ብልሃት ነው አለ።” እንዲህ አለ፡ “እርባና ቢስ ነው። ታውቃላችሁ፡ አዕምሮን የማንበብ ብቃት ወይም ሌላ ነገር ነው። በድርጅታችን ውስጥም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ የሚችሉ ሰዎች አሉን። ‘ቢሾፕ **እከሌ-እና-እከሌ፡ ኑ ቅረቡ።** አንተም፡ ደግሞ፡ ና ወዲህ ቅረብ።’ እኛም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ የሚችሉ አሉን” አለው። በፈርዖን በኩል የሚናገረው ሰይጣን ነበር።

በሙሴ በኩል የሚናገረውም እግዚአብሔር ነው።

173 ይሁን እንጂ ይህ ሰው ሲወጣ ተመልከቱ። ኢያኔስ እና ኢያምብሬስ በሙሴ ፊት ወጥተው፡ በሕዝብ ፊት እንዲሁ መጥተው፡ ሙሴ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ተአምራቶች አደረጉ። “ቢቻልስ ኖሮ የተመረጡትንም ያስታሉና።” ይህ ትክክል ነው? ሙሴ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። ተረድታችኋል? አሁን አስታውሱ፡ መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡ በመጨረሻው ዘመንም እንደገና ይደገማል።

በሙሴና በኢያምብሬስ መካከል የነበረው ልዩነት ምንድን ነው?

ሙሴ፡ “ውሃው ውስጥ ደም ይሁን” አለ።

ሐሰተኞች ነቢያትም፡ “ይኸው፡ እኛም፡ ውኃው ውስጥ ደም መክተት ችለናል” አሉ። እንዲሁም ሆነ።

ስለዚህ ሙሴ “ቁንጫዎች ይሁኑ፡” አለ። ከማን እየተቀበለ ነበረ? በቀጥታ ከእግዚአብሔር ዘንድ። አያችሁ?

እና ምን አደረገ? “መልካም፡ እሺ፡ እኛም፡ ቁንጫዎች ማምጣት እንችላለን፡” አሉ። እንዲሁም አደረጉ። ሙሴ የፈጸመውን ተአምር፡ እነሱም፡ ማድረግ ይችሉ ነበር!

174 አስታውሱ፡ ልብ በሉ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እንመጣበታለን። ሌሎች የሚያደርጉትን ሁሉ ማድረግ ይችላሉ፡ ቃሉን መከተል ግን አይችሉም። ቃሉን መከተል አይችሉም።

175 ልብ በሉ፡ ማድረግ ይለዋል። ሙሴ ግን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ እውነተኛ-ነቢይ፡ በእግዚአብሔር የታዘዘ ነብይ ነበረ፡ “እናንተ፡ ይህን ማድረግ አትችሉም! አትችሉም!” በማለት፡ ከእነርሱ ጋር ሰጣ ገባ ውስጥ አልገባም። ተዋቸው፡ እንዲቀጥሉ ፈቀደላቸው። የድርጅት ነቢያት ናቸው፡ ግን ቀጠሉ።

176 ሙሴ በቀጥታ ሄዶ፡ እግዚአብሔርን አዳመጠ። እግዚአብሔር “አሁን **ይህን** አድርግ” ሲል፡ ሙሴ ያደርጋል። አዲስ ነገር ያደርጋል። ሲሆኑም፡ እያንዳንዳቸው የሆነ ስሜት ወይም የሆነ ነገር ይሆናሉ፡ ይኸው ይመጣሉ። እነሱም፡ ሙሴ እንዳደረገው፡ ያደርጉ ነበር።

177 አሁን ልብ በሉ። ሰዎቹ ብቅ ይላሉ... ኦህ፡ እናንተ ሰዎች፡ ይህ እንዳያመልጣችሁ! እነዚህ አጭበርባሪዎች፡ አስመሳዮች፡ እውነተኛው ሰው ከሄደ በኋላ ብቅ ይላሉ። አያችሁ? ለማስመሰል ይመጣሉ። አያችሁ፡

መምጣት ነበረባቸው። ዲያብሎስ ምንም ነገር መፍጠር አይችልም፥ ኦሪጂናሉን ማበላሸት ብቻ ነው።

ኃጢአት ምንድን ነው? የተጣመመ ጽድቅ ነው። ምንዝርና ምንድን ነው? የተጣመመ መልካም ስራ ነው። ውሸት ምንድን ነው? የተዛባ እውነት ነው። መዛባት!

178 ሐናንያን ተመልከቱት፡ የመጀመሪያውን ቃል መዛባት። በለዓምን ተመልከቱት፡ የመጀመሪያውን ቃል መዛባት። የሴዴቅያስን እንመልከተው፡ የመጀመሪያውን ቃል መዛባት።

መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሰዎች እውነት ለመሆን የተረጋገጠውን፡ ካጣመሙ በኋላ... ወይም የጸደቀውን እውነተኛውን ቃል ለማዛባት እንደሚመጡ ተናግሯል።

179 “የወንጌላዊነት ሥራህን አድርግ፡” ባለህበት፡ “የአገልግሎትህ የተሟላ ምስክር አድርግ። ምክንያቱም ሰዎች ጤናማውን ትምህርት የማይታገሡበት ጊዜ ይመጣል፡ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ፡ ከዚህ ይልቅ ከራሳቸው ምኞት ጋር የሚስማማ ብዙ አስተማሪዎችን ለራሳቸው ይሰበስባሉ፣ ከዚያም እየወጡ የፈለጉትን ማድረግ ይጀምራሉ፡ እና፡ ‘ችግር የለውም፡ እኛም ተመሳሳይ ምልክቶች አሉን’ ይላሉ። ከእውነትም ፈቀቅ ይላሉ፡ ወደ ተረትና ወደ ዶግማቲክ አስተምህሮ፡ ይወሰዳሉ።”

180 ኦህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ንቃተ ህሊና፡ በፊቱ ምን ያህል እውነት እና ግልፅ እንደሆነ ቆም ብሎ ሲያስብ የሰውን ነፍስ የሚመታ ፍርሃት! የዛሬ ሰላሣ-ሶስት አመት፡ የመሰረት ድንጋይ ተቆፈረ ያ እዚያ ያለው ትንሽ ወረቀት ተነበበ። ይህ የማዕዘን ድንጋይ በተቀመጠበት በ—በዚያ ማለዳ በስሸንዝ ሰትሪት ላይ፡ የተናገረውን ተመልከቱ። አሁን ተመልከቱ። እዚህ ወንዝ ላይ፡ የጌታ መልአክ በእሳት ዓምድ መልክ ሲወርድ፡ በመቶዎች የሚቈጠሩ አብያተ ክርስቲያናት፡ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች፡ በወንዙ ዳርቻ ላይ ቆመው ነበር፣ የተናገረው ነገር፡ ከተፈጸመ ተመልከቱ። ምን እንደሆነ ተመልከቱ።

181 በጣም ከባድ ነው። ከባድ ነገር እንደሚመስል፡ አውቃለሁ፡ ወንድሞቼ። ነገር ግን... መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ ኢየሱስ ራሱ እንዲህ ብሏል፡ “ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።” ዙሪያው መንገድ የለውም። ፈጽመው አያዩትም። የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፡ የተመረጡት እንኳ ይስቱበት ነበር።

182 አስተውሉ፡ እነዚህ ሰዎች ብቅ ያሉት እውነተኛው ከእግዚአብሔር የተቀባ፡ የእርሱ እውነተኛ ነብይ፡ ሙሴ ከተላከ በኋላ ነው። ሙሴ ሁሉን ማድረግ ይችላል፡ እነሱ ሲያስመስሉ ነበር።

183 አሁን፡ ወንድሞቼ፡ እኅቶቼ፡ እኔ... ይህ የራሴ ቤተ ክርስቲያን ነው። ከእግዚአብሔር ቃል እስከሆነ ድረስ፡ የፈለግኩትን የመሰበክ መብት አለኝ። እኔም እናንተን አልኰንንም፡ ነገር ግን አሁን የምንኖርበትን ጊዜ እና ሰዓት እንመርምር።

184 ለወንድም ሩዴል፡ ለጁኒየር ጃክሰን፡ እና እዚህ ላሉት፡ ወንድማማች ቤክርስቲያናት ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ቀደም ሲል፡ የረሳኋቸው። ዛሬ

ጠዋትም በቤተ ክርስቲያኑ ምንም—ቦታ ስላልነበረ፡ በመገናኛ ዘዴ እየተከታተሉ ያሉም፡ አሉ።

185 እስቲ ለአንድ ደቂቃ፡ እስቲ አስቡት። ሙሴ የሠራቸውን ተአምራት ፈጽመዋል። ሙሴ ቁንጫዎችን አመጣ፡ እነሱም አስመሰለው ቁንጫዎችን አመጡ። አያችሁ?

እግዚአብሔር “ከእርሱ በበላችሁ ቀን፡ በእርግጥ ትሞታላችሁ፡” አለ።

186 ሰይጣን መጣና እንዲህ አለ፡ “በእርግጥ ጥበበኛ ትሆናላችሁ እንጂ፡ አትሞቱም አለ። የተሻለ ድርጅት ይኖራችኋል፡ የተሻለ... ” ታውቃላችሁ። “ታውቃላችሁ፡ ሁሉም ነገር የተሻለ ይሆንላችኋል፡ የተሻለ ብርሃን ይኖራችኋል።” አያችሁ፡ ማዛባት ብቻ። እና...

187 አስታውሱ፡ በሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3፡18 መሠረት፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ ይህም፡ “በመጨረሻው ዘመን፡ ኢያምብሬስና ኢያኔስ በምድር ላይ ይነሣሉ።” አሁን፡ ሁለቱ ሰዎች መኖራቸውን ልብ እንድትሉ የምፈልገው፡ አያችሁ፡ አስመሳዮች።

188 እስቲ ወደ ሶዶም ልመልሳችሁ፡ ከጊዜ በኋላ፡ እነዚያ ሶስት፡ ሶስቱ መላዕክት እንደመጡ አይተናል፡ እና ማስመሰሉን፡ ወዘተ ተመልከቱ፡ አያችሁ፡ የትኛው ልክ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ተመልከቱ። አያችሁ? አያችሁ?

189 አስተዉሉ፡ ተመሳሳይ ተዓምር አደረጉ። ነገር ግን፡ አስተዉሉ፡ ያስመሰሉት ግን፡ ቃሉ በእግዚያብሔር በተላከዉ፡ እውነተኛ ላይ ከተቀባ በኋላ ነው፡ በሁለተኛነት፡ ብቅ አሉ።

190 ለአንድ ደቂቃ ብናሰበው ብዮ አሰባለው። በቅርብ ጊዜ፡ ከሀያ ዓመት ገደማ በፊት፡ ሰዎችን በእጃቸው ይዤ፡ ምልክት ታየ። ወንድሜ፡ በሁሉም ነገሮች ላይ ምልክቶች፡ እና ሌሎች ነገሮች ነበሩ... አንዱ በቀኝ እጁ፡ ሌላዉም በግራ እጁ፡ ሌላውም ያሸተዋል። ሁሉም አይነት፡ ተመልከቱ... የሚያሳሰበኝ... በዚህ ጊዜ እዉነቱ ምን እንደሆነ እንድነግራችሁ እግዚያብሔር አይፈቅድልኝም፡ አንድ ቀን ግን እውነቱን ታገኛላችሁ። ያም ከንቱነታቸው እንዲገለጥ ብቻ ነዉ። በመጀመሪያ፡ ትክክል አልነበረም። ጌታ ቢፈቅድ፡ አንድ ቀን፡ እነግራችኋለዉ።

191 አስተዉሉ፡ ተመሳሳይ ተዓምራትን አድርገዋል፡ ነገር ግን... ልብ በሉ፡ በመጀመሪያ፡ እውነተኛው ቃል እስኪወጣ ድረስ ምንም አላደረጉም። ሰይጣን በኤደን ገነት ያደረገዉ እንደዛ ነዉ። ሁልጊዜ የሚያደርግበት መንገድ ይህ ነዉ። ማን አስቀድሞ ትንቢት ተናገረ? ሙሴ። መጀመሪያ ወደ ትዕይንቱ ማን መጣ፡ ሙሴ ወይስ በለዓም? ሙሴ። መጀመሪያ ወደ ትዕይንቱ ማን መጣ፡ ኤርምያስ ወይስ ሐናንያ? ለማለት የፈለግኩት አያችሁ?

192 ልብ በሉ፡ ኮረጁ። ከቅን ልብ የሚያደርጉ፡ ሥጋውያን አስመሳዮች፡ ባለፈው ሳምንት እንዳየነው፡ እንደ ዳዊት፡ “እግዚአብሔርን እናገለግላለን” ብለው ያስባሉ፡ ነገር ግን ሥጋውያን አስመሳዮች ናቸው። ትንሽ ጊዜ ልስጣችሁ። በእነዚህ ነገሮች እንድታስቡ እፈልጋለሁ። እኔ ካልተናገርኩ፡ በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ ይገልጠዋል፡ በተለይም ለተመረጡት። አያችሁ?

193 የፈርዖን ሃይምኖት እንዲህ ይላል፡ “እኛም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ የሚችል ሰው አለን፡” እነሱም አደረጉት። አያችሁ? ፈርዖን ይህን ለምን አደረገ?

እግዚአብሔርስ ለምን ፈቀደው? እግዚአብሔር አንድን እውነተኛ የተቀባ ነቢይ፡ በፈርዖን ፊት ታምራቶችን እንዲያደርግ ለምን ላከ፡ እና ሃይማኖታዊ ኩረጃ መጥቶ በሰዎች ፊት እንዲያስመስል ለምን አደረገ? አስመሳይ እንዲነሳ እውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረገው ነገር፡ በትክክል እንዲፈጽም ለምን ፈቀደ? አያችሁ፡ የቅዱሳን መጻሕፍት ቃል መፈጸም አለበት።

194 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ይህን ያደረገው የፈርዖንንና የግብፃውያንን ልብ ለማደንደን ነው፡ ሙሴ ቃሉን የያዘ ብቸኛው ሰው አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ሙሴ ያደረገውን ሁሉ እነሱም ማድረግ ይችሉ ነበር።

195 እና እግዚአብሔር ይህ ነገር በመጨረሻው ዘመን እንዲከሰት የፈቀደው ለምንድን ነው? ስለዚህ፡ ሴዴቅያስን እንደ ውሸታም መንፈስ ሆኖ የተናገረው ተመሳሳይ መንፈስ፡ "እነዚያ ነገሮች እንዲፈጸሙ፡ አክዓብን ወደዚያ ሰፍራ እንዴት እናወጣዋለን?" እነዚያ በቤተክርስቲያኖቻቸው የታመኑት ሰዎች፡ እንዴት ያወጣቸዋል፡ እነዚህ ነገሮች እንዲፈጸሙ፡ ወደዚህ እንዲመጡ እንዴት ሊያደርጋቸው ይችላል? እነርሱ፡ በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን "'ሀብታም' ነኝና፡ ባለጠጋ ሆኜአለሁ፡ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም፡ ንግሥት ሆኜ እቀመጣለሁ ብለሻልና።' ምንም የሌለህ! ጐስቋላና ምስኪንም፡ ዕውርም፡ የተራቆትህም መሆንህን አታውቅምን? ስለዚህ ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ፡" "ዘይትና ወርቅ" አለው። ለምን እንዲህ አደረገ?

196 እነዚህ ነገሮች የሚፈፀሙት በእውነተኛው የአምላክ ቃል አማካኝነት በሚሆንበት፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ይህ አስመሳይ እንዲነሣ የፈቀደው ለምንድን ነው፥ አስመሳዮችም መጥተው ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉና፡ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲክዱ የፈቀደው ለምንድን ነው? ለሙሴም እንዲሁ አደረገ። ፈርዖንም በሙሴ ላይ እንዲሁ አደረገ፡ ሌሎቹም፡ ኢያኔስ እና ኢያምብሬስም፡ ሙሴ ላይ እንዲሁ አደረጉ። በዘመን ፍጻሜ እንደሚደገም መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል። ይኸው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ ካልተፈጸመ፣ የት ነው?

197 ሙሴ እንዲህ በማለት ጎርሯልን፡ "ይኸውላችሁ! ይኸውላችሁ! እንዲህ አትሁኑ። ይህን ለማድረግ የተሾመው ብቸኛው ሰው እኔ ነኝ። ይኸውላችሁ! አሁኑኑ፡ አቁሙ"? እርሱ ዝም አላቸው።

198 ዝም አላቸው። አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሏል፡ "ከንቱነታቸው እንደ ተገለጠ፡ እነዚያም በዘመን ፍጻሜ ይገለጣሉ።" ሙሽራይቱ ተነጥቃ ወደ ሰማይ በምትወሰድበት ጊዜ ይገለጣሉ። አስተውሉ።

ሙሴ፡ እውነተኛው የተገለጠ ቃል፡ ምንም ነገር አልተናገረም፡ ብቻ ተዋቸው። ይህን ያደረገው ግን የፈርዖንን ልብ ለማደንደን፡ ፈርዖንን ለማታለል ነው።

199 አክዓብን ለማታለል ሲል ተመሳሳይ ነገር አድርጓል። ብቻውን የቆመ ያ ታናሽ ሰው፡ ምስኪኑ ሚክያስ፡ "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡" አላቸው። ሌላም የተቀባ ሰው መጣና፡ "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡" አለ። ሁለቱም፡ የሚቃረኑ ነበሩ።

200 እኛም ዛሬ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል ከሚለው ጋር እንቆማለን፡ ይህም በመጨረሻው ዘመን የውሃው ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ

ስም ይሆናል ነው። ሌላኛው ተአምራት አድራጊ ሰውም ይመጣል፡ እና፡ የሰላሴ እምነት አማኝ ነው።

201 ***ሥላሴ*** የሚለውን ጽኁፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለ አሳዩኝ። ሦስት አማልክት ያሉበትን ስፍራ አሳዩኝ። እንዲህ ያሉ ነገሮች የት እንዳሉ አሳዩኝ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የለም። "በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም፡" እነዚህን መገለጫዎችን ተጠቅሞ የተጠመቀ አለ የሚል ነገር አንድም የለም። ይህ ሁሉ፡ "ኦህ፡ ምንም ችግር የለውም፡ እኅቶች። ጽጉራችሁን ብታስረዝሙት... ማለቴ ብታሳጥሩት፡ ምንም ችግር የለውም። ምንም ችግር የለውም። **ይህንን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** ማድረግ የለባችሁም፡ ኦህ፡ ያም ትርጉም የለውም፡ አንዳንድ ያረጁ ደመናዎች ናቸው።"

202 መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይላል! እነሆ ቃል ገብቷል፡ "በመጨረሻው ዘመን፡ የኤልያስን መንፈስ ይልካል፡ ሰዎችንም፡ የእግዚአብሔርን ልጆች፡ በቃሉ ወደ ነበረው ጅማሬ፡ ወደ መጀመሪያው እምነት እንዲመለሱ ይጠራቸዋል።" ይህ ቃል ተረጋግጧል፡ የሰው ልጅ በዘመን ፍጻሜ፡ በሶዶም እንደነበረው፡ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘለዓለምም ነው። ይህን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። የእግዚአብሔር ቃል ነው። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚል ነው።

ልብ በሉ፡ እግዚአብሔር በቃ እስኪል ድረስ፡ ሙሴ እንዳደረገው ሁሉ፡ እነሱም ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል።

203 አሁን አስታውሱ፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚለው፡ በዚህ ቀን ይፈጸማል። አሁን፡ በዓለም ዙሪያ ፈልጉ፡ እያንዳንዱን የአምልኮ ሥርዓት ውሰዱ፡ እያንዳንዱን ኀሳ ውሰዱ፡ እያንዳንዱን ሰው ውሰዱ፡ እያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ውሰዱ! እናንተ ሰባኪዎች፡ ይህን እንድታደርጉ፡ በክርስቶስ ስም፡ እምላችኋለሁ። ጋዜጦችን እንድታነቡ አደራ እላችኋለሁ ወይም መሄድ በምትፈልጉበት ቦታ ሁሉ ሂዱ፡ እና አሁን በምድር ላይ ካልሆነ ተመልከቱ። አያችሁ?

204 ስለዚህ፡ ማቴዎስ 24:24 ፍጹም ትክክል ነው። "ሐሰተኛ፡ የተቀቡት በመጨረሻው ዘመን ይነሣሉ፡ ሐሰተኛ ነቢያትም ይሆናሉ፡ ብዙዎችንም ያስታሉ።" "ብዙዎችን ያስታሉ፡" የሚለውን፡ በምሳሌዎቹ መካከል፡ አሁን ተመልከቱ። "ነቢያት፡" ብዙ ቍጥር ነው፥ "ክርስቶሶች፡" የተቀቡት፡ ብዙ ቍጥር ነው፥ ብዙና የተለያዩ ናቸው፡ ሜቶዲስቶች፡ እና ታውቃላችሁ፡ ባፕቲስቶች፡ እና ጴንጤቆስጤ፡ እና የመሳሰሉት። አያችሁ?

ነገር ግን አንድ እውነተኛ የክርስቶስ መንፈስ አለ፡ እርሱም ይህን ለማድረግ እንደገባው ቃል ኪዳኑ ቃል ሥጋ ሆኖ ነው።

አሁን ደግሞ ወደ ተጨማሪ፡ ጥቅሶች እንሄዳለን።

እግዚአብሔር በቃ እስኪል፡ ድረስ ቆዩ፡ ከዚያ ሁሉም ነገር አበቃ። ከንቱነታቸው ተገለጠ።

205 አስተውሉ። ቅርፊቱ፡ በትክክል የስንዴ ፍሬ እንደሚመስል አስታውሱ። አያችሁ? አሁን ያኔ፡ በሉተራን ዘመን ዘንድ፡ "ግንዱ ስንዴ ነው፡" ማለት አይቻልም፡ ነገር ግን በውስጡ ሕይወት አለው። ግንዱ ምንም ችግር የለበትም፡

በግንዱ ውስጥ ያለው ህይወትም መልካም፡ ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ሕይወት አልቆመም አድጓል፥ ከኤልሳዕ ጀምሮ እስከ ኤልያስ ድረስ አድጓል። እድገቱን ይቀጥላል። ነገር ግን፡ ወደ ሌላ ደረጃ መሆኑን፡ አስታውሱ። በዚህ ደረጃ ላይ መቈየት አይቻልም። የሌላ ዘመን በድን ሙብላት አንችልም። የጴንጤቆስጤን በድን፡ የሜቶዲስት፡ ወይም የባፕቲስት በድን ሙብላት አንችልም። አያችሁ፡ በድን ሆነ። ትኩስ ምግብ፡ የዘመኑ ቃል፡ የመሳሰሉት አሉን።

206 ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ቢኖር፡ ቅርፊቱ ልክ የስንዴ ፍሬ ይመስላል። አትለዩትም... ሳር ሳለ አይመስለውም፡ ዝራረት ላይም አይመስለውም፡ ቅርፊቱ ላይ ግን በእርግጠኝነት ይመስለዋል። እዚያኛው ላይ አይመስለውም... በሉተር ዘመን፡ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ያው አይመስልም፥ በዌስሊ ውስጥ አይመስልም፥ ነገር ግን በጴንጤቆስጤ ውስጥ በእርግጠኝነት ይመስላል፡ ይህም “ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን ያስታል።” አያችሁ? ይሄው ነው ዘመናችሁ።

207 ነገር ግን፡ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን፡ በመጨረሻው ዘመን፡ የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን እንደነበረች አስታውሱ፣ እናም ክርስቶስ መጥቷል፡ ዘሩ፡ ስንዴው፡ ራሱ። እንዲህ ሲሞክር... በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ራሱን ለመግለጥ ሲሞክር፡ ወደ ውጭ እንደተወሰደ፡ አስታውሱ። አሁንም ተቀብታለች፡ በተባለች፥ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር።

208 ነገር ግን ቃሉ **ይህ** ነው፡ ክርስቶስ ራሱ፡ ይህም ለገዛ አካል፡ ለሙሽራይቱ ተቀብቶ የሚወርድላት ቃል ራሱ ነው። ስንዴው ላይ በወረደው ውኃ፡ ልክ እንደተናገርነው፡ የተቀቡትን፡ እንክርዳዶቹንም፡ ማለት የተቀቡ ሰዎችንም ያጠጣቸዋል። በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት የሚችሉት፡ የተመረጡ፡ ወይም አስቀድመው የተወሰኑ ብቻ ናቸው። አሁን፡ ኤፌሶን 5፡1 እንዴት እንደነበረ፡ እንዲህ ይላል።

209 እነሱ የተቀቡ ሰዎች ናቸው። ሰው ሁሉ፡ “ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! እዚህ ጋር ነጻነት አገኘን። ሃሌሉያ! ይላል... ኦህ፡ ሃሌ ሉያ! በልሳኖች እንናገራለን፡ እንዘላለን። እኛ የሴቶች ነጻነት አለን፣ እናንተ ሰዎች እነዚህ ሁሉ ነገሮች ውስጥ ልታስገቧቸው ትሞክራላችሁ።” አያችሁ? ቀጥሉ። ማድረግ የምትችሉት ምንም ነገር የለም። ይኸው፡ “በትክክል፡ በልሳኖች እንናገራለን፡ እንጮኻለን። በመንፈስ እንጨፍራለን። ቃሉን እንሰብካለን፡” ይላሉ። ከእሱ ጋር የሚቃረን ነገር የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት እነዚህ ሰዎችም እንዲሁ ያደርጋሉ።

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ቢቻልስ ኖሮ፡ የተመረጡትን እንኳ ያስታል።”

210 አሁን ልብ በሉ፡ ቅርፊቱ... ከመጀመሪያው ዘር፡ ወደ መሬት የገባው ዘር፡ ምንም ድርጅት አልነበረውም። ራሱን የቻለ፡ ፍሬ ነበር። ሲወጣ ግን፡ ፍሬ ሳይሆን፥ ድርጅት ነበር፡ አያችሁ፡ ቅጠሎች፡ ስብል።

ከዚያም ወደ ሌላ ደረጃ ተሻገረ፡ ይህም ወደ ዝራረት። አሁንም ግን እንደ መጀመሪያው አልነበረም። ድርጅት ነበር።

211 ወደ ቅርፊት አደገ፡ ብዙ ቅጠሎችም አወጣ፡ ጴንጤቆስጤ፡ አሁን ከሞላ ጎደል መልኩን ይዟል። እስቲ ተመልከቱት። ከጊዜ ወደ ጊዜ መልክ እየያዘ

ነው፡ ተመሳሳይ መልክ ይዟል ማለት ይቻላል፡ እዚያ ያለውን ትንሽ ፍሬ ስትመለከቱት በትክክል የስንዴ ቅንጣት ይመስላል።

212 ነገር ግን በመጨረሻ ተገለጠ፡ እና ምንም ድርጅት የለም። ከእንግዲህ ተሸካሚዎች የሉም። ድርጅት ተሸካሚ ብቻ ነው። ከንግዲህ ተሸካሚዎች የሉም፡ ግንዱ መሞት አለበት፣ አገዳው መሞት አለበት፡ ሁሉም ነገር መሞት አለበት፡ ነገር ግን ስንዴው መኖር ይቀጥላል። የትንሳኤው አካል፡ በቀጥታ ወደ ታች ይመጣል እና እነሱን ይወስዳቸዋል። "ኋለኞች ፊተኞች፡ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።" አያችሁ፡ በትንሣኤው ቀን ያስነሣቸዋል። እየተከታተላችሁ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታኢ።] መልካም። አስተውል፡ ፍሬው...

213 ቅርፊቱ በትክክል ፍሬውን ይመስላል። እና የስንዴ እርሻ፡ ወይም ሌላ ነገር ያለው ሰው፡ አይቶ እንዲህ ይላል፡ "እግዚአብሔር ይመስገን፡ የስንዴ ሰብል አለኝ፡" የስንዴ ቅንጣት ሳይኖረው አለኝ ይላል። እምም? ሲታይ ስንዴ ይመስላል፡ ነገር ግን እንክርዳድ ነው።

214 አሁን፡ እንግዲህ ወዳጆቼ፡ ከእኔ ጋር ወደ ኋላ እንመለስ። የክርስቶስ ሙሽራ የሆነች አካሉ፡ የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ከመውደቋ (ከሞት) በኋላ፡ የመጀመሪያው ሪቫይቫል የመጣው፡ ከየት ነው? ክርስቶስ ሙሽራውን አደራጀት፡ ቤተክርስትያኑን፡ ልክ ነው? በፍጹም አላደራጀም፥ በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ሐዋርያትን፡ ነቢያትን፡ እና የመሳሰሉትን፡ በመሾም ንጹሕ እንድትሆን አድርጓታል። ከሦስት መቶ ስድስት ዓመታት በኋላ ግን፡ በኒቂያ ላይ፡ ሮም ውስጥ፡ ተደራጁ እና ድርጅት አቋቋሙ። እውነት ነው? ያን ጊዜ ሞተች። ከዚያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የማይስማማ ማንኛውም ሰው ተገደለ። እናም እስካሁን ድረስ፡ ለብዙ መቶ ዓመታት በቆሻሻው ውስጥ፡ ወደቀች።

215 ነገር ግን፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ በሉተር ውስጥ መጣች። የስንዴ የመጀመሪያ ትንሽ ሳሮች ወጡ። ሁለተኛው ደግሞ፡ ከዚያ ውስጥ ወጣ። ቀጠሉ፡ እነ ዙዊንግሊ እና የመሳሰሉት መጡ፡ እና ሌሎች ድርጅቶች እና የመሳሰሉትን ቀጠሉ። ከዚያ፡ ከጊዜ በኋላ ደግሞ፡ አንግሊካን መጣች።

216 ከዚያም በኋላ ምን ሆነ? ዌስሊ ከአዲስ መነቃቃት ጋር ብቅ አለ። በትንሹ ስንዴ የሚመስል፡ ከዝራረት ጋር መጣ። ከዚያም ምን ሆነ? ተደራጀ፡ እና ደረቀ እና ሞተ።

217 ሕይወት በቀጥታ ወደ እንክርዳዱ ገባ፡ እና እንክርዳዱ ልክ እንደ ስንዴው ፍጹም ሆኖ ወጣ። በመጨረሻ ግን፡ ባለፉት ሰምንት፡ ወይም አሥር ዓመታት፡ በተለይም ባለፉት ሦስት ዓመታት የእርሱ ክፋት በግልጽ ታይቷል። አሁን ምን አደረገ? ከስንዴው ራቀ።

218 አሁን በዚህኛው ታላቅ መነቃቃት ውስጥ ግን ባለፉት ሀያ ዓመታት ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት የሌለው ለምንድን ነው፡ የተቀቡ ነቢያት፡ የተቀቡ አስተማሪዎች፡ እና የመሳሰሉት አሉ፡ እዚህ ግን ለምን የለም? ከፍሬ በኋላ ምንም ስለሌለ። አያችሁ፡ ያለ ድርጅት፡ ተመልሷል። ኦህ፡ ማይ፡ ዓይነ ስውር ሰው ሳይቀር ሊያየው ይችላል። መደራጀት አይችልም፡ በእጅጉ ይቃወማል። የስንዴ ዘር፡ ራሱ ነው። የሰው ልጅ ይገለጣል። በመጨረሻው ዘመን የስንዴ ዘር፡ የሰው ልጅ ወደ ራሱ ይመለሳል።

219 “በመጨረሻው ቀንም፡ በእርሱ ላይ የሐሰት አሰመሳዮች ከውሰጡ ይነሣሉ፡ ከተቻለም የተመረጡትን እንኳ ሊያታልል።” ድርጅታዊ ቅርፊታቸው አሁን እየተወገደ እንዳለ አሁን ተመልከቱ።

220 የሰንዴው ክፍል ለሆኑት፡ ለተመረጡት ብቻ፡ እንዲታወቅ ይደረጋል። ምን ያህል ደሰ እንደሚል ልብ በሉ። ብቻ… አሰተውሉ፡ የተቀቡት ሰዎች እንዲህ ይሆናሉ፡ ይልቁን የተመረጡት እውነተኞቹ፡ አሰቀድመው የተወሰኑት፡ ወደ ኤፌሶን ሰዎች፡ 5:1 ላይ፡ ማለት፡ 1:5 ላይ፡ የተሾሙ ይሆናሉ፡ የተመረጡ ይሆናሉ። የማይሳሳቱ እነሱ ብቻ ናቸው።

221 የተቀቡት ነቢያት ሐሰተኞች እንደሚሆኑና፡ ከእነዚህም መካከል በእውነት የተቀቡ እንደሚገኙ፡ ልብ በሉ። እንዴት ታውቁታላችሁ? በቃል። ልክ፡ ጥላ ውሰጥ እንዳየነው ነው። አያችሁ? እሰቲ “ኣሜን፡” በሉ። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—እርታኢ።] አያችሁ?

222 ልብ በሉ፡ የተቀቡ ሰዎች፡ የሚለያቸው ቃሉ ብቻ እንጂ፡ ምልክቶቹ አይደሉም። ኦህ፡ አይደሉም። እነሱም ተመሳሳይ ምልክቶችን ያደርጋሉ፡ የሚለያቸው ግን ቃሉ ነው። በትክክል። ሁሉም ተመሳሳይ ትንቢት ተናግረዋል። ሁሉም **ይህን፡ ያን፡** ወይም **ሌላውን፡** በተመሳሳይ መልኩ፡ አድርገዋል። ኢየሱሰ ተመሳሳይ ነገር እንደሚያደርጉ ተናግሯል። የሚለያቸው ግን፡ ልብ በሉ፡ ምልክቶች አይደሉም ቃሉ ነው።

223 ልብ ብላችኋል? ኢየሱሰ፡ በማቴዎሰ 24 ላይ እንዲህ ብሏል። “በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኛ ኢየሱሶች ይነሣሉ።” አላለም። ኦህ፡ አይሆንም፡ ለእዚያ በጭራሽ አይቆሙም። አይሆንም። አንድን እውነተኛ የጴንጤቆሰጤ እምነት ተከታይ፡ ራሱን፡ “ኢየሱሰ ነኝ፡” ይላል ብላችሁ ታሰባላችሁ? አያችሁ? አንድ ሐሰተኛ ሜቶዲሰት፡ ወይም ባፕቲሰት፡ ወይም እንደዚህ ያለ ሰው፡ ወይም ከድርጅቶቹ አንዱ፡ “እኛ ኢየሱሰ ነን፡” ይላሉ ብላችሁ ታሰባላችሁ? ከዚህ የተሻለ ነገር ያውቃሉ። ይህን አያደርጉም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሰ “ሐሰተኛ ክርሰቶሶች” ይመጣሉ ብሏል፡ “ሐሰተኛ ክርሰቶሶች፡” እንጂ፡ ኢየሱሶች አይልም። “ኢየሱሰ ነኝ፡” ቢሉ፡ ማንም አያውቃቸውም። ኦህ፡ አያቃቸውም።

224 ነገር ግን “ሐሰተኛ ክርሰቶሶች” ናቸው፡ እና አያውቁትም፡ ምክንያቱም ቃሉን ይቃረናሉ። እና እግዚአብሔር ያጸድቃል። አሁን, አሁን ይህን ለግጥሚያ በማምጣት ላይ ነኝ፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ተመሳሳይ ነገር በእውነት ሲሆን አይተናል። ኢየሱሰም እንዲህ ብሏልና።

225 አሁን፡ እንደነገርኳችሁ፡ በሰልክ መገናኛው—ዘዴ ያላችሁ፡ እናንተ ሰዎች፡ እየኮነንኳችሁ አይደለሁም፡ ይህች ግን ቤተክርሰቲያኔ ናት እና—እና መንፈሰ ቅዱሰ የሾመኝ ቡድኔ፡ ሰለሆነ እውነቱን ልነግራቸው ይገባኛል። ሰዓቱ እየረፈደ ነው።

226 አሁን፡ “ሐሰተኛ ክርሰቶሶች፡” ሐሰተኞች፡ የተቀቡ ሰዎች፡ ካልሆኑ በቀር፡ ያንን መጠቀም አይችሉም፡ በሁሉም የቃሉ ምልክቶችና ፊደላት የተሞሉ ናቸው። “በመንፈሰ ቅዱሰ ጥምቀት ያምናሉ?” በደንብ። “**በዚህ** ሁሉ ያምናሉ?” አዎን። “በልሳን መናገርንም ያምናሉ?” አዎን። “ምልክቶች እና ድንቆች እንደሚከተላቸው፡ ምልክቶች እንደሚከተላቸው ያምናሉ?” አዎን። ያ

ሜቶዲስት አይደለም፡ ያ ባፕቲስት አይደለም፡ አይ፡ አይ፡ ያ የጴንጤቆስጤ ነው። እያችሁ፡ ይህ የመጨረሻው ዘመን ነው።

227 አሁን፡ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን ይህንን በጭራሽ ሊያስተውሉት አይችሉም። የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ዘመን ይህን አላስተዋለም፥ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ይህን አላስተዋለም፥ የፕሬስባይተሪያን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ይህን አላስተዋሉም። ነገር ግን፡ ጴንጤቆስጤ፡ ለዋናው በጣም ቅርብ ነው! ሰንዴው... ማለት ቅርፊቱ ልክ እንደ ሰንዴው የሚመስልበት፡ እዚህ ጋር ነው። እነርሱ ፈጽመው አያስተውሉም። እያችሁ? አያስተውሉትም። ይሁን እንጂ፡ ይህ የመጨረሻው ቀን ነው። አዎን፡ ወዳጄ።

228 አስተውሉ፡ መጀመሪያ ላይ እንደነበረው ሁሉ፡ በመጨረሻም እንዲሁ ይሆናል... ሔዋን አንድን ቃል በተሳሳተ መንገድ እንደተረጎመችው፡ ሰይጣንም ሔዋንን ይህ አደረጋት፡ እሷም አመነችው። እሷ እንጂ፡ እርሱ አይደለም፥ ቤተ ክርስቲያን እንጂ፡ እርሱ አይደለም። እያችሁ? ሐሰተኛውን ቃል የተናገረችው ቤተክርስቲያኗ ነች። እያችሁ? አዳም አይደለም፡ ሄዋን ናት። ክርስቶስ አይደለም፡ ቤተክርስቲያኗ፡ ሙሽራዋ፡ የተቀባች፡ መሆን የነበረባት፡ ራሷን ሙሽራ ብላ የምትጠራ፡ እያችሁ፡ የተሳሳተ ቃል ይዛለች።

229 ይህን ማየት አትችሉም? ለምን፡ እንደ ጫማ ክር ይመሳሰላሉ፡ እንደ ኣይኖቻችሁ ጭራ ይመሳሰላሉ። ለምን፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ በከፈታችሁ ቁጥር፡ በደንብ አንድ ላይ ይተይበዋል። ሔዋን፡ አዳም ሳይሆን፥ ሔዋን አመነች፡ አዳም አይደለም። ዛሬም፡ ሙሽራይቱ ነኝ፡ ባይዋ-እንጂ፡ ክርስቶስ አይደለም። ሙሽራይቱ፡ ሙሽራ ነኝ-ባይዋ ሁሉም ነገሮች አሏት፡ ተመሳሳይ ምልክቶች፡ ተመሳሳይ ድንቆች፡ ሁሉም ነገር ተመሳሳይ ነው፡ እውነተኛዋ ግን አይደለችም። "ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን ያስታሉ።"

230 አሁን በፍጥነት፡ ይህንን በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ማጠናቀቅ ከቻልን፡ በጊዜ እንወጣለን። በራሳችሁ፡ የተሳሳተ ግንዛቤ እ—እንዳይኖራችሁ፡ በደንብ ልብ በሉ።

231 አሁን፡ "ሐሰተኛ ኢየሱስ፡" ተብለው መጠራት አይፈልጉም። "ኢየሱስ፡" ተብለው መጠራት፡ አይፈልጉም። በእርግጠኝነት፡ በጣም ግልጽ ነው። ማንኛውም ሰው ያውቀዋል። ሰው ሁሉ ኢየሱስ አለመሆናቸውን ያውቃል። በጀርባቸው ዘይት ቢኖራቸውም፡ በእጆቻቸው ላይ ደም ቢኖር እና ዓይኖቻቸውን ወደላይ-እና-ወደታች ቢያደርጉ አይገደኝም፡ በደንብ ያውቁታል... ጤናማ አስተሳሰብ ያለው ሰው፡ ኢየሱስ አለመሆናቸውን ያውቃል። እያችሁ? እነዚህ ሰዎች ያንን አይቀበሉትም። ሆኖም ራሳቸውን "የተቀቡ" ብለው ይጠራሉ። "የተመረጡትን እንኳ ለማሳት፡" ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ያደርጋሉ። "ነገር ግን ሐሰተኛ ክርስቶሶች፡ ማለትም የተቀቡ ሰዎች፡ ይነሣሉ፥ የሚቻል ቢሆን ኖሮ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።"

አሁን በጥንቃቄ ተከታተሉ። ይህ ሃሳብ እንዳያመልጣችሁ፡ ምክንያቱም መደመጥ የሚገባው ነው።

እሱ እዚህ ማይክሮፎን ላይ አንዳንድ ቴፕ እያስቀመጠ ነው፡ ወደ ላይ ከመብረር ለመጠበቅ። እያላበኝ ነበር፡ እና ቴፑ ላይ ተንጠባጥቧል፡ እያችሁ።

ስለዚህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው፡ እንደዛው ይሆናል። አያችሁ?

232 ልብ በሉ፡ ሐሰተኛ ኢየሱስን አይደለም። “ሐሰተኛ ክርስቶሶች!” የተቀቡ መሆናቸውን ቢያምኑም፡ ኢየሱስ እንዳልሆኑ ያውቃሉ። አያችሁ፡ በጣም ግልጽ ነው። ዛሬ አንድ ሰው ቀርቦ፡ “እጄ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች ተመልከቱ። ግንባሬ ላይ ያሉትን ደግሞ ተመልከቱ። እኔ ኢየሱስ ነኝ፡” ቢልስ። ይኸው፡ ወዲያውኑ፡ ሐሰት እንደሆነ እናውቃለን። እና፡ኢየሱስም እነዚህ ሰዎች ይመጣሉ አለማለቱን፡ አስታውሱ። “ሐሰተኛ ክርስቶሶች” ይመጣሉ ብሏል። “ክርስቶሶች፡” ብዙ ቁጥር፡ የሃይማኖት ተቋማት፡ እና የመሳሰሉት፡ **የተቀቡ ሰዎች** አለ፥ በቃሉ ሳይሆን፡ በሃይማኖታዊ መንፈስ የተቀቡ። እየተከታተላችሁ ነው? ሐሰተኛ ኢየሱስን አይደለም። “ሐሰተኛ ክርስቶሶችን፡” ሐሰተኞች፡ የተቀቡ ሰዎች። አያችሁ? አቤት፡ እንዴት ግልጽ ነው! እንዴት... በእርግጠኝነት ይህ አያመልጣችሁም!

233 አሁን፡ አስታውሱ፡ ሁሌም ሦስት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ነግሬያችኋለሁ። ሦስት የሰዎች የዘር ሐረጎች አሉ፥ ካም፡ ሴም፡ እና ያፌት፡ ሦስት ዘሮች ናቸው። ሦስት ክፍሎች አሉ፡ እነዚያም፡ እንደተናገርኩት አማኝ፡ አስመሣይ-አማኝ፡ እና የማያምን ናቸው። ሁሌም እንደዚያ ነበር፡ ሁሌም እንደዚያ ይሆናል። አያችሁ? ሙሴ፡ ከአማኝ ወገን ነበር፡ ያኔስና እና ኢያንበሬስ ደግሞ፡ ከማያምኑት ወገን ነበሩ። አያችሁ? በለዓምም ነበር፥ ሙሴ... ሁሌም ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ፡ ሦስት ዓይነት ማለት፡ አማኝ፡ አስመሣይ-አማኝ፡ እና እምነት አልባ።

234 አሁን አስታውሱ፡ እምነት አልባ፡ የሃይማኖት ተቋም ቤተክርስቲያን፡ በጭራሽ በምንም ዓይነት ምልክት የማታምን፣ ቀዝቃዛ፡ ተራ፡ ደንዳና፡ በዓለም ላይ ያለች ቤተክርስቲያን፡ የሃይማኖት ተቋም ነች። አስመሣይ-አማኝ ግን ቅርፊት ነው። አስመሣዩ-አማኝ ሰው ይህ አይነቱ ነው። እና ከዚያ እውነተኛ አማኝ አለ ይህም በጣም እውነት ነው። አሁን፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ፡ አብረው ሲሄዱ ተመልከቷቸው።

235 እና እምነት አልባዎቹ ምን ያህል ደፋሮች እንደሆኑ ተመልከቱ፣ ወይም እነዚህ አስመሳይ-አማኞች እና እምነት አልባዎቹ። አቤት! ደፋር ናቸው፡ ተመልከቱ፡ ልክ ሰይጣን በእውነተኛው ቃል መገኘት ፊት፡ እንደሚቆም፡ “ተብሎ ተጽፏል!” ልክ ነው?

236 ሰይጣን እንዲህ ያደረገው ለምንድን ነው? የዘመኑን ስለማያውቅ ነው... ቃሉ የዘመኑ ቃል እንደነበር ያውቅ ነበር፡ ይህ ትሑት ምስኪን ሰው ግን ያ ቃል እሱ መሆኑ ተጠራጠረ። “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ። የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚመጣ አውቃለሁ፡ ምክንያቱም እንደሚመጣ ተጽፏል። ደግሞም ‘እንዲጠብቁህ ስላንተ መላዕክትን ያዛቸዋል፡’ ተብሎ ተጽፏል። አያችሁ? አረጋግጥልኝ! አንድ ተአምር አድርግ! እስቲ ስታደርገው ልይህ።” አያችሁ? አያችሁ?

237 እምነት አልባው፡ አስመሣይ-አማኝ፡ ሲያስመስል እዩት። ይሁዳን ተመልከቱት በመካከላቸው፡ በተመሳሳይ ጊዜ፡ አስመሣይ-አማኝ! አያችሁ? ልብ በሉ፡ እውነተኛው ቃል ይህ ነበር።

238 ምን ያህል ደፋር ናቸው! “አሁን፡ እንዲህ አይነቱ ሞኝነት ትኩረት አትስጡት፡ ባዶ ነው። ወደዚያ አትሂዱ። ብዙ የማይጠቅም ጫጫታ ነው። ባዶ

ነው። ልብ ወለድ ብቻ ነው። በአእምሮአችሁ ውስጥ ነው።" አያችሁ፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ? በቃሉ ፊት ለፊት ቆሙ እና እንዲህ በሉት።

239 ሰይጣን በቀጥታ ገባ። መጽሐፍ ቅዱስ በይሁዳ ላይ እንደተናገረው፡ "የመላእክት አለቃ እንኳን ከሰይጣን ጋር፡ ሲከራከር፡ 'ጌታ ይገሥጽህ፡' አለው።" በቃሉ ላይ ይጻረራልና!

የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው፡ የተቀባ ይህ ነው፡ የዘመኑ እውነተኛው ቃል የሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመጻረር ቆመ፡ እና "ተብሎ ተጽፎአል፡" አለ።

240 በዘመኑ ፍጻሜ ላይ ተመልከቱ። "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስት ድረስ ነው።" ኦህ፡ ይገርማል! የተመረጡት የማይስቱበት ምክንያት፡ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ምክንያቱም እነሱ ራሳቸው ቃል ስለሆኑ ነው። አያችሁ? ልክ ቀደም ሲል እንደተናገርኩት፡ በሰሩ ውስጥ ያለው ሕይወት፡ ራሱን መካድ አይችልም። አያችሁ፡ ቃሉ ነው እና በቃሉ ወቅት ነው። ትክክል ነው።

241 እንደ ኤርምያስ፡ እርሱ አውቆታል። ሐናንያ ምንም ቢል፡ ሰፍራውን ያውቅ ነበር። ሙሴ እና—እና ሌሎቹም፡ እንዳደረጉት ሁሉ ያው ነው። ያም ማለት፡ ያውቃል፡ ሐሰተኛው ነቢይ ምንም ቢል፡ የእግዚአብሔር ቃል እንዳለ ያውቃል። ተብሎ ተጽፏል።

ሚክያስ "እሺ፡ እስኪ ጠብቁኝ እናያለን፡" ያላቸው በዚህ ምክንያት ነው።

242 አክዓብ "ድርጅቴ ትክክል ነው። ነቢያቶቼን አምናለሁ፡" አለ። በሰላም እስክመለስ ድረስ... ያንን ሰው ወደ እስር ቤት ወርውሩት። ያን ጊዜ አሳየዋለሁ! የመከራ እንጀራ ሰጡት። ዞር በል በሉት፡ ከእሱ ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት አታድርጉ። በሰላም በተመለስኩ ጊዜ፡ ያንን ሰው እናስተናግደዋለን።"

243 ሚክያስም "ብትመለስ፡ እግዚአብሔር በእኔ አልተናገረም፡" አለው። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እንደያዘ ያውቃል፡ ራእዩም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ከሚለው ጋር ይሰማማል፥ ለዚያ ወቅት እንጂ፡ ለሌላ ወቅት አይደለም። አሜን! ሃሌ ሉያ! ወቅቱ!

ደፋር ነው፡ ከመላእክት አለቃ ጋር ቆሞ ተከራከረ! በአባባል፡ "መላእክት ለመራመድ በሚፈሩበት ቦታ ሞኞች በታኮ ጫማ ይራመዳሉ፡" ይባላል። በትክክል።

244 ኢየሱስ እንደተናገረው፡ የተመረጡት ሰዎች፡ ሊታለሉ የማይችሉበት ምክንያት፡ እነሱ ቃል ስለሆኑ ነው። ሌላ ነገር መሆን አይችሉም፡ ሌላ ነገር መስማት አይችሉም። ሌላ ነገር ማወቅ አይችሉም። ትክክል ነው።

245 አስታውሱ፡ ሙሴ በእነዚህ ሰዎች አስመሳይነት አልደነገጠም። ደንግጧል'ዴ? ሙሴ እንዲህ አለ፡ "አሁን፡ ሰማኝ፡ ፈርዖን ሆይ። ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ጌታ ይህን አድርግ አለኝ፡ ነገር ግን፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ ሰዎችህም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ አይቻለሁ። ስለዚህ፡ ምን እንዳሰብኩ እነግርሃለሁ፡ እኔም ከእናንተ ጋር እቀላቀላለሁ"? ኧይ! እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔር ነቢይ አይደለም። በጭራሽ፡ አይደለም! የቻለውን ያህል ሁሉ ብቻውን ጸንቶ ቆመ። እግዚአብሔር በሆነ መንገድ፡ በትክክል፡ ነገሩን

እንደሚያስተናግድ ተረድቷል፡ ቃል ገብቶለታልና። “ከአንተ ጋር እሆናለሁ። አልተውህም።”

246 ስለሚያውቅ፡ ከእነሱ ጋር አልተቀላቀለም። ኧረ፡ በፍጹም። ከያዘው ጋር ጸና። ማንኛውም የሃይማኖት ተቋማቸው አልፈለገም። ከእግዚአብሔር ጋር ጸና። ማድረግ በቻሉት ነገር ሁሉ አልተማረከም። አንድ ነገር ባደረጉ ቁጥር... እርሱ ቅማል አመጣ፥ እነሱም ቅማል አመጡ። ደም አመጣ፡ እነሱም ደም አመጡ። ሁሉንም ነገር አመጣ፡ ሰር ሰሩን፡ በሁሉም መንገድ እርሱን አስመሰሉት። እሱ ጸንቶ ቆመ። በትክክል ያውቅ ነበር፡ ምን፡ እግዚአብሔር በሥራ ላይ መሆኑ።

247 አሁን ገብቷችኋል? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—እርታኢ።] ሁለት ጊዜ ሁለት፡ አራት አታገኙም ወይ? [“አሜን።”] ብዙ መጨነቅ አይጠበቅባችሁም። ስለዚህ፡ ስለዚህ—መረዳት ትችላላችሁ፡ አያችሁ።

ለምን? እውነተኛ አማኞች፡ በዚህ አይታለሉም፡ በዘመኑ የሚጸኑ አስቀድመው የተወሰኑ ዘር ናቸው።

248 ኢየሱስ፡ ደግሞ፡ እንዳለው፡ “በዚያን ቀን ብዙዎች፡ በሰሜ ይመጣሉ፡ እንዲህም ይሉኛል፡ ‘ጌታ ሆይ፡ በሰምህ አጋንንትን አላወጣሁምን? ’” ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “በመጨረሻው ዘመን፡ ጊዜው ሲጠናቀቅና ታላቁ ትንሣኤ ሲመጣ፡ ብዙዎች ይመጣሉ በመንግሥቱም ይቀመጣሉ።” የእግዚአሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት።

249 ብዙዎቹ፡ እንክርዳዶቹ ይመጡና ከሰንዴው ጋር አብረው ተቀምጠው፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ይኸውልህ፡ አሁን፡ ጌታ ሆይ! በልሳኖች ተናግሬአለሁ። ጮህኩኝ። በመንፈስ ጨፈርኩ። አጋንንትን አስወጥቻለሁ። በልሳኖች ተናግሬአለሁ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርጌአለሁ።”

ምን የሚል ይመስላችኋል? ልብ በሉ። “እናንተ ዓመፀኞች፡ ከቶ አላወቅኋችሁም።”

250 **ዓመጽ** ምንድን ነው? ማንም ሰው ጠይቁ። “ማድረግ እንዳለባችሁ አውቃችሁ፡ አለማድረግ ነው።” ቃሉን ታውቁታላችሁ። ሰምታችሁታል። ቴፑን እየሰማችሁት ነው። መልእክቱን እያዳመጣችሁ ነው። ጌታ አምላክ ሲናገር፡ ይህን ሲያረጋግጥ፡ እውነተኛ ሲያደርገው አይታችኋል። ፀሐይ ከውጭ እያበራ እንዳለ ያህል ግልጽ እንደሆነ ታውቁታላችሁ፡ ነገር ግን እናንተ ሃይማኖታችሁን አክርራችሁ የምትይዙ፡ እነዚያን የሐሰት ነገሮች አጥብቃችሁ የምትይዙ፡ እናንተ ዓመፀኞች ናችሁ!

“ኦህ፡ አዎን፡ በጣም ጥሩ ኮንፈረንሶች አዘጋጀሁ። **ይህንን** አድርጌያለሁ፡ **ያንን** አድርጌያለሁ።”

“እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ፡ ከቶ አላወቅኋችሁም፡” አላቸው።

251 “እንዴ፡ መንፈስ ቅዱስ’ኮ በእኔ ላይ ወርዷል።” እኔም በምንም አልጠራጠርም። “በልሳኖች እናገራለሁ። በመንፈስ እዘምራለሁ። ብዙ ነገር አደርጋለሁ... ” ምንም ጥያቄ የለውም። ትንሽም ቢሆን አልጠራጠርም። ኦህ፡ ወንድሜ፡ እኅቴ ሆይ፡ እንዴት ያለ ሁኔታ ነው!

ይህ የሚያስፈራ ጊዜ ነው፡ የት ላይ ነን? ይህ ቃል አሁን ወደ ሕይወት እየመጣ ነው። አስተውሉ።

252 አዎን፡ ይህን እንደሚያደርጉ ተናግሯል። ልብ በሉ፡ "እናንተ ዓመፀኞች።" እዚህ ላይ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለኝ። የት እንደነበር በትክክል አላውቅም ነበር። በጣም ብዙ ጊዜ ወሰዶብኛል። አንድ ደቂቃ ብቻ ሰጡኝ፡ ልፈልገው፡ እና ምን ነበር መሰላችሁ፡ አገኘሁት—አገኘሁት ማቴዎስ 7:21። ብቻ የት እንደሆነ አ—አላወቅኩም ነበር። አንዳንድ ጊዜ፡ የሆነ ነገር ላይ አልጽፍም፡ እንግዲህ፡ እንዲህ ሰ—ሰሰብክ፡ በቅዱስ ቃል ላይ የጠቀሰኩትን ነገር እ—ረሳሁት። ማቴዎስ 7:21።

> **በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፡ ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ የሚለኝ ሁሉ፥ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።**
>
> **በበዚያ ቀን ብዙዎች፡ ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ በሰምህ ትንቢት** አል**ተናገርንምን** ይሉኛል...

253 ነቢያቶች፡ የተቀቡ ሰዎች! ልክ ነው? "ነብይ አልነበርንምን? ቅቡዓን፡ ቅቡዕ አልነበርንምን? በሰምህ ትንቢት አልተናገርሁምን? በአንተም ሰም አጋንንትን አላወጣሁምን? " በኢየሱስ ሰም ለመጠመቅ ፈቃደኛ ሳትሆኑ ይህን ማድረግ የምትችሉት እንዴት ነው? እያችሁ? ኦህ፡ ይገርማል! እያችሁ እንዴት እንደሚያሰቱ? በቀጥታ ወደዚያ ነጥብ ይሄዳሉ፡ ከዚያም ወደ ኋላ ይመለሳሉ። በቀጥታ ወደ ቃሉ ይሄዱና፡ ከዚያም ወደ ኋላ ይመለሳሉ። አሁን ይህን ተመልከቱ፡ ከአንድ ደቂቃ በኋላ፡ እናየዋለን።

> **ብዙዎች፡ ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ**... ትንቢት አልተናገርንምን፡ ነቢያት አልነበርንምን? **ይሉኛል**...

አዎn፡ በማቴዎስ 24:24 ላይ ሰለዚህ ጉዳይ ተናግሬያለሁ።

> ... **ሰምህም**... **አጋንንትን አላወጣንምን**? **በሰምህም ብዙ ተአምራትን** አላደረግንምን-... ብዙ **ሰራዎች?**
>
> **የዚያን ጊዜም፡ ከቶ አላወቅኋችሁም፡ እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ** ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።

254 "በፊታችሁ በተቀመጠና ባያችሁት ጊዜ፡ ሲሰራ አይታችኋል፡ ቃሉ መሆኑን አይታችኋል፡ ሰለ ሃይማኖት ተቋማችሁ ግን፡ በተቋም ተጣብቃችሁ ቀራችሁ። በፍጹም አላውቃችሁም። ምንም ያህል አጋንንት ብታሰወጣ፡ ምንም ያህል **ይህንና ያንን** ብታደርግ ግድ የለኝም፥ ሰለ አንተ ምንም የማውቀው ነገር የለም።"

በለዓምም "በሰምህ፡ ትንቢት ተናገርሁ፡ ተፈጸመ፡" ብሏልና።

"ያ ትክክል ነው፡ ነገር ግን፡ ወደ ቃሉ ሲመጣ፡ እምቢ ብለኸዋል።"

255 ወንድሜ ሆይ፡ አሳቹ ክፍል፡ ይታይሃልን? በትክክል "በነቢይ፡" ሳይሆን፡ ግን በቃሉ፡ በእውነተኛው ቃል፡ በተገለጠው ንጹህ ቃል። "እናንተ ዓመፀኞች!"

ሰይጣን በታሪክ ዘመናት ሁሉ እውነተኛውን ቃል ለማስመሰል፡ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ይህን እናውቃለን፡ አይደል?

256 ልብ በሉ፡ ድንበር ድረሰ ይመጣል ግን ያቋርጣል። እዚህ ላይ ተመልከቱ፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 6 ላይ፡ እንዲህ አለ (ይህ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት

እያነበብነው ነበረ፡ በሚቀጥሉት ደቂቃዎች፡ "እንመለስበታለን፡" ብያችሁ ነበር።)፡ እንዲህ አለ፦

> … **እሾህና** ኩርንችትን ግን ብታወጣ ግን… **የተጣለች ናት** ለመረገምም **ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።** (ድንበር!)

> **… የሰማያዊውን ስጦታ… የቀመሳ**ችሁ፡…

257 "ቀምሳችሁ፡" በሌላ አባባል፡ አይታችሁታል! አይ [ወንድም ብራናም ከንፈሮቹን አሰጮኸ—አርታኢ።] በቃ በአፋችሁ ቀምሳችኋል። አይታችሁታል፡ እውነትም መሆኑንም አውቃችኋል። እውነት መሆኑን ታውቁት ነበር። "ሰማያዊው ሰጦታ ቀምሳችሁታል።"

> … እና በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ **ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆናችኋል፡**

> **… የእግዚአብሔርን መልካም ቃል ቀምሳችኋል፡…**

"ቀምሳችሁ፡" ትክክል እንደነበር አይታችኋል። "መንፈስ ቅዱስም በእናንተ ላይ ወረደ፡" የማሳ ውስጥ እንክርዳድ።

> … ከዚያም **ካዳችሁ፡…**

"የተቀደሳችሁን፡ የጠራችሁንና ቅባቱን ያፈሰሰባችሁን፡ እውነተኛውን ክርስቶስን ካዳችሁ።"

> … ከእንግዲህ፡ **ለኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አይኖርም።**

ይቅር የማይባል ነው! "ለእነርሱ እውነትን ወደ ማወቅ መምጣት ፈጽሞ የማይቻል ነው።"

> የመንፈስ **ቅዱስ ተካፋዮች ሆነው ለነበሩት… ይህ የማይቻል ነውና፡**

258 እንክርዳድ ላይ ይዘንባል፡ እያችሁ፡ "ከኢየሱስ ጋር ይጀምራሉ፡ እና፡ 'ጌታ ሆይ፡ እቀጥላለሁ፡'" ቃሉ ሲጠቀስ ግን፡ ወደ ኋላ ትመለሳላችሁ። "የመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ተደርገዋል፡ እንዲያውም ቃሉን ቀምሰውታል፡ ወይም ቃሉ ሲገለጥ አይተዋል።" ከዚያም ከእርሱ ፈቀቅ ይላሉ፡ "ፈጽሞ አይመለከቱትም ወደ እርሱም አይቀርቡም።"

259 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይላልና። አሁን፡ እናንተ… "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ እኔ ግን በፍጹም።" እያችሁት? "በፍጹም አይቻልም።" መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይላልና፡ መንፈስም ይመሰክራል።

260 ልብ በሉ፡ እስቲ አንድ ትንሽ ምሳሌ ልስጣችሁ። በሙሴ ትንቢት መሠረት የመጡትን ሰዎች ተመልከቱ፡ በትንቢቱ መሠረት፡ ከድርጅቱና፡ ከማንኛውም ነገር መጡ፡ ታላላቅ ስራዎችን፡ ድንቆችንና የመሳሰሉትን ነገሮች ተመለከቱ፡ ወደ ውስጥ ለመግባትም ድንበር ላይ ደረሱ።

261 አሁን፡ ሊ፡ የአንተ ነገር "በመጽሐፉ ላይ ስላለው ስም፡" እነሆ። አየህ? ይሄን አስተካክለሃልና። እናንተ እዚህ የሌላችሁ፡ በመገናኛው-ዘዴ ላይ ያላችሁ—ሰዎች፡ ይህ እዚህ ለተቀመጠው ዶክተር ሊ ቨይልን ነው። ሰባቱን የቤተክርስቲያን ዘመናት የሚገልፀውን መጽሐፍ ሰዋሰው እያስተካከለ ነው።

“ከበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ስምህ ተሰረዘ፡” የሚለው ችግር፡ ወይም ጥያቄ ተነሣ። አያችሁ፡ ብዙ አገልጋዮችን ግራ አጋባ። ብቻ መጽሐፉን እስክታገኙ ድረስ ጠብቁ፡ ከእናንተ መካከል በውስጡ ትንሽ ብርሃን ያለው ሰው መረዳት ይችላል። አያችሁ?

262 ልብ በሉ፡ አሁን፡ ማየት ካልፈለጋችሁ ራሳችሁን ታዞራላችሁ አትመለከቱትምም። “ከቀይ ስር ደም ማግኘት አይቻልም፡ በውስጡ ደም የለምና፡” ትለን ነበር እናቴ።

263 ልብ በሉ፡ ብርሃኑ ይመጣል፡ ጨለማ ውስጥ አይደለም። ብርሃኑ ወደ ጨለማ ይመጣል፡ ጨለማውም አይቀበለውም። በዚህ ጊዜ የተቀቡትን ሰዎች ልብ በሏቸው።

264 ይህም ሙሴ እነዚያን የእስራኤል ልጆች እንዳወጣቸው ሁሉ፡ እነሱም ሰምተውታል ይሁን እንጂ ከዚያ ከታላቋ ሀገር ጋር ተጋጭቶባቸዋል። አሁን፡ እስራኤል ልዩ ልዩ ተቋማት በአንድ ላይ ነበረች። የራሷ መሬት፡ የራሷ ቤትም አልነበራትም። ወደ ቤት ጉዞ ላይ ነበረች።

265 እኛም ቤተክርስቲያን የለንም። ወደ ቤተክርስቲያን እየሄድን ነው፡ ወደ ቦክራት ልጅ ቤተክርስቲያን ጉዞ—ላይ... ነን፡ ከሰው ዘንድ የሆነች፡ ምድራዊት ቤተክርስቲያን ሳትሆን፡ በክብር ውስጥ ያለች ቤተክርስቲያን። አያችሁ፡ ወደ ቤታቸው በጉዞ ላይ ያሉ፡ የተጠሩት-ሰዎች፡ በክብር ያለችው ቤተክርስቲያን፡ በዘላለም ሕይወት የተወሰኑ ሰዎች።

266 ወደ ማዶ ለመሻገር ወደ ቦታው በደረሱ ጊዜ፡ ቃሉን ተጠራጠሩና፡ ወደኋላ ተመለሱ። ኢያሱ ካሌብና አብረዋቸው የነበሩት ሰዎች ምድሪቱ መኖሯን ለማረጋገጥ ሄደው፡ የእግዚአብሔር የቃሉ ኪዳን የሆነውን፡ “ወተት እና ማር ያላት፡ መልካም ምድር ናት፡” የሚለውን የወይን ፍሬ ይዘው ከተመለሱ በኋላ። እና እንዲያረጋግጡላቸውም፡ በዚህ በኩል፡ ይዘው መጡ። እነሱም ቀምሰው፡ “ኧረ፡ ኧረ፡ ቢሆንም፡ አንችላቸውም፡” አሉ።

267 ከዚያ ምን ሆነ? ምድረ በዳው ላይ ጠፉ። በዚያው ቆመው ራሳቸውን አደራጁ፡ እና እያንዳንዳቸውም፡ ሞቱ፡ ነገር ግን ወደ ባሕሩ ተሻግረው ያመጧቸው፡ ኢያሱና ካሌብ ነበሩ፥ ሙሴ ግን ተወሰደ። እርሱም ቤተክርስቲያኗን የመጠባበቅ፡ የብሉይ ኪዳን ትንሣኤ፡ የአዲስ ኪዳን፡ እና የተነጠቀው አካል ምሳሌ ነው። እነዚያን ሦስት ሰዎች አያችሁ? እነዚህ ሦስት ሰዎች መስመር ውስጥ መከፋፈል ይቻላል፡ አያችሁ፡ ስለዚህ፡ አማኝ እና የማያምን በማለት። አያችሁ?

268 እግዚአብሔር ያንን ኃጢአት “በጭራሽ።” ይቅር እንዳላለው፡ አስታውሱ። አሁን እንዴት ሊገቡ ይችላሉ? መጀመሪያ ላይ፡ እሾህ ከሆነ፡ መጨረሻ ላይ እሾህ ይሆናል። የተመረጡት ብቻ ያዩታል።

269 አሁን በጥንቃቄ ተከታተሉ። ልክ ከጨለማው ዘመን በፊት፡ ትንሹ የእግዚአብሔር ሰው፡ ቅዱስ ማርቲን ነበር። ስንቶቻችሁ የቅዱስ ማርቲን ጽሑፎችን አንብባችኋል? ብዙዎቻችሁ ኣንብባችኋል። የቅዱስ ማርቲን ጽሑፎችን ለመግኘት ሄደን ነበር፡ ቄሱም፡ “ነገር ግን ቀኖና አልተደረገም” አሉን። እርግጥ ነው፡ በእነርሱ ዘንድ፡ አልተደረገም፡ በእግዚአብሔር እንጂ።

መንፈስ ቅዱስ በሦስተኛዋ የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ እንድናስቀምጠው ነግሮናልና። አያችሁ?

270 እንዴት ያለ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበር ተመልከቱ፡ የተጠራ፡ የተወሰነ። ወላጆቹ፡ አረማውያን ናቸው። አባቱ፡ ወታደር ነው። የአባቱን ፈለግ ለመከተል፡ ወታደር ሆነ። እና፡ በሆነም ጊዜ፡ እና ሁል ጊዜ አምላክ አንድ ቦታ አለ ብሎ ያምን ነበር፥ የጫካ ሰው ሲሆን፡ እግዚአብሔርን ግን ማየት ቻለ። አንድ ቀን በአንድ ከተማ አጠገብ እያለፈ፡ አንድ ሽማግሌ ለማኝ በዚያ ተኝቶ ነበር፡ ሞት አፋፍ ላይ ነበር፡ እርዳታ እየጠየቀ… በዚያ ምሽት ብርድ ነበርና። "ኦህ፡" እንዲህ አለ፡ "ልብስ ነገር ስጡኝ፡ ዛሬ ማታ ልሞት ነው" ይል ነበር።

271 ማንም ሰው ያን አላደረገለትም። እና ማርቲን ወደ አንድ ጎን ተቀምጦ ለተወሰነ ጊዜ እያየው ቆየ። ማንም አላደረገለትም ነበር። አንድ ካፖርት ብቻ ነበረችው። ያን ካፖርት—ከሰጠው፡ ለራሱም ግዳጅ ላይ ስለነበረ፡ እሱ ራሱ፡ በጣም ሊበርደው ይችላል። በመሆኑም "ከእሱ ጋር ካካፈልኩት ሁለታችንም በሕይወት የመኖር እድል አለን፡" ብሎ አሰበ። ስለዚህ የራሱን ካፖርት ወሰደ፡ በሰይፉ ለሁለት ከፈለውና ሽማግሌውን ለማኝ ሸፈነው። የተቀረውን ግማሽ ለራሱ ለበሰ።

ሁሉም ሰው እንዲህ አለ፡ "ተመልከቱት እንዴት ያለ አሰቂኝ-ታጣቂ ነው፡ እንዴት ያለ አሰቂኝ-ወታደር ነው፡ ግማሽ ካፖርት የለበሰ!"

272 በቀጣዩ ምሽት፡ ከግዳጅ ወጥቶ አልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ፡ ከእንቅልፉ ነቃ። በዚያ ክፍል ውስጥ አየ፡ እነሆ ኢየሱስ ክርስቶስን ቆሞ፡ አየው እርሱም በግማሿ ካፖርት እንደተጠቀለለ ነበር። ወዲያውኑ አወቀው፡ "ለእነዚህ የራሴ ለሆኑት ለታናናሾች፡ ለቀቧኋቸው ያደረጋችሁት ሁሉ፡ ለእኔ አደረጋችሁት፡" ተኝቶ ነበር።

273 ታላቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር። ቤተክርስቲያን ሳቀችበት፡ አሳደደችው፡ አባረረችው፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ አደረገችበት፡ እርሱ ግን የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር። የተናገረው ነገር ተፈጸመ። በዚያ ዘመንም እሱን ያመኑት ብዙ ሰዎችም፡ ነበሩ።

274 ዲያብሎስ እንዴት ማታለል እንደሚችል ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። አንድ ቀን በክፍል ውስጥ እያጠና ነበር። በራሱ ላይ አክሊል የነበረው፡ ኃያል መልአክ መጣ፡ በእግሩ የወርቅ ጫማ፡ በልብሱ ዙሪያ የወርቅ ጥለት ለብሶ መጥቶ፡ እንዲህ አለው፡ "ማርቲን፡ እኔን ታውቀኛለህ? " እንዲህ አለው፡ "እኔ ጌታህና አዳኝህ ነኝ። ያዳንኩህ እኔ ነኝ። ማርቲን፡ አምልከኝ።" ነገር ግን ይህ ነቢይ፡ ትንሽ እንግዳ ነገር እንዳለ በማወቁ፡ እሱን መመልከቱን ቀጠለ። እንዲህ አለው፡ "ማርቲን ሆይ፡ እኔ አዳኝህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። አምልከኝ! ማርቲን፡ አታውቀኝም? "

275 ማርቲን የቅዱሳን መጻሕፍት ጥቅስ፡ በአዕምሮው ውስጥ ተመላለሰበት። "ሰይጣን ሆይ፡ ከእኔ ራቅ፡" አለው። "አንተ በራስህ ላይ አክሊል አለ። የእግዚአብሔር ቃል ግን 'ቅዱሳኑ በዘመኑ መጨረሻ አክሊል ያለብሱታል' ይላል፡" አለው።

ይህ ለጴንጤቆስጤ ማታለያ አይሆንም ነበር? ቃሉን ተጠንቀቁ፡ ወንድም። እዚህ ጋር ነው ዋጋው።

276 አንድ ቀን፡ በድጋሚ፡ በገዳም ውስጥ፡ እና ጥቂት ወጣት መነኲሳት ዘንድ፡ አንድ ቅዱስ ሽማግሌ ነበሩ። ከመካከላቸው አንዱ ትንሽ ቁጡ ነበር። ይህንን ተመልከቱ፡ ይህ ጥሩ—ጥሩ ምሳሌ ነው። ከሌሎቹ በላይ የሆነ ነገር መሆን ፈልጐ ነበር። ራሱን ባለሥልጣን፡ ትልቅ፡ የተሻለ፡ አድርጎ ለማሳየት ፈልጐ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ባለ ሁሉም ዓይነት ደረጃ፡ እና የሆነ ትልቅ ነገር። የተለየ መሆን ፈለገ። በሌሎች ወንድሞች ሁሉ ይህ አይፈልግም... ታውቃላችሁ፡ የተለየ መሆን ፈለገ። አያችሁ? እሱ፡ ምንም ይሁን ምን፡ በጣም እብሪተኛ ነበር። ለብቻው የተለየ አትኩሮት የሚሻ ሰው ነበር። ማንም ሊነካው አይችልም። አሁን ምን እንደተከሰተ ተመልከቱ። ትልቅ ነገር ነበረበት። ከትላልቅ—ማህበረሰብ ጋር የሚወዳደር ነበረ። እየተከታተላችሁኝ ነው? አያችሁ? ስለዚህ፡ ተናገረ፡ ትንቢት ተናገረ። "እግዚአብሔር፡ እኔንም፡ ነቢይ አደረገኝ። እኔም ነቢይ ነኝ" አለ።

አሁን፡ በአገሪቱ ውስጥ አንድ የተገለጠ ነቢይ ነበር፡ ያም ቅዱስ ማርቲን ነበር፡ ነቢይ ሆኖ ተወለደ።

277 ይህ ልጅ ግን እንዲህ አለ፡ ወጣቱ ሰው እንዲህ አለ፡ ሀያ-አምስት ዓመት ገደማ የሚሆነው ወጣት መነኩሴ፡ እንዲህ አለ፡ "ጌታ ነቢይ አድርጎኛል፡ እናም ይህን አረጋግጥላችኋለሁ።" እንዲህ አለ፡ "ጌታ ዛሬ ማታ ትልቅና፡ ጥሩ ካባ፡ ይሰጠኛል፡ ነጭ ካባ ያለብሰኛል፡ በመካከላችሁም ያሰቀምጠኛል። ከዚያም ሁላችሁ ወደ እኔ ትቀርባላችሁ፡ ታያላችሁ፡ ትእዛዜንም ትቀበላላችሁ።"

አሁን ያንን ከዛሬ ጋር አወዳድሩት፡ አያችሁ፡ "የድርጅቱ መሪ እኔ እሆናለሁ። ሌሎቻችሁን መነኲሳት፡ እመራችኋለሁ።"

278 እና በእርግጠኝነት፡ "በዚያ ምሽት፡ በሕንፃው ውስጥ መብራቶች መጡ፡" የቅዱስ ማርቲን ጽሑፍ ይናገራል። አንብቡት። የተረጋገጠ ነው። ታሪክ ነው። እና መብራቶች መጡ፡ ሁሉም ተመለከቱት፡ እነሆም... ነጭ ካባ ለብሶ፡ በመካከላቸው ቆሞ ነበር። "የነገርኳችሁን አያችሁ? " አላቸው፡ ያ ግን ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነው።

279 እናም ሄዶ የኮሌጁን ዲን ሲያገኘው፡ ዲኑ ትንሽ ወደላይ-እና-ወደታች ከተንጎራደደ በኋላ፡ "ልጄ ሆይ፡ ያ ልክ አይደለም፡" አለው። እንዲህ አለው፡ "አንድ መንገድ ብቻ አለ።" እሱም ይህ ነው! "ይህን ማወቅ የምንችልበት መንገድ አንድ አለ። ከተፈጥሮ በላይ ይመስላል።" ልጄ ሆይ፡ በጴንጤቆስጤም ያንን ዘንድ በኖረ ነበር፡ ሥሩን፡ ማጥመጃውን፡ ገመዱን፡ መንጠቆውንና፡ ሌሎቹን ነገሮች ሁሉ! አለውም፡ "ተአምራቱ መልካም ቢመስልም፡ ከቃሉ ጋር ግን በትክክል አይመስለውም። አሁንም፡ እንዲህ ያለ ሰው፡ ማርቲን የሚባል፡ የተቀባ ነቢይ አለን። ና፡ ወደሱ እንሂድ።"

ሰውየውም "አይ፡ አይ! ማርቲን ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡" አለ።

"ምንም ይሁን፡ መሄድህ አይቀር፡" አሉትና። ማርቲን ፊት እሱን ለመውሰድ፡ እጁን ይዘው ሲጎትቱት፡ ካባው ከእርሱ ወደቀ።

አያችሁ፡ "ቢቻል ኖሮ የተመረጡትንም እንኳ እስከሚያስቱ።" አያችሁ፡ ያውቋቸዋል። ኢየሱስም "በጎቼ ቃሌን ያውቃሉ፡" ብሏል።

"ኦህ፡" "'**ድምፄን** ይሰማሉ፡"' አልህን።

280 ቃሉ ነው። “ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።” አያችሁ? የተመረጡት ይህን ያውቃሉ። “እንግዳ ቃል፡ ወይም እንግዳ ድምፅ፡ አይከተሉም።”

281 ያኔ የነበሩት ሰዎችም እንዲህ ናቸው፡ አይከተሉም ነበር። ማርቲን እንዳለ ያውቁ ነበር፡ በዚያ ዘመን የነበረው ነቢይ፡ እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ለይቶ ያወቀው፡ ቃሉን የሚያውቅ ነበር። ያም ሰው በፊቱ መቆም አልፈለገም።

282 በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፡ “ሰጋ ባለበት፡” ወይም ቃሉ ባለበት፡ “በዚያ፡ በወቅቱ፡ ንስሮች ይሰበሰባሉ።” አሁን ይህ-... ይህን መጻፍ ትፈልጋላችሁ፡ ማቴ 24፡28 ነው። ከዚህ ትንሽ ቀደም ብሎ፡ ማቴዎስ 24፡24፣ ከአራት ቁጥሮች በታች፡ ለመረዳት ከፈለጋችሁ፡ ተመልከቱ። “ሰጋ ባለበት፡” መናውም ባለበት፡ ቃሉም ባለበት፡ “በዚያም ንስሮች ይሰበሰባሉ።”

283 አሁን መፍጠን አለብኝ። ወደ ላይ ተመለከትኩና ስንት ሰዓት እንደሆነ አየሁ... አ—አሰራ ሁለት ከሰባት ወይም ሰምንት ደቂቃ ነው። በጣም እፈጥናለሁ፡ ወይም ዛሬ ማታ ማጠናቀቅ አንችላለን፡ እንደተመቻችሁ። ዛሬ ጠዋት ወይም ዛሬ ማታ? አይደል? ሰንቶቻችሁ ዛሬ ከአገልግሎት በኋላ ወደ ቤት መሄድ አለባችሁ፡ እጃችሁን እንመልከት፡ አያችሁ። ኦህ፡ ይገርማል፡ ብንቀጥል ይሻላል!

284 በእነዚህ ሰልኮች ላይ ያሉትን ሰዎች በዚህ መንገድ በማቆየቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡ ግን እፈጥናለሁ። ከገንዘባችሁ የበለጠ ዋጋ አለው። አያችሁ፡ ለእኔ፡ እንደዛ ነው። ገንዘባችሁ ይጠፋል። ይህ ግን አይጠፋም፥ ቃሉ ነው። አያችሁ?

285 “ሰጋ ባለበት፡ በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ።” ሰጋው ባለበት፡ እ—እ—እርድ በተፈጸመበት፡ በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ። ትኩስ ሥጋ ባለበት፡ ወቅታዊ ቃል ባለበት፡ በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ።

286 ከበሰበሰ በኋላ ግን፡ አሞራዎቹ ወደ እሱ ይጐርፋሉ። አዎን። ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ? እርድ ሲፈጸም፡ ንስሮች ይመጣሉ፡ ከተጣለ በኋላ ግን፡ ከተበላሸ በኋላ፡ አሞራዎች ይመጣሉ። ንስር ከዚህኛው ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አያችሁ?

287 ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ሰጋ ባለበት፡” መና በወረደበት፡ ትኩሱ መና የወረደ ለታ፡ “በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ።” ያም ለዘመኑ የተሰጠ መና ነው። አያችሁ? ልብ በሉ።

288 ከበሰበሰ በኋላ ግን፡ ትሎች በውስጡ ይገባሉ፡ ከዚያም አሞራዎች ይመጣሉ። እስኪበሰብ ድረስ ሊያሸቱት አይችሉም። ኢየሱስ ቆሞ “ኢየሩሳሌም ሆይ፡ ነቢያትን ሁሉ በድንጋይ የወገርሽ!” ማለቱ አይደንቅም፡ ያን ተውላጠ ሰም ልብ በሉ፡ “ኢየሩሳሌም፡ ኢየሩሳሌም፡ ምን ያህል ጊዜ... ” እርሱ ማን ነበር? “ወደ እናንተ የላክሁትን ነቢይ ሁሉ በድንጋይ የገደላችኹ ሆይ፥ ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትሰበስብ ስንት ጊዜ ልሰበሰባችሁ ፈለግሁ፡” ታላቂቱ ቤተክርስቲያን፡ ኢየሩሳሌም።

289 ምድራዊ ያይደለች ኢየሩሳሌም፡ “ከላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን ነን፡” ቃሉ የመጣው፡ አስቀድሞ ከመወሰን ነው፡ አያችሁ። የሚጠፋው አሮጌው ኢየሩሳሌም

ሳይሆን፥ ሊጠፋ የማይችለው አዲሱ ኢየሩሳሌም ነው። በሰው እጅ የተገነባች፡ አሮጌዋ ኢየሩሳሌም አይደለችም፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር የተገነባች አዲሲቱን ኢየሩሳሌም፡ አያችሁ፡ እነሆ ቃሉ ከላይ አሁን ተገለጠ። "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ። እኔ እሄዳለሁ ሄጄም ለእናንተ አዘጋጅላችኋለሁ፡" ፈጣሪው የወርቅ ጎዳናዎችን፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮችን ያዘጋጃል። ያ የማይጠፋው ነው።

290 "ኢየሩሳሌም፡ ኢየሩሳሌም፡ ምን ያህል ጊዜ፡" ገና ከጊዜ መጀመሪያ እንሥቶ፥ ሦስተኛ አካል፡ ወይም፡ ሌላ ሰው ሳይሆን፡ "እኔ ራሴ ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትሰበስብ ልሰበስብሽ ፈለግሁ፡ አንቺ ግን አልፈቀድሽም። አሁን ግን ጊዜሽ ደርሷል።" አያችሁ?

"ሰጋው ባለበት፡ በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ።" ሰጋው ከበሰበሰ በኋላ ግን፡ አሞራዎች ይሰበሰባሉ። አያችሁ?

291 ልብ በሉ፡ ሙሴ፡ ለእግዚአብሔርን ልጆች የሰጣቸው... ሙሴ ንስር ነበር፡ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ልጆች የኖኅን ትርፍራፊዎችን በጭራሽ አልሰጣቸውም። አያችሁ? ትኩስ የእግዚአብሔር ቃል ይዞ ነበርና። "ጌታ አምላክ በምድረ በዳ ተገናኘኝ፡ ቃሉንም አረጋገጠልኝ፡ ወደዚህ እንድመጣ እናንተን እንዳወጣችሁ ልኮኛል።" ከዚያም በዙሪያው፡ አስመሳዮች እያስምሰሉ መጡ። አያችሁ? እርሱ ግን የዘመኑ ቃል ይዞ ነበረ።

292 ምክኒያቱም፡ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃል የገባለትን አብርሃምን፡ እንዲህ ብሎታልና፡ "ዘርህ በባዕድ አገር፡ አራት መቶ ዓመት ይኖራል፡ እኔ ግን እጎበኛቸዋለሁ በጽኑ እጅም አወጣቸዋለሁ።"

ሙሴም፡ "አሁን፡ ጌታ እግዚአብሔር ይናገረኛል ያሳየኛልም፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝም ነግሮኛል፡ እኔም እነግራችኋለሁ።" "'እኔ ነኝ' ልኮኛልና፡" አላቸው።

293 "እኔ ነኝ!" እንጂ "የነበርኩ፡ ወይም የሚኖር፡" አይደልም። "እኔ ነኝ፡" በአሁኑ ጊዜ፡ አሁን የሚለው ቃል ነው። የነበረው ቃል፡ የሚመጣው ቃል ሳይሆን፡ አሁን ያለው ቃል... አያችሁ? ገብቷችኋል? "እኔ ነኝ!" "እኔ ነኝ" ቃል ነው። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።" ልክ ነው? "እኔ ነኝ።" "ይህ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፡ እግዚአብሔር ነቢይ አድርጎ ላከኝ። እኔ የዚህ ቃል መልስ ነኝ፡ ወደዚህ ወርደህ ይህን አድርግ አለኝ።"

ያንን ባደረገ ጊዜ፡ ፈርዖንም እንዲህ አለ፡ "እንግዲህ፡ በእኛ ዘንድም ይህን ማድረግ የሚችሉ ብዙ ወንዶች ልጆችም፡ አሉን፡" አስመሳዮች።

294 ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ "አሁን፡ በመጨረሻዎቹ ቀኖች እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንደገና ይከሰታል፡" አያችሁ፡ ተመሳሳይ ነገር እየፈለገ ነው። ቀድሞ ማን እንደወረደ ተመልከቱ። ከቃሉ ጋር ማን እንደ ጸና ተመልከቱ። ያ ነው። የሚታወቀበት መንገድ ይህ ነው።

295 ስለዚህ፡ ታያላችሁ፡ ሙሴ ለኖኅ ዘመን የነበረውን እንዳልሰጣቸው፡ እናስተውላለን፡ "አሁን መርከብ እንሠራለን፡ ታውቃላችሁ፡ ቃል ይህ ነው። ኖኅ አንድ ቀን መርከብ ሠርቷልና።" አይ፡ አሞራዎችም በዚያ ሲመገቡ ነበር። አይ። አይ።

ይህ ቃል የተሰፋ ቃል ነው። አስተውሉ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን መልእክት፡ ለዘምኑ አስቀድሞ የተወሰነው እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነበረው።

296 ኢየሱስም ቢሆን ከሙሴ የተረፈውን አልሰጣቸውም። ሙሴ የዘመን ቃል ነበረው፡ ሙሴ ግን ነቢይ ነው። እዚህ ጋር እግዚአብሔር ራሱ ነው፡ ተመልከቱ፡ እርሱ ከሙሴ—ከሙሴ የተረፈውን በጭራሽ ሰጥቶ አያውቅም።

በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን አሞራዎች ግን እዩአቸው፡ በላዩ ላይ ሰፍረው ነበር። "እናውቃለን! ሙሴን አለልን! አንተ አታስፈልገንም።"

እርሱም "ሙሴ ስለ እኔ ተናግሮአልና፡ ሙሴን ብታውቁት፡ እኔን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር፡" አላቸው። አያችሁ?

297 "ስጋ በሚገኝበት በዚያ፡ ንስሮች ይሰበሰባሉ።" ንስሮች ሆይ! የቃሉ ትኩስ እርድ፡ ያደገና እና የሰባ ቃል፡ የተገለጠና ለልጆች ምግብ እንዲሆን የተሰጠ ነው።

አሁን፡ በመቶዎች ለሚቈጠሩ ዓመታት ወድቆ የቆየ ያረጀ ያን ስጋ፡ በዚያም ይሆንላቸዋል።

298 አሁንም ያው ነው! ሉተር የንስሓን መልእክት አመጣ፡ እናንተ ግን፡ የሉተራን ጥንብ አንሳዎች! ባፕቲስት መልእክት አመጣ፡ እናንተ ግን፡ የባፕቲስት ጥንብ አንሳዎች! አያችሁ? ጴንጤቆስጤው መልእክት አመጣ፡ አሁን እየመጣ ነው፡ የጴንጤቆስጤ ጥንብ አንሳዎች!

"ስጋ ባለበት በዚያ ግን፡ ንስሮች ይሰበሰባሉ።"

አስታውሱ፡ በዚያን ዘመን አንድን ሉተራን፡ ይህን የካቶሊክ ብስባሽ አታበሉትም፡ (አሁን ትችላላችሁ)። በጭራሽ፡ ወዳጄ። ትኩስ ሥጋ ነበረው። ይህም የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነበር።

299 ሜቶዲስቶችን፡ የሉተራን መልእክት መመገብ አይቻልም። ኦህ፡ አይቻልም፡ ያንን ብስባሽ አይፈልጉም። ተልቷልና። አያችሁ፡ ሕይወት ተለይቶት ወደ ሌላ ነገር ተቀይሯል። ያኔ ድሮ፡ የሞተው ያረጀ ግንድ ነው። ሕይወቱ ወጥቶ እየተጓዘ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራም ጴንጤቆስጣዊነትን ልትመግቧት አትችሉም። በጭራሽ፡ አትችሉም! ትል-ያፈነዳቸው ድርጅቶች፡ ለምንም አይጠቅሙም! አይ፡ አይ!

300 የተሰፋው ቃል፡ "ታላቁና የሚያስፈራው ቀን ከመምጣቱ በፊት፡ ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ። እሱም የልጆቹንም ልብ ወደ አባቶቻቸው እምነት ይመልሳል።" "እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጡ ተሰፋዎች ሁሉ፡ እኔ አደርገዋለሁ፡ በዚያም ንስሮች ይሰበሰባሉ።" "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።" አያችሁ?

301 ኢየሱስ ያንን በጭራሽ አልሞከረውም። ኢየሱስ ሲመጣ ግን፡ "ሙሴንና ሕጉ አለልን፡" ባዮች የአሞሮች መንጋ ገጠሙት። አያችሁ? እሺ፡ በዚያ በታረደበት ወቅት እንዲበሉ ለእነርሱ መስጠቱ መልካም ነበረ። አያችሁ፡ ያኔ ችግር አልነበረውም።

302 ይሁን እንጂ መሥዋዕቱን ያረደው ሙሴ፡ ራሱ፡ እንዲህ ተንብዮ ነበር፡ እንዲህ በማለት፡ “እግዚአብሔር አምላክ፡ ከወንድሞቻችሁ መካከል፡ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል። እንዲህም ይሆናል፡ ነቢዩንና የሚናገረውን የማይሰማ ማንም ቢኖር፡ የማይቀበለው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጠፋል።” እንደዛም ሆነ።

303 ከብሉይ ኪዳን፡ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደ ስድስት መቶ የሚጠጉ የተለያዩ ትንቢቶች እንዴት እንደተፈጸሙ ተመልከቱ። “እጆቼንና እግሮቼን ወጉ።” በሕይወቱ የመጨርሻዎቹ ሰባት ወይም ሰምንት ሰዓታት ውስጥ፡ ምን ያህሉ እንደተፈጸሙ ረሳሁ፡ ነቢያት ሁሉ በትክክል፡ ተናግረዋል።

304 የዛሬ አንድ ዓመት አንዳች ነገር እንደሚከሰት ዛሬ ትንቢት ብናገር፡ ምናልባት ት—ትክክልም ሆነ ስሕተት፡ የመፈጸሙ ሀያ በመቶ እድል ሊኖረኝ ይችላል። እንደሚከሰት ከተናገርኩ ግን፡ መቼ እንደሚከሰት ካልተናገርኩ፡ በመቶ ትንሽ እድል አገኛለሁ። መቼ እንደሚከሰት አስቀድሜ ከተናገርኩ፡ ያነሰ እድል ይሰጠኛል። የተከሰተበትን ቦታ መተንበይ ከቻልኩ፡ አሁንም ትንሽ እድል ይሰጠኛል። ማን ላይ ይሆናል... የሚለውን ከጨመርኩበት፡ አሁንም እውነት ካልሆነ፡ ወደ አንድ መቶ ሺዎች ያህል መጠን የማይፈጸምበት ደረጃ እደርሳለሁ።

305 ስለ መሢሑ የተጻፈው ቃል ሁሉ፡ ሃሌሉያ፡ አንድም ሳይቀር፡ ቃል በቃል ተፈጸመ። እንዲያውም አንድ ቀን፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበበ ሳለ፡ በዓረፍተ ነገሩ መሐል ላይ ቆም ብሎ፡ ተናገረ፡ “የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ፡ ነጻ አወጣ ዘንድ... ” በአረፍተ ነገሩ መሐል ላይ አቆመ፡ ምክንያቱም ቀጣዩ አረፍተ ነገር በዳግም ምጽአቱ ላይ የሚፈጸም ነው። አሜን! “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” አያችሁ?

306 እንግዲያውስ በወቅቱ እየመገባቸው የነበረው፡ የወቅቱ ቃል እሱ ራሱ ነበር። ሙሴ እውነት ነገራቸው፡ ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ሁልጊዜ ከውስጡ የሐይማኖት ተቋም ይመሰርቱበታል፡ ከዚያ በኋላ አሞራዎቹ...

307 ንስሮች በልተው ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ የተወሰነ ነገር ይቀራል። ከዚያም ሌላ ነገር ለማየት ይጠባበቃሉ። “ቃሉን፡” እንዲህ ይላሉ፡ “ሌላ ነገር ይመጣል። ትናንት አጋዘን በልተናል፥ ነገ በግ እንበላለን።” ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ? “የበሰበሰ የአጋዘን በድን እዚያ አለ፡ ሌላ በተወው የሚደሰቱ፡ ነገ ደግሞ በግ እንበላለን። የት አለ? ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? የመላእክት ምግብ! ዛሬ መና የበሉ ሰዎች፡ በሚቀጥለው ቀን ራሱን ለመብላት ለማሳደር ቢሞክሩ፡ ይበላሻል። ጥላዎቹ ሁሉ፡ እንዴት ፍጹም እንደሆኑ አታዩም? አሁንም ያው ነው!

308 በኢየሱስ ዘመን የነበሩት አሞራዎች አጋንንትን ያወጡ እንደነበር፡ ልብ በሉ፥ በበሰበሰ ስጋ ላይ ላይ የሰፈሩ ቅቡዓን። ልክ ነው? አጋንንትን ያስወጡ ነበር። ኢየሱስም እንዲህ ብሏልና።

309 በዚያን ጊዜ፡ ነቢያት እንደነበሩአቸው አስታውሱ። እነ ቀያፋ፡ ሊቀ ካህናቱ፡ ትንቢት ተናግሯል። ይህን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ቀያፋ ትንቢት ተናገረ። በእርሻው ውስጥ ያለውን የእንክርዳድ ቦታ ልብ በሉ፡ በተመሳሳይ ቅባት የተቀባ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን ተናገረ ያለው ለምንድን ነው? “በዚያን ዓመት ሊቀ ካህን ስለነበር።” በሰንዴው መካከል የሚቀመጥ፡ የበሰበሰ ስጋ የሚበላ፡

እንክርዳድና አሜከላ፥ መንፈስ ግን እውነተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በእርሱ ላይ ነበረ። እንዲሰብክ፡ እንዲተነብይ፡ ሊሆን ያለውን እንዲናገር፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእሱ ላይ ነበር፥ የተረጋገጠውን የዘመኑ ቃል ግን ተቃወመው ሰቀለውም።

310 ኦህ፡ ምህረት ያርግልን፡ ወንድሜ! እነዚህን ነገሮች ሰንት ጊዜ መናገር አለብን፡ እያችሁ፡ በምጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንቴ እንመልከት? እፈጥናለሁ። እዚህ ጋር፡ ሁሉንም ነገር ለማረጋገጥ አሥር ገጽ የሚሆኑ፡ ጥቅሶች አሉኝ። "ፀሐይ በጻድቁም ሆነ በኃጢአተኛው ላይ፡ ተመሳሳይ ነው።"

311 ይህን ለማረጋገጥ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ። "እኔ በአምላክ ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆነ፡ ልጆቻችሁስ በማን ያሰወጧቸዋል?" እንግዲህ፡ እነርሱም አጋንንትን ያወጣሉ፡ ትንቢትን ይናገራሉ። ልክ ነው? እርሱ ራሱ የዘመኑ ቃል መሆኑን ግን እውቅና አልሰጡትም፡ (ለምን?) ከእነርሱ ጋር ሰላልተሰማማ ነው።

312 አሁን ማቴዎስ 24፡24ን እንውሰድ፡ "ሐሰተኛ ክርሰቶሶች፡" የተቀቡ ሰዎች፡ "ይነሳሉ፡ እንዲሁም ትንቢት የሚናገሩ ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፡" እያችሁ፡ "ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።" አሁን ገብቷችኋል?

313 ልጆቻችሁ ሲል ልብ በሉ። "ልጆች እነማን ናቸው... እኔ አጋንንትን የማሰወጣው በእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፡" እርሱ ራሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነበር፡ "የሃይማኖት ተቋም ልጆቻችሁስ በማን ያወጧቸዋል?" አሁን፡ ዲያቢሎስን ማባረር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡ ያንን እናውቃለን፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ምክንያቱም፡ ጠንካራው ሰው በቤት ውስጥ ካለው ሰው የበለጠ ጠንካራ መሆን አለበት። ይህን ለማድረግም ኃይል ነበራቸው።

314 የክርሰቶስ ተቃዋሚ፡ በመጨረሻው ዘመን እንደሚነሳ... ከራእይ ዘንድ ተረድታችኋል፡ ታውቃላችሁ፡ "ብዙ ድንቆችንና ምልክቶችን እንደሚያደርግ፡ እንዲሁም በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ እንደሚያሰት እና፡ ሰማቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያልተጻፈ፡ ክርሰቲያኖችንና ሌሎችን ሁሉ፡ እንደሚያሰት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡" የማቴዎስ 24: 24 መልስ፡ "ሰማቸው ዓለም ከተመሠረተበት ጊዜ እንሥቶ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያልተጻፈ።"

315 በዛ—በዛ እውነተኛ የብርቱካን ዛፍ ሰሮች ውስጥ የነበረው ሕይወት፡ እነዚያን ሁሉ የሆምጣጤ ዓይነቶች አልፎ፡ በዛፉ ጫፍ ላይ ፍሬውን በላይ ያስቀምጣል፡ ከሁሉም ሃይማኖታዊ ተቋማት እና ቅርንጫፎች በላይ ያደርጋል። አገኛችሁኝ? እፈጥናለሁ። ጠንካራው ሰው...

ዳዊትን አስታውሱት፡ እርሱ ሐቀኛና፡ ቅን ሰው ነበር፡ ይህን ለማድረግ ሳይሾም ግን፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማገልገል ሞከረ።

316 "እነዚህ፡" የተቀቡ ሰዎች፥ ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ፡ "የሰውን ትርጓሜ ያለውን (የቅዱሳን መጻሕፍት) ትምህርት ያስተምራሉ።" እያችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን፡ የተረጋገጠ ቃሉ ሳይሆን፡ ታሪካዊ ክርሰቶስን የሚያስተምር ነው፡ እያችሁ፡ እንዲህ መሳይ ነገር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም “እርሱ ነው፡” ይላል። “የነበርኩወይም ወደፊት የምኖር፡” ሳይሆን “እኔ ነኝ።” “እኔ ነኝ፡ አሁን።” እርሱ እዚህ ውስጥ የሚኖር ቃል ነው።

እሱ፡ መጀመሪያ ላይ ነበር፡ እሱ በ—በቡቃያው ውስጥም እርሱ ነበር፥ በዝራረት ውስጥ ነበር፥ በአገዳው ውስጥ ነበር፥ አሁን ግን ፍሬው ውስጥ ነው።

317 አሁን፡ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ እንደገና ለመኖር ትሞክራላችሁን? ያ ሕይወት ወደ ኋላ ቢመለስስ፡ (የወጣው) ሕይወት መቼም ቢሆን ይናገራል ብላችሁ ታስባላችሁ፡ ያረጀው አገዳ ከደረቀ በኋላ ይመለሳልን፡ እንደገና ተመልሶ በውስጡ ይኖራልን? በፍጹም አይሆንም። “አንድ ጊዜ ብርሃን ለበራላቸው ሰዎች ይህን ማድረግ አይቻልም፡” ቃሉም በተፈጸመ ጊዜ ከቃሉ ጋር አብረው አይቀጥሉም፡ “ሞተዋል፡ ጠፍተዋል፡ እሾህና አሜከላም ወደ መጣል ቀርበዋል፣ መጨረሻቸውም ወደ መቃጠል ነው።” ልክ ነው?

አሁን በተቻለኝ አቅም ለመፍጠን እየሞከርኩ ነው።

318 አሁን ቅዱሳት መጻሕፍትን ልብ በሉ። በታሪክ ውስጥ ያለ አምላክ እንደማስተማር፡ ተመልከቱ፡ ልክ ባለፈው ጊዜ ለመኖር እየሞከሩ እንዳሉ፡ ለምሳሌ፡ “እነ፡ ዌስሊ **እከሌ-እና-እከሌ** አለ።” ወይም፡ “**እከሌ-እና-እከሌ እከሌ-እና-እከሌን** እንዲህ አላቸው።” የዘመኑ የተሰፋ ቃል፡ በዘመኑ በግልፅ የታወቀውን መና እየተቃወማችሁ ነው። በአዲሶቹ ጠርሙሶቻችን ውስጥ ያረጀውን የሉተራን፡ የባፕቲስት፡ የጴንጤቆስጤ ወይን ጠጅ ለማስገባት ይሞክራሉ። አይሠራም። እና አዲሱን የወይን ጠጃችንን፡ ባረጀ ጠርሙሶቻቸው ውስጥም፡ አይሠራም። ይህን አዲስ የወይን ጠጅ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ለማስገባት ቢሞክሩ፡ ስህተታቸው ይገለጣል። ይህን ማድረግ አይችሉም። ይህ ቤተክርስቲያኗን ያፈርሳታል።

“አሁን፡ ወንድሜ፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ በቃሉ በትክክል አይቼዋለሁ!”

319 “አሁን፡ ዶክተርዬ፡ እስቲ ተመልከት፡ ይህን... እኛ—ሊኖረን አይችልም።” ኔድ፡ እስከ አሁን የተረዳኸው ይመስለኛል። “እኛ፡ እኛ አሁን እዚህ ጋር ይህ ሊኖረን አይችልም። እኔ—ብትተውት ይሻላችኋል እላለሁ።” ታውቃላችሁ። አያችሁ፡ አይሠራም። ትፈነዳለች።

320 “በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ እራፊ አታሰቀምጡም፡ ምክንያቱም ልብሱን በሙሉ ትቀዳላችሁና።” አያችሁ? ኢየሱስ እንዲህ አላለም? አዲሱን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ ማድረግ አትችሉም። አቁማዳው ያፈነዳልና። አዲሱ የወይን ጠጅ በውስጡ ሕይወት አለው። መልካም።

321 እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ በሉ፡ አሁን በጣም መፍጠን አለብን፡ ንግግራችን... እያጠናቀቅን። መጽሐፈ ራእይ 16:13 እስከ 14፡ ላይ ያለውን ሃሳብ ልብ በሉ። ምናልባት እሱን ለማንበብ ጊዜ አይኖረኝም። እርግጠኛ እንድትሆኑ እና እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ። አሁን ልብ በሉ፡ ይህ በሰድስተኛው እና ሰባተኛው ጽዋ መካከል ያለው ድምፀ ነው።

አሁን... ብቻ ጥቂት ተጨማሪ ደቂቃዎች መታገስ ከቻላችሁ በደቂቃ ውስጥ እዘጋዋለሁ። አሁን በመዝጊያ ላይ ነን።

322 ከራእይ 16:13 እስከ 14 ላይ የሚገኘውን፡ በስድስተኛውና በሰባተኛው ጽዋ መካከል ልብ በሉ። “ሦስት ርኩስ መናፍስት እንደ እንቁራሪቶች” (ይህን አስተውላችኋል? ) “ከሆነ ሰው አፍ ውስጥ ነው የወጡት።” አሁን በፍጥነት፡ ተከታተሉኝ። ተዘጋጅታችኋል? “አሜን።” በሉ፡ [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] የመናፍስቶች ሰላሴ!

323 አሁን የሃይማኖት ተቋም ወንድም ሆይ፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ተረጋግተህ ቁጭ በል። ተነሥተህ ከክፍሉ አትውጣ፡ እናንተ በሬድዮና፡ በመገናኛ-ዘዴ ላይ ያላችሁም እንዲሁ። የቴፕ መቅጃችሁን አታጥፉ። አንድ ደቂቃ ብቻ ታገሱ፡ እና አድምጡኝ። ከእግዚአብሔር የተወለዳችሁ ከሆናችሁ፡ ታዳምጣላችሁ።

324 የእንቁራሪቶች ሰላሴ! እንቁራሪት ሁል ጊዜ ወደ ኋላ የሚመለከት እንስሳ ነው። ወደ መጣበት አቅጣጫ ያያል እንጂ፡ በፍጹም ወደሚሄድበት አያይም። አያችሁ? አይታያችሁምን? ሥላሴአዊነት የተወለደው የት ነው? አስታውሱ፡ “ሦስት ርኵሳን መናፍስት፡” ራሳቸውን የቻሉ መናፍስት። እየገባችሁ ነው? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።]

325 ልብ በሉ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን፡ የሥላሴ አስተምህሮ ወደ ተወለደበት ወደ ኒቂያ ጉባኤ ወደኋላቸው ያያሉ። እንደዚህ ዓይነት ነገር የለም። የኒቂያ ምክር ቤት በኒቂያ፡ ሮም፡ ሥላሴ ወደ ተወለደበት ቦታ ወደ ኋላ ይመለከታሉ።

326 ከየት እንደመጡ ልብ በሉ። ልብ በሉ። ካረጀው ሰላሴ የመጣው የእንቁራሪቶች ሥላሴ፡ አዲስ ሥላሴን ወለደ፡ እናታቸውን። ከዚያስ ከምን ወጣች? ሥላሴ፡ “ዘንዶው፡” አያችሁ፡ “አውሬው፡” እና “ሐሰተኛው ነቢይ።” አዲሱ፡ ሥላሴ። እነዚህ እንቁራሪቶች የወጡት መቼ ነበር? መቼ ነው? ልብ በሉ፡ ከድሮም እዚያው ነበሩ፡ እስከ ስድስተኛው እና ሰባተኛው ጽዋ ድረስ ግን አልተገለጠም ነበር፡ ይህን ለመግለጥ (እህም? ) ማህተሞቹ ከመከፈታቸው በፊት።

327 “ምክንያቱም በሰባተኛው መልአክ መልእክት ውስጥ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢሮች ይታወቃሉና፡” እነዚህ የሥላሴ ነገሮች በሙሉ፡ እና የሐሰት ጥምቀቶች፡ እና ሌሎች ነገሮች ይገለጣሉ። እውነቱ ምን እንደሆነ እንድናውቅ እግዚአብሔር ይርዳን! አንድ ሰው የሆነ ነገር ሊነግረን እየሞከረ ነው ብላችሁ እንዳታስቡ...

328 መንፈስ ቅዱስ ይህን መልዕክት እያስተላለፈ እንደሆነ ይሰማኛል፡ አያችሁ። እኔ ከራሴ እየተናገርኩ አይደለም፡ ወንድሜ። በጉባኤው ውስጥ ካለው የጌታ መልአክ ዘንድ እየተናገርኩ ነውና። ይህም ትክክል ነው።

329 ሥላሴን፡ ልብ በሉት! “ዘንዶው፡” ዘንዶው ምን እንደነበረ የምታውቁት ስንት ናችሁ? ሮም ነበር። “ዘንዶውም ሴትየዋ ስትወልድ ልጇን ለመብላት በፊቷ ቆመ።” ልክ ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “አውሬ” ማለት ምን ማለት ነው? ስልጣን። መልካም። “ሐሰተኛ ነቢይ፡ ሐሰተኛ ነቢይ፡” በሐሰት፡ የተቀባ ሰው። አያችሁ?

330 የት ተጀመረ? ይህ “ሐሰተኛ ነቢይ፡” ነጠላ ቍጥር ነው። “ሐሰተኛ ነቢይ፡” የመጀመሪያው ጳጳስ፥ ከዚያ ደግሞ “የ—ጋለሞታዋ፡ እና የጋለሞታዎች እናት፡” ሁሉም ነገር ከዚያ የመጣ ነው።

331 የሐሰት ሥላሴ እየተነሣ ነበረ፡ በመጀመሪያዎቹ ቀናት ውስጥ አይደለም፡ በመጀመሪያዎቹ ቀናት ቢሆን ሊገለጥ አይችልምና፡ በቀጥታ ከሱ ጋር ቀጠለ። ነገር ግን ሰባቱ ማህተሞች መጥተው፡ እነዚያን ምስጢሮች ሲከፍቱና ሲገልጡ፡ "እንደ እንቁራሪቶች የመሰሉ፡ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ራሳቸውን ለመግለጥ የሚወጡት፡" ያኔ ነው፡ ይህም እውነትን የሚጻረር የሥላሴ ትምህርት ነው። አያችሁ? አይደል!

ከየት እንደመጣ ተመልከቱ? ተመልሰው ወደ የት እንደሚሄድ ተመልከቱ? የአብያተ ክርስቲያናት ካውንስል። ሁሉም ወንድማማቾች ናቸው፡ እንደውም፥ ተመሳሳይ መንፈስ፡ ተመሳሳይ ነገር አላቸው።

332 ተመልከቷቸው። ተአምራቶችን በማድረግ፡ በጣም ያስታሉ! እነዚህም በመጨረሻው ዘመን ሊያታልሏቸው፡ ተአምራትን እያደረጉ፡ ወደ ምድር አማልክት የሚመጡ አጋንንት ናቸው፡ ይህ በማድረጋቸውም ይሳካላቸዋል። እግዚአብሔር ስለዚያ ክፉ መንፈስ ምን ኣለ?

ያ ሲናገር፡ "ወርጄ በእነዚያ ነቢያት አፍ ውስጥ እገባለሁ በሐሰትም እንዲተነብዩ አደርጋቸዋለሁ፡ አክዓብም ወደዚያ ወጥቶ እንዲጠፋ አደርጋለሁ።"

333 እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፡ "ሂድ። ይሳካልሃልና። እንዲያምኑህ ታደርጋቸዋለህ። ከመጀመሪያም፡ ከቃሉ ወገን አይደሉምና።" አያችሁ? "ታሳምነዋለህና፡ ሂድ። በእነዚያ ሐሰተኛ ነቢያት ውስጥ ስትገባ፡ ይህን የምታደርገው አንተ ነህ፡ ይህም በእነሱ ላይ ስለሚተማመን ነው። ስለ ቃሉም ምንም የሚያውቀው ነገር የለም፡ ለመማርም አይሞክርም። ይህን ማድረግ አይችልም፡ ከመጀምሪያውም አመኬላ ነውና፡" አያችሁ? አያችሁ? "ይሳካልሃል።"

ወደ ኋላቸው የሚያዩት፡ እነዚያን ሐሰተኛ እንቁራሪቶች ተመልከቷቸው፡ "ለምን፡ በኒቂያ ምን እንዳሉ ታውቃላችሁ? "

334 በዚያ በኒቂያ፡ የተናገሩት አይገደኝም። እዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ የተናገሩትን ነገር ነው የምናገረው፡ የሚሆነውን እንጂ፡ ያለፈውን አይደለም፥ የሚሆነውን ነው፡ እርሱ **"እኔ ነኝ"** ነውና። አያችሁ?

"ሐሰት።" ይህን ተመልከቱ። ሃህ! ከየት እንደመጡ ልብ በሉ።

335 አሁን (በጥሞና አዳምጡ።) ሰባቱ ማህተሞች ከተከፈቱ በኋላ፡ በግልጽ እናያለን። ይህም ምሥጢሩን ለመግለጥ ነው፥ ይህ ሥላሴ ምንድን ነው? አያችሁ? ሥላሴ ተብሎ የተጠራው የት ነው? አያችሁ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የት ነው ሥላሴ የሚለው ቃል የተጠቀሰው? ሶስት አማልክትስ የት ሊኖሩ ይችላሉ፡ እንዴት ነው እኛ ሦስት አማልክት እያመለክን አረማውያን የማንሆነው?

336 "እኔና አብ አንድ ነን፡" እያለ፡ እንዴት ሊለያዩ ይችላሉ? "እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፡ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ፡ አያችሁ፡ በአለማመናችሁ።" ኃጢአት አለማመን ነው። "ባለማመናችሁ ትጠፋላችሁ።"

> ኦህ፡ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ፡ ከየትስ መጣ
> ትሉኛላችሁ፡

ኦህ፡ አባቴን ታውቃላችሁ፡ እስቲ ስሙን ተናገሩ?
እኔ የሳሮን ጽጌረዳ፡ የንጋት ኰከብ ነኝ።

እሱ ማን እንደሆነ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?

በቊጥቋጦ እሳት ውስጥ ሙሴን ያነጋገርኩት እኔ ነኝ፡
የአብርሃም አምላክ፡ የሚያበራም የንጋት ኰከብ እኔ ነኝ።
ከየት መጣህ ትሉኛላችሁ፡ ኦህ፡ የሣሮን ጽጌረዳ እኔ ነኝ፥
ኦህ፡ አባቴን ታውቃላችሁ፡ እስቲ ስሙን ተናገሩ? (አሜን!)

አልፋና፡ ዖሜጋ፡ መጀመሪያ እና መጨረሻ እኔ ነኝ፥
እኔ ፍጥረት ሁሉ ነኝ፡ ስሜም ኢየሱስ ነው።

እውነት ነው። ሥላሴ አይደለም! አይ፡ ወዳጄ። እሱ ውሸት ነው።

337 ሰባቱ ማህተሞች፡ "መፈጸም ያለባቸውን" ሚስጢሮች በመክፈታቸው፡ ተገለጡ። ማኅተም ተከፈተ፥ እነዚህን ሁሉ ዓመታት፡ በአብያተ ክርስትያናት፡ እና በሐይማኖት ተቋማት አማካኝነት፡ ማህተሞች የደበቋቸው የተደበቁ እውነቶችን ይፈታል ያሳያል።

በራእይ ምዕራፍ ሰባት ላይ-... የተገለጸችው "ታላቂቱ ጋለሞታ፡" ማን ነበረች? ደግሞም "የጋለሞታዎች እናትም፡" ናት። አያችሁ?

"ወንድም ብራንህም፡" እንዳልከው፡ "እንግዲያውስ አሁን፡ 'አሞራዎች' ብለሃቸዋል።" በትክክል እውነት ነው።

338 ይሁን እንጂ፡ አሞራ ወፍ መሆኑን፡ አትዘንጉ። ደግሞም፡ እንዲበር የተቀባ ነው። "የተመረጡትን ለማሳት፡ ሁለቱ መናፍስት እጅግ ይመሳሰላሉ... " አሞራም እንደ—እንደ ንሰር ትልቅ ነው። እንደ ንሰር መብረር ይችላል፡ እናም ለመብረር፡ ወይም ለመሰበክ፡ ወይም ለመተንበይ የተቀባ ነው፡ ልብ በሉ፡ ልክ እንደ ንሰር። ንሰርን ግን በከፍታ ላይ መከተል አይችልም። በጭራሽ፡ በጭራሽ። እርሱ ንሰርን መከተል ከሞከረ፡ ድክመቱ ይገለጣል። አዎን፡ ወዳጄ። ንሰርን መከተል አይችልም።

339 ኦህ፡ ማለት ይችላል፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ። የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው፡ ሁሉን ቻይ የሆነው፡ እግዚአብሔር አብ፡ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን አምናለሁ፡" ወዘተረፈ ሊል ይችላል። ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ ይህን ማድረግ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እሱ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው መሆኑስ? አያችሁ?

340 ንሰር በልዩ-ሁኔታ የተሰራ ወፍ ነው። በምድር ላይ፡ እንደ እሱ ያለ ምንም ነገር የለም። አያችሁ? እ—እሱን... ጥንብ አንሳው ወይም ሌላ አይነት ወፍ፡ እሱን መከተል ቢሞክር፡ ይወላገዳል። ድክመቱ፡ በትክክል ይገለጣል። አዲሱን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ ለማድረግ ሲሞክር ይፈነዳበታል። አያችሁ፡ ይፈነዳል። ይወላገዳል። እንዲህ እንዲሆን አልተሰራም፡ አይደለም... አካላቱ እዚያ ከፍታ ላይ እንዲሸከሙት ተደርገው አልተፈጠሩም። ወደዚያ ታላላቅ አየር ወደሚያጥርበት ከፍታ ሲደርስ፡ አስቀድሞ የታሰበ፡ የተመረጠ፡ የተወለደ ንሰር ሆኖ፡ ባይሠራ ኖሮ፡ ይበታተን ነበር። አያችሁ? ከክንፎቹ ላይ ላባዎቹ ተሰባብረው፡ ወደ ምድር ይወዳድቃሉ። እርግጥ ነው። ንሰርን

በከፍታ፡ መከተል አይችልም። ከሞከረ ግን፡ ድክመቱ ይገለጣል። ትክክል ነው። አትችሉም።

341 ለምን? እንደ ንስር ማየት አይችልም። ስትደርሱ የት እንዳላችሁ ማየት ካልቻላችሁ፡ ከፍ ብላችሁ መዝለላችሁስ ምን ይጠቅማችኋል? ከፍታዎች ላይ፡ ንስርን ለመምሰል፡ በጣም ከፍ ለማለት ቢሞክር፡ እዚያ ሲደርስ ምን እየሰራ እንደሆነ ማየት እንዳይችል አይኑ ይታወራል? እውነት ነው። ሊጮኽ እና ድምጽ ሊያሰማ፡ እና ወዲያ ወዲህ ሊል ይችላል፥ ይሁን እንጂ በቀላሉ ቃሉን ንገረው፡ ወንድሜ፡ ያኔ ድክመቱ ይገለጣል።

342 ስለ ኢየሱስ ስም ጥምቀት አውራው፡ ወይም፡ ትላንትናም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው እንደሆነ አውራው፡ የ—የመሳሰሉት ነገሮች፡ ንገረው። “ታዲያስ፡ ኦህ፡ ይኸውላችሁ!” አያችሁ? ኦህ፡ አዎን፡ ላባዎቹ ወዲያውኑ ይረጋገፋሉ። እነሆ፡ ተነሥቶ፡ ትንቢት ይናገራል፡ አጋንንትንም ያሰወጣል፡ በልሳኖችም ይናገራል፡ ይጮሃል፡ ወለሉ ላይ፡ ወዲያ-እና-ወዲህ ይላል ይሮጣል። አትከተሉት፥ ለምን፡ መጋለጡ አይቀርምና።

343 ሆኖም፡ የተሾመ ነው። የተቀባ ነው። መብረር ይችላል። ሚዛኑን መጠበቅ ይችላል፡ ወደ ላይ መውጣት ይችላል፡ ነገር ግን... ብዙ አይዘልቅም። አያችሁ፡ የበሰበሰ መብላት ይችላል፡ ከዙፋኑ የሚመጣውን ትኩስ ሥጋ ግን መብላት አይችልም።

344 ዓይነ ሰውር ነው። በጣም ግራ ይጋባል፡ ለምን ግራ እንደሚጋባ ግን አያውቅም። አያችሁ፡ እርሱን ሰንዱ ለማድረግ፡ እንደሚወርደው ዝናብ፡ በእርሱ ላይ የሚወርደው ያው መንፈስ ነው፡ ከመጀመሪያ ግን ሰንዴ አይደለም። ይፈነዳዳል፡ “ኦህ፡ ከዚህ በላይ መሄድ አልችልም... ኦህ፡ አይ፡ ጌታዬ! ዶክተር ጆንስ ያለውን አውቀዋለሁ... ” መልካም፡ ቀጥል። አየህ? ቀጥል፡ ከፈለግህ።

345 አይ፡ ልብ በሉ፡ እንዲህ ዓይነት ወፍ ለመሆን አልተወለደም፡ አልተሰራም፡ አልተወሰነም፡ ወይም አልተመደበም። ምን... ምናልባት... ሎሚው በብርቱካን ዛፍ ላይ ሊያድግ ይችላል፡ ግን በጭራሽ ከሰሩ አልወጣም። የተጨመረ ነገር ነው። እና በሃይማኖት ተቋማቸው ውስጥ በጣም ከፍታ ላይ ሲደርሱ አስቀድሞ የተወሰነው የእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጠ ማየት አይችሉም፡ ያኔ ድክመታቸው ይታወቃል። “ኦህ፡ ያ ነገር፡ በራሱ ላይ ያለው እሳት፡ እና ሁሉም ነገር፡ ኦህ፡ ትርጉም የለሽ ነው።” አያችሁ? የታወቀው።

346 ይህን ያህል ርቀት ለማየት አልተፈጠረም። ማየት የሚችለው የሃይማኖት ተቋሙ መነጽሮች የሚፈቅዱለት ርቀት ያህል ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ፡ ግን፡ እንደ ሌሊት ወፍ እውር ይሆናል። ድክመቱ የሚገለጠው ያኔ ነው። አያችሁ? እውነተኛ ንስር ግን ምግቡን ለመመገብ ተመቻችቶ የሚቀመጥበት ቦታ ነው። አዎን፡ ጌታዬ። እውነተኛዎቹ፡ የተመረጡ ንስሮች ምን እንደሆኑ የሚያዩበት ቦታ ነው። ቃሉን አልቀበልም ሲል፡ ወዲያውኑ የሃይማኖት ተቋም አሞራ መሆኑን ይታወቃል።

347 ለምን፡ ለምን አይበርም? ምክንያቱም፡ ምን እየበላ እንደነበረ ተመልከቱ። የበሰበሰ የሃይማኖት በድን ሲበላ ቆይቷል። ያ ደግሞ—ሰውነቱን መንፈሳዊ አያደርገውም፡ መንፈሳዊ ብቃት ላይ አያደርሰውም፡ በሌላ አባባል፡ ከሃይማኖት ተቋማት መለያየቶች በላይ ከፍታ ላይ አያወጣውም። አያችሁ? አያችሁ፡ እሱ

የሚመገበው የበሰበሰ ነገር ብቻ ነው፡ ሰውነቱ የተሠራው ከዛ ነው። ያ ትኩስ ሥጋ ያንን ንስር ወደ ሚሸከምበት ወደዚያ ከፍታ መሄድ አይችልም። እሱ ያንን ማድረግ አይችልም። አያችሁ?

348 ይህ የማቴዎስ 24:24 ፍጻሜ ነው። እየበረረ ነው፡ በአየር ላይ እየዘለለ ነው፡ ክንፎቹን እያወዛወዘ ነው፡ ነገር ግን በቂ ከፍታ ላይ መድረስ አይችልም። አያችሁ? ትክክል ነው። አያችሁ፡ መሄድ አይችልም፡ ትኩሱን መና ለማግኘት በቂ ከፍተኛ መድረስ አይችልም። እዚህ መሬት ላይ የሚገኘውን የተላ መና መመገብ ይችላል፡ ከሳምንት በፊት፡ ከአንድ ወር በፊት፡ ወይም ከአርባ ዓመት በፊት፡ ተገጭተው የሞቱትን የቆዩ ጥንቸሎች መብላት ይችላል። ያን መብላት ይችላል፡ በሱ ላይ ሊደሰት፡ እና ሊያሽካካ እና ሊጮህ፡ ወዲያ ወዲህ ሊል፡ ሊዘል እና እንደ ሌላ ንስር ሊበርር ይችላል። እንደ ሌላ ወፍ፡ የተቀባ ነው።

349 የንሰር ዓይነት ነው፡ ጥንብ አንሳ ነው። ይህ እናውቃለን። በእርግጥ ነው፡ እውነተኛውን ንሰር መከተል ግን አይችልም። አያችሁ? ይህን ማድረግ አይችልም። አይችልም፡ ጌታዬ። ሰውነቱ የተሰራው እንደዚህ አይደለም፥ ሲበላ የኖረው የተላ ስጋ ነው፡ አያችሁ፡ እና አይሆንም... ይህ አይሆንም—ትኩስ ሥጋ፡ ትኩስ መና አይሆንም። ሉተር እንዳለው፡ ዌስሊ እንዳለው፡ ወይም ዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ** እንዳሉት ብቻ ይሆናል። ኢየሱስ ለዚህ ዘመን የተናገረው ሊሆን አይችልም።

350 አሁን ወደ መዝጋት፡ እንሂድ። በመጨረሻው ዘመን፡ የተቀቡ ሰዎች፡ "ክርስቶሶች፡" ነገር ግን "ሐሰተኛ አስተማሪዎችና ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው።" ምን ያህል አሰገራሚ እንደሆነ አስተውሉ! አሁን፡ ይህን እንድታወዳድሩ እፈልጋለሁ፥ ለማንበብ ጊዜ የለንም። ማቴዎስ 24:24 ከሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3:8 ጋር አወዳድሩት።

351 ማቴዎስ 24፡24 እንዳለው፡ በመጨረሻው ዘመን፡ አያችሁ፡ "ሐሰተኛ ክርሰቶሶች ይመጣሉ፡" ሐሰተኛ፡ የተቀቡ ሰዎች፡ "ሐሰተኞች ነቢያት፡ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡" ልክ እንደ እውነተኛው፡ እንደ እውነተኛው፡ "እናም የተመረጡትን ሊያስቱ—እስኪዳዳቸው ድረስ።" አሁን አስተውሉ፡ እዚህ ጋር የተናገረው ኢየሱስ ነው።

352 እዚህ ላይ፡ ጳውሎስ ከኋላው መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ "እነሆ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ የአምልኮት መልክ ያላቸው፡ አያችሁ፡ ሃይማኖተኞች ይመጣሉ። እነሱም በዓለም ምኞቶች የተታለሉ፡ ሞኝ ሴቶችን ይመራሉ።"

ከዚያም፡ "ለምን እነዚህን ሴቶች ትመርጣላችሁ፡" በማለት ይገረማሉ? ኦህ፡ ይገርማል... ማየት እንኳን አይችሉም።

"በልዩ ልዩ ምኞት የተሞሉ፡ ሞኝ ሴቶችን ይመራሉ፡" ከዚህ... ከመሳሰሉት ነገሮች ራቁ... አያችሁ፡ "እንደ ያኔሰና ያምብሬሰ... "

ማቴዎስ 24፡24 ላይ፡ "ሐሰተኛ ክርሰቶሶች፡" በሐሰት፡ የተቀቡ ሰዎች፡ የተመረጡትን ለማሳት ምልክትና ድንቅ የሚያደርጉ።

353 አሁን፡ ኢያኔሰና ኢያንበሬሰም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፡ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ ያደርጋሉ፡ ሰለ እምነት የተበላሸ አእምሮ ያላቸው። **ተራው** እምነት ሳይሆን፡ **ዋናው** እምነት! "አንድ እምነት፡ አንድ ጌታ፡ አንድ ጥምቀት-... "

**በአንድ** ጌታ ሳታምኑ **አንድ** እምነት ሊኖራችሁ አይችልም። ሁለት ጥምቀቶች ሊኖሩህ አይችሉም፡ አንዱ ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስ። አንዱ ጥምቀት፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ። አየህ? እውነት ነው። አያችሁ፡ የሐሰት ጥምቀት!

354 አስተውሉ፡ ቤት ስትሄዱ አንድ ላይ አነጻጽሯቸው። ኢየሱስ፡ በማቴዎስ 24:24፡ ላይ ሲናገር፡ ጳውሎስ በ2 ጢሞቴዎስ 3:8፡ እና ሌሎች በርካታ ጥቅሶችን አስተውሉ። አሁንም አነጻጽሩት።

ከዚያም ሌላ ጥቅስ ጨምሩበት፡ ሉቃስ 17:30፡ ሚልክያስ 4።

የዘመኑን የተቀባውን ቃል፡ "ኢያኔስና ኢያምብሬስ ሙሴን እንደተቃወሙ፡" "ስለዚህ እነዚህ ሰዎች፡" አንድ ሰው ሳይሆን፡ "ሰዎች፡" የተቀቡ፡ "እውነትን ይቃወማሉ።"

355 "የሰው ልጅ በሚገለጥባት በዚያች ቀን።" ራዕይ 10:1 እስከ 7፡ ወደ ቤት ስትሄዱ አንብቡት፡ "የሰባተኛው መልአክ መልዕክት፡ የማኅተሞቹን መከፈት።" ምንድነው እሱ? የሰው ልጅ ማለት መልአኩ አይደለም፡ መልዕክተኛው ግን የሰው ልጅን እየገለጠ ነው። አሁን ሁለቱን መለያየት ትችላላችሁ? ለእናንተ በጣም አስቸጋሪ የሚመስለው እዚህ ጋር ነው፡ አያችሁ። የሰው ልጅ ራሱ፡ አይደለም፥ ነገር ግን ሰባተኛው መልአክ፡ ሰባተኛው መልእክተኛ፡ የሰውን ልጅ ለሕዝብ እየገለጠ ይገኛል፡ ምክንያቱም ከአገዳው ወጥቷል። አሁን አያቀናጃትም። ምክኒያቱም እሱ ራሱ፡ እንደገና፡ ዘር ሆኗል።

356 "በዚያም ቀን፡ ኢያኔስና ኢያምብሬስ ይቋቋማሉ፡" የተቀቡ ሰዎች (አስመሣይ-አማኞች እና የማያምኑት፡ ተራዋ ቤተክርስቲያን እና ጴንጤቆስጤዎች) እውነተኛዋን ዘር ላይ ይነሱባታል፡ "ይሁንና ተዉአቸው፡ የእነሱ ድክመትም፡ እንደነሱ ሁሉ ይገለጣል።" አያችሁ? አሁን ገባችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

357 ራእይ 10 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ።" አስታውሱ፡ ሰባተኛውን፡ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። "የመልአኩ ድምጽ ሲሰማ፡" ያ ዘመን ተጠናቅቆ የቤተክርስቲያን ዘመን በሚሆንበት ጊዜ፡ የጴንጤቆስጤው ድርጅት ሲያበቃ፡ የዚያ መልእክተኛ...

358 እያንዳንዱ መልእክተኛ ምን ነበር? ማርቲን ሉተር ምን ነበር? ለካቶሊካዊያን የተሰጠ ተግሳጽ ነበር። ዌስሊ ምንድን ነበር? ለሉተራኖች የተሰጠ ተግሣጽ ነው። ጴንጤቆስጤ ምንድን ነው? ለሌሎቹ የተሰጠ ተግሣጽ ነው። አሁን ሕይወት የት ሄዷል? ከድርጅቱ ርቋል። ከእንግዲህ ወዲህ አገዳው ላይ አይገኝም፡ ዘር ላይ ነው። ይህ ምንድን ነው? ለጴንጤቆስጢያዊያን ተግሣጽ ነው፡ አያችሁ፡ የዚህን ዘመን ቅዱሳን ቃላት ለመፈጸም። አያችሁ?

359 ልብ በሉ፡ ይህም መልእክተኛ... መልዕክቱን በሚጀምርበት ቀን ሳይሆን፡ በዚያው በሚያውጅበት ቀን ነው። አያችሁ? የመጀመሪያው ሰበት፡ ፈውስ፥ ሁለተኛው ሰበት፡ ትንቢት መናገር፥ ሦስተኛው ሰበት፡ የቃሉ መከፈት፡ የምስጢሮች መገለጥ ነው። ቃሉን ለመግለጥ፡ ከነቢያት በላይ፡ ከፍ ያለ ማዕረግ የለም። ነቢዩ ማረጋገጫ ማግኘት የሚችለው ብቸኛው መንገድ ግን በቃሉ ብቻ ነው። እና፡ አስታውሱ፡ ሦስተኛው ሰበት የሰባቱንም ማህተሞች መከፈት ነው፡ ይህም በቃሉ ታትሞ የነበረውን የተደበቀውን እውነት ለመግለጥ ነው። አያችሁት? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

360 ይህ ነገር በሚፈጸምበት ቀን ይህ የሚሆነው፡ ያኔ ነው፡ ማለት ኢያኔስና ኢያምብሬስ፡ የተባሉት አስመሳዮች፡ ዳግመኛ ይታያሉ። ሙሴ የመጀመሪያውን ቃል ይዞ በመጣበት ጊዜ እንዳደረጉት ሁሉ፡ ይህን ለመቃወም፡ ቃሉን ለማስመሰል ይነሳሉ። በትክክል እውነት ነው። ማቴዎስ 24:24 ምን እንደሚያመለክት አስተዋላችሁ? አያችሁ፡ የተቀቡ ሰዎች!

361 ከመዝጋታችን በፊት ልንነግራችሁ የምንፈልጋቸው ሦስት ነገሮች አሉ። ይህ ብቻ ነው። አሁን መዝጊያው ላይ በጥንቃቄ እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ። ሦስት ነገሮችን፡ አስታውሱ፡ ሦስት ነገሮች ተፈጽመዋል። አሁን ከፊታችሁ ሦስት ነገሮች አሉ።

362 አንደኛ። ዓለም በሶዶም ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። ኢየሱስ እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯል። ሴቶቻችን ወንዶችን ለመምሰል መሞከራቸው፥ ወንዶችም፡ ሴታሴት ሆነው ሴቶችን ለመምሰል መሞከራቸው፥ አሁን ያለውን ጥፋት እዩት፥ ብልሹ፡ ቆሻሻ፡ ተራ-ወራዶች፡ በዲያብሎስ-የታሰሩ ሆነው፡ አያውቁትም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚሆን አስቀድሞ ተናግሯል፡ የደረስነው እዚህ ላይ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡ ኢያኔስ እና ኢያምብሬስ የተገለጡት፡ በዚያን ዘመን ነው። ሁለተኛው።

ሦስተኛ፡ የሰው ልጅ የሚገለጠው በዚያን በተመሳሳይ ዘመን ነው።

363 ይኸው አማኝ፡ ይኸው አስመሳይ-አማኝ፡ ይኸው የማያምን። እውነተኛው እና ጻዲቁ ቃል ጐልቶ ይታያል፡ አስመሳይ-አማኙ ደግሞ፡ እያስመሰለ አለ፥ የማያምነው ደግሞ ሁሉንም ነገር ይክዳል።

> ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል፡
> የክብርን መንገድ በእርግጥ ታገኛለህ፥ ( ትክክል ነው? )
>
> ሕዝቦች እየተሰበሩ፡ እስራኤል ተነቃቅተዋል፡
> መጽሐፍ ቅዱስ የተነበያቸው ምልክቶች፥
> የአሕዛብም ቀኖች ተቈጠሩ (የሰዶም)፡ በአስጨናቂ ሸክም፡
> "የተበተናችሁ ሆይ፡ ወደ ወገናችሁ፡ ተመለሱ።"
>
> የቤዛችሁ ቀን ቀርቧልና፡
> የሰዎች ልብ፡ በፍርሃት ወድቋል፥
> በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞሉ፡ መብራቶቻችሁ ዝግጁ እና ግልጽ ይሁኑ፡ (የዘመኑ ቃል ማየት ትችሉ ዘንድ።)
> ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧል።
>
> ሐሰተኛ ነቢያት ይዋሻሉ፡ (የተቀቡ ሰዎች፡ ይነሣሉ ተብሏል።)፡ የእግዚአብሔርን እውነት ይክዳሉ፡
> ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን መሆኑን ይክዳሉ፥

ይህ ነው፡ አያምኑም። መጽሐፍ ቅዱስ ያ ነገር ይሆናል አለ። ይሄው!

ይሁንና ሐዋርያት የሄዱበትን መንገድ እንከተላለን።

ያው ብርሃን! "እና የአባቶችን እምነት ለልጆች ይመልሳል።"

የቤዛችሁ ቀን ቀርቧል፡ (በጣም ቀርቧል።)
የሰዎች ልብ በፍርሃት ተውጧል፥ (ምድር ወደ ውስጥ
እየሰመጠች ነው።)
ኦህ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞሉ፡ መብራቶቻችሁ
የተሰተካከሉና ግልጽ ይሁኑ።
ወደ ላይ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧል።

ታምናላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እንግዲያውስ ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

364 ይህ መልእክት ወደሚሄድበት ምድር፣ ከምሥራቅ ዳርቻ እስከ ምዕራብ፡ ከካሊፎርኒያ እስከ ኒው ዮርክ፡ ወደ ደቡብ፡ ወደ ሰሜን፡ ወደ ተልዕኮዎች፡ እና ወደሚሄድበት ሁሉ፡ እንዲሁም ለዚህ ተበርናክል። ድሆች ነን። እነዚህ ታላላቅ፡ ትላልቅ፡ ያጌጡ ነገሮች እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፡ የሉንም። የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ እየሞከርን ነው። "አብ የሰጠኝ ሁሉ ግን ይመጣል።"

365 አሁን፡ እናንተ ይህንን ቴፕ የምታዳምጡ፡ ይህ በእርግጥ መሆኑን እንድታውቁ እፈልጋለሁ። ዛሬ ይህንን መልእክት እያዘጋጀሁ፡ ስለራሴ ለመናገር እየሞከርኩ ይመስላችሁ ይሆናል። እኔ ከዚህ በቀር ምንም የለኝም፡ ድምጽ ከመሆን በቀር ምንም አይደለሁም። እና፡ የእኔ ድምፅ፡ እንደ እኔ ፍላጎት ቢሆንማ፡ አዳኝ መሆን ነበር የምፈልገው። ይሁን እንጂ የአባቴን ፈቃድ ለማድረግ ወሰኛለሁ፡ ደግሞም ይህን ለማድረግ ቈርጫለሁ።

366 ወንዙ ላይ በተገለጠበት ጊዜ ቆሜ ብቻ ነበር እንጂ፡ የተገለጠው እኔ አልነበርኩም። እነዚህን ነገሮች የሚፈጽማቸው እኔ አይደለሁም እንዲሁም እንደተባለላቸው በፍጹም እውነት የሚገፈጸሙ ነገሮች እኔ አልተናገርኳቸውም፥ እኔ እሱ በሚሠራ ጊዜ አጠገቡ የነበረ ሰው ብቻ ነኝ። እሱ ለመናገር የተጠቀመበት፡ ድምፅ ብቻ ነበርኩ። የማውቀው ነገር አይደለም፡ ነገር ግን ይናገረብኝ ዘንድ፡ ራሴን አሳልፌ የሰጠሁ ሰው ነኝ። እኔ አይደለሁም፡ ሰባተኛውም መልአክ አይደለም፡ ኦህ፡ አይደለም፥ የሰው ልጅ መገለጥ ነበር እንጂ። እግዚአብሔር የገለጠው ምሥጢር ነው እንጂ፡ መልእክቱ፡ የመልአኩ አይደልም። የሰው አይደለም፥ ከእግዚአብሔር ነው። መልአኩ ከሰው ልጅ የተላከ መልእክተኛ ነበር እንጂ፥ እሱ ራሱ የሰው ልጅ አልነበረም። የሰው ልጅ ክርስቶስ ነው፥ የምትመገቡት እርሱን ነው። የምትመገቡት ተራ ሰውን አይደለም፡ የተራ ሰው፡ ቃሉ ይወድቃል። ነገር ግን እናንተ የማይወድቀውን የሰውን ልጅ የቃል-አካል እየተመገባችሁ ነው።

367 በነዚህ የሐይማኖት ተቋማት እንዲሁም በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ፡ ኃይል ታገኙ ዘንድ በእያንዳንዱ ቃል ላይ ሙሉ በሙሉ ካልተመገባችሁ፡ እኛ በምንጸልይበት በዚህ ጊዜ፡ ይህን ታደርጋላችሁን?

368 አባት ሆይ፡ ይህ ከባድ ነገር ነው። ለሟች ይህን ማድረግ ቀላል አይደለም። አንተ ሁሉንም ነገር ታውቃለህ። አምላክ ሆይ፡ ይህ በተሳሳተ መንገድ እንዳይተረጎም፡ እለምንሃለሁ። ሕዝብህ ግን፡ በቃልህ ብርሃን፡ እንዲመላለስ እጸልያለሁ።

369 አሁንም፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ማን ማን የተመረጠው እንደሆነ አላውቅም፥ አንተ ታውቃለህ። መምጣትህ መቼ እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን

ይህ በሚሆንበት ጊዜ፡ እነዚህ ሐሰተኞች፡ የተቀቡ ሰዎች፡ ከጅምሩ ትክክል እንዳልሆኑ መናገርህን ብቻ አውቃለሁ።

370 ሙሴ ምንም ማድረግ ስላልቻለ፡ ዝም አላቸው። አንተ የምትለውን ብቻ ተናገረ። ቁንጫዎች ይሁን በል አልከው፥ ይሁን አሉ። ውኃውን ወደ ደም ቀይር አልከው፥ አደረጉት። ሙሴ የተናገርከውን፡ ቃል በቃል ፈጸመ እንጂ፡ ሌላ ምንም አላደረገም፡ ብልሹዎቹ እንዲገለጡ ያደረግኸው አንተው ነበርክ።

371 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬም፡ እግዚአብሔር ነህ። ይህ ቃል ራሱ በዘመን ፍጻሜ እንደሚሆን ተናግሯል። ባለፈው እሁድ እንደነገርነው፡ ብዙ ቅኖች ሰዎች፡ የቃልኪዳኑን ታቦት፡ በሌዋውያን ትከሻ ላይ ሳይሆን፡ በአዲስ ጋሪ ላይ አድርገው፡ እጃቸውን በማንሣት ሞተዋል። “በኃጢአትና በመተላለፍ ሞተዋል፥” ከገዛ ሕሊናቸው ጋር ይከራከራሉ።

372 ብዙ አገልጋዮች ጥናት ውስጥ፡ ቃሉን ያነባሉ፡ ገጹን በፍጥነት ይቀይሩታል፡ ይህን የሚያደርጉት በሕዝቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት፡ ከማህበራዊ አቋም ላለመነጠል፡ ቤተክርስትያናቸው እና ከሐይማኖት ተቋማቸው ላለመነጠል ሲሉ ናቸው። ይህን በፍጹም እንዳናደርግ እግዚአብሔር ይርዳን!

373 ጌታ ሆይ፡ ልባችንን ከዓለም ቆሻሻ ሁሉ፡ አንጻ። ጌታ ሆይ፡ ለመንጻት ዝግጁ ነኝ። ለዚህች ቤተክርስቲያንና ለሚያዳምጡት ሁሉ፡ ይህን ቴፕ ከሚያዳምጥ ማንኛውም ሰው ጋር፡ ዝግጁ ነኝ። ጌታ ሆይ፡ ቆሜ መንጻትን፡ እለምንሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውሰደኝ፡ አፍርሰኝ እና ቀይረኝ እና የምትፈልገው ዓይነት አገልጋይ አድርገኝ።

374 ምክንያቱ፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ “እኔም ከነፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፡” ኢሳይያስ እንዳለው፡ ”ከንፈራቸውም በረከሱባቸው ህዝብ መካከል በመቀመጤ፥ የእግዚአብሔር ራዕይ ሲገለጥ አይቻለሁና፡ ወዮልኝ፡” ኢሳይያስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ መላእክትን ባየ ጊዜ ተናገረ። ጌታ ሆይ፡ የመጨረሻውን ጊዜ አያለሁ፡ እናም እኔ እና ቤተሰቤ ወዮልን፥ እኔ እና ሕዝቤ ወዮልን። የዘላለም አምላክ ሆይ፡ ይቅር በለን። ለራሴም ሆነ ለሕዝቡ እማፀናለሁ። ከማያምኑ ሰዎች ጋር እንዳንጠፋ፡ ነገር ግን ከምዕመናን ጋር እንድንሆን።

375 እያንዳንዱ ሃይማኖት ተቋም፡ ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዱ ወንድ ወይም ሴት... እንደማትወደው እያወቅኩ፡ የሃይማኖት ተቋም እንድትባርክ አልጠይቅህም። ይሁን እንጂ፡ ጌታ ሆይ፡ ከበጎችህ መካከል አንዳቸውም እዚያ ቢሆኑ፡ ይህን ቴፕ እንዲሰሙ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ እንዲሰሙ እና አንተ በምትሰጣቸው ግንዛቤ፡ እንዲረዱ እጸልያለሁ፡ እና አንተን ለመቀበል እንዲወጡ እጸልያለሁ። በዚህ ዘመን መታወር እና ወግ እንዳይታለሉ። በሌላ ዘመን በድን የሆነን ነገር ለመብላት አይሞክሩ። ቃሉን ይውሰዱ።

376 ፈሪሳውያን የሰቀሉህ በዚህ መንገድ ነው፡ ጌታ ሆይ። የሙሴን ዘመን በድን ይሻለናል ባሉ ጊዜ፡ ሊደሰቱበት ሞክረው ነበር፥ በምድረ በዳ፡ በጥላ የሰጠሃቸው፡ በየምሽቱ ትኩስ መና የሰጠሃቸው፡ የእያንዳንዱ ትውልድ ጥላ ነው። የወደቁት እዚህ ላይ ነው። ያ መረዛቸው። ያን የተበከለ ምግብ መብላታቸው፡ ገደላቸው።

በዛሬው ጊዜም፡ በመንፈስ፡ ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነው፡ በሃይማኖታዊ እምነት አማካኝነት፡ በመንፈስ፡ ይገድላቸዋል።

እምላክ ሆይ፡ እርዳን። አሁን ሁሉም ነገር በእጅህ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

ራሳችንን ዝቅ አድርገን ውሳኔያችንን እየወሰንን፡ ይህን እንዘምራለን። እስከመጨረሻው ትሄዳላችሁ?

እኔ አዳኜን መስማት እችላለሁ... (እርሱ ቃል ነው።)
ይጠራኛል፡
እሰማዋለሁ...

“ኦህ፡ ለረጅም ጊዜ ተቅበዘበዝኩ፡ ነገር ግን፡ በእውነት፡ አሁን እርሱን እየሰማሁ ነው፡ ‘እናንተ የተቅበዘበዛችሁ፡ ወደ እኔ ኑ።’”

... ሰማሁ...

377 “‘መስቀላችሁን ተሸከሙ፡ ዕለት ዕለትም ተከተሉኝ።’ ‘አዎ፡ በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድ እንኳ፡ ክፉን አልፈራም፥ በለመለመ መስክ ይመራኛል፡ በእረፍት ውኃ ዘንድ ያሳድረኛል።’”

እሱ ወደሚመራኝ ቦታ...

378 “ጌታ ሆይ፡ ይህን የሥላሴ ውሸት አይቻለሁ። መላውን ዓለም በውስጡ ተዘርቶ አይቻለሁ፡ እንክርዳድ በየቦታው ተዘርቷል። ይሁንና ጌታ ሆይ፡ አሁን ወደምትመራኝ ሁሉ፡ በሐዋርያት ሥራ 19 ላይ እንዳሉት እሆናለሁ። ‘ይህን በሰሙ ጊዜ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዳግመኛ ተጠመቁ።’”

... ተከተሉ፡

“ጌታ ሆይ፡ አንተን ለመቀበል፡ የቻልኩትን ያህል መንገድ ተጉዤያለሁ።”

አሁን እኔ ከእርሱ ጋር ሁሉንም መንገድ እሄዳለሁ።

379 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ከልቤ እንደመጣ አምናለሁ። አሁን እየዘመሩ ካሉ ሰዎች ሁሉ ምናልባትም ይህን ቴፕ ከሚሰሙ ወይም፡ አሁን ከማይሰሙት ሁሉ፡ ከልባቸው እንደሚመነጭ አምናለሁ። ዋጋው ምንም ይሁን ምን፡ ጌታ ሆይ፡ ፈቃደኞች አርገን። እንዲህ፡ “ሌላ ሠራዊት ለመግጠም እንደሚሄድ፡ ወታደር፣ ንጉሥ፡ መጀመሪያ ቁጭ ብሎ ያሰባል፡ ማሸነፍ ይችል ይሆን፡ የዓለምን ነገር መተው ይችል ይሆን? ያን ትታችሁ፡ ከተጻፈው ከእግዚአብሔር ቃል ሠራዊት ውስጥ መቀላቀል፡ ከወታደሮቹ ጋር መሮጥ፡ ከንሰሮቹ ጋር መብረር ትችላላችሁን? ” ጌታ ሆይ፡ በኢየሱስ ስም፡ አድርገው።

380 ታምናላችሁ? ትቀበላላችሁ? እሺ። ጌታ ፈቃዱ ከሆነ፡ ዛሬ ማታ፡ እንደገና እዚህ እንገናኛለን። ይህ እውነት እንደሆነ ታምናላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታኢ።] ግልጽ ነው አይደል? [“አሜን።”]

እንግዲያውስ የኢየሱስን ስም ይዛችሁ ሂዱ።
የዋይታና የሐዘን ልጆች፥
ደስታ እና ምቾት ይሆንላችኋል፡
ሁሉም ቦታ ይዛችሁ ሂዱ...

አሁን፡ አጠገባችሁ ካለው ሰው ጋር ሰላም ተባባሉ።

ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ፡ (የምድር ተስፋ!) የሰማይ ደስታ፥

ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

ለኢየሱስ ስም ስገዱ፡
በእግሮቹም ስር ተደፉ፡
በሰማይ የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ይለብሳል… (ታዲያ፡
  እሱ እግዚአብሔር ነው።)
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

ውድ ስም፡ (ውድ ስም!) ኦህ እንዴት ጣፋጭ ነው! (ኦህ
  እንዴት ጣፋጭ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

ዛሬ ጠዋት አገልጋዮች ሁሉ መታወሳቸውን እገምታለሁ፡ እውቅና አግኝተዋል።

381 አንድ ሰው ሳምንቱን ሙሉ ሲጸልይ ሲቆይ፡ እነዚህ ጥቅሶች፡ ከፊት ለፊታችሁ ቆመው ሲመለከት፡ ምን ማለት እንደሆነ ይጠይቃል። ጳውሎስ “ወንጌልን ባልሰብክ፡” “ወዮልኝ፡” ብሏል። በመንገዱ ማብቂያ ላይ፡ “የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ እንደ ተሰጠኝ ለእናንተ ከማወጅ አልተቆጠብኩም፡” ብሏል።

አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን እረሳለሁ፡ ሕፃናትን ማቅረብ፡ አደራ መስጠት።

በቀደም፡ ቢሊ ሲናገር፡ አንድ ሰው መጥቶ፡ “ልጄን ለእግዚአብሔር አደራ ለመስጠት፡ ላለፉት ሁለት አመታት እየተመላለስኩ ነው፡” ብሎኛል አለ።

382 ቢሊም አለው፡ “እባክህ አይክፋህ። እኔ ራሴ፡ አንድ ዓመት የሞላው ሕፃን አለኝ፥ እሱም ገና አደራ አልተሰጠም፡ ገና። ስለዚህ እሱ ራሱ ወደዚያ የሚሄድበት ዕድሜ እስኪደርስ እጠብቃለሁ፡ መሰለኝ አለው።”

ስለዚህ ወንድም፡ እኅት፡ እንደሱ—አይደለም፡ አያችሁ፡ እኔ… አንድ ነገር፡ ልጆቻችንን አደራ መስጠት ይገባናል።

383 ሁሉንም ሰው ማጥመቅ ይኖርብናል። ገንዳ አለን፡ ውሃም አለን። ካልተጠመቃችሁ፡ የሚያግዳችሁ ምንድን ነው? እዚህ ውኃ አለ። አሁኑኑ ኑ። እስከ ማታ አትጠብቁ፡ አሁኑኑ ኑ። ንስሐ የገባውንና ኃጢአቱን የተናዘዘውን ሁሉ የሚያጠምቅ ሰው እዚህ አለ። ደርዘን ጊዜ ተጠምቃችሁ ከሆነም፡ የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያጠምቋችኋል። አያችሁ? እኛ እንደሱ ነን።

384 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ መልዕክቱ በልቤ ውስጥ ነው። መናገር አለብኝ። ባለቤቴ፡ ልጆቼ፡ ፓስተሬ፡ ወይም ሌላ ሰው የሚናገረው ምንም ይሁን ምን፡ የነፍሴ ዓላማ ይህ ብቻ ነው። እርሱ ጌታዬ ነው። ይህ መናገር አለብኝ። የነፍሴ ዓላማ ይህ ነው።

385 እናም አሁን፡ ብዙ ጊዜ፡ አገልጋዮችን ማስታወስ እረሳለሁ። ምናልባትም… ወንድማችን፡ ወንድም ኔቪል፡ የተወደደ ሰው ነው። እዚህ ያላችሁ ወንድሞች፡ እናንተን በማግኘታችን ደስተኞች ነን።

386 ወንድሜ ሆይ፡ እናንተም ከዚህ የተለየ አመለካከት አላችሁ ብለን፡ አንቃወምም። ምናልባት ብዙዎቻችሁ የሰላሴ ሰባኪዎች ትሆኑ ይሆናልና። እኛ ከእናንተ ጋር መጣላት አንፈልግም። እንወዳችኋለን። ካልወደድናችሁ፡ ይህን ባላምን ኖሮ፡ በጉልበቴ ተንበርክኬ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ትክክል አድርገኝ፡" እስክል ድረስ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን አልወጣም ነበር።

387 እብሪተኛነት አልፈልግም፡ ራስ ወዳድ መንፈስ ከእኔ ጋር እንዲቀላቀል አልፈልግም። መንፈሴ ንጹሕ እና የጸዳ፡ የወንድማማች ፍቅር፡ በመንፈስ ቅዱስ እንዲቀደስ እፈልጋለሁ። አሁን፡ አንድ ሰው በእኔ ላይ መጥፎ ነገር ቢያደርግ፡ ምንም ችግር የለውም። እና ምንም እንኳን በእነሱ ላይ የመመለስ መብት ቢኖረኝም፡ በሕይወቴ ያንን አልፈልግም። አልፈልግም፡ ፍቅር እንዲኖረኝ እ—እሻለሁና። በፍቅር ለመታረም ዝግጁ መሆን እፈልጋለሁ፡ ሰማይ ላይ መልስ መስጠት የሚችል ፍቅር።

388 የተለየሁ ነኝ ማለቴ አይደለም። ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ካቶሊክ፡ ፕሬስቢተሪያን፡ ማንነታችሁ ምንም ይሁን ምን፡ እነዚህን ነገሮች የምናገረው የተለየሁ እንድሆን፡ ትዕቢተኛ ስለሆንኩ አይደለም። ይህን ካደረግሁ ግብዝ ነኝና፡ በዚሁ መሠዊያ ወድቄ፡ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ይኖርብኛል።

389 ነገር ግን የምናገረው፡ ከፍቅሬ የተነሳ እላችኋለሁ፡ ወዴት እየሄዳችሁ እንደሆነ እያለሁና። አሁን፡ እኔ ከራሴ ይህን አልልም፡ ደግሞም ይመስለኛል አልልም። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነው። ይህም እውነት ነው። ለእነዚያ ነገሮች እወዳችኋለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

390 አሁን ከመሄዳችን በፊት፡ እስቲ፡ የዚህን መዝሙር ሌላኛውን ግጥም እንዘምር። ከቻላችሁ፡ ዛሬ ማታ እዚህ እንድትሆኑ እንፈልጋለን። ካልቻላችሁ፡ እስክንገናኝ ድረስ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ከምድሩ በረከት የተወደደውን እንዲሰጣችሁ እ—እንጸልያለን፡ አያችሁ።

... ሰም ውሰድ

65-0725M በዘመኑ ፍጻሜ የተቀቡ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org